

የኢትዮጵያ
ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)

40ኛ መደበኛ መግለጫ

የኢሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ምርመራ ግኝቶች
ዓመታዊ መግለጫ

ግንቦት 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ማውጫ

አጭር ዳሰሳ፡ 1

አገር አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ፡ 4

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) 5

የመደበኛ መግለጫው ወሰን እና ዋና አላማ 6

በዚህ ምርመራ የተሸፈኑ አካባቢዎችና ምርመራው የተካሄደበት ጊዜ 7

የመረጃ ምንጮችና የማስረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች 7

የምርመራው ስራ ውስንነትና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች 8

የምርመራ ስራው ዋና ዋና ግኝቶች 8

አማራ ክልል፡ 8

በአማራ ክልል በተከሰተው ግጭት ምክንያት የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፡ 20

የግጭቱ መነሻ ምክንያት፡ 20

በግጭቱ የተሸፈኑ አካባቢዎች እና የደረሱ የመብት ጥሰቶች፡ 20

ክፍል አንድ፡ 22

ክፍል ሁለት፡ 51

ኦሮሚያ ክልል፡ 57

ትግራይ ክልል፡ 68

ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፡ 70

ጋምቤላ ክልል 75

አፋር ክልል፡ 76

ሲዳማ ክልል፡ 80

ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፡ 82

ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፡ 88

ተያያዥ የህግ ግዴታዎች 97

ምክረ ሀሳብ 103

ዋና ጽ/ቤት፡ አዲስአበባ

አ.አ ስታዲየም አጠገብ፣ላሊበላ ሬስቶራንት ጎን፣ ሣህለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ፣ቢሮ ቁጥር 19

ኢ-ሜይል:info@ehrco.org

ድረገጽ: www.ehrco.org

ፌስቡክ፡https://www.facebook.com/ehrco1/

ትዊተር፡ https://www.twitter.com/ehrcoethio

ቴሌግራም፡ https://t.me/ehrco

የፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የሰብዓዊ መብቶች ከትትል እና ምርመራ መምሪያ፡ አዲስ አበባ

ስልክ: (+251) 011 558-2387

ኢሜይል:info@ehrco.org

ቀጠና / ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

ደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ሐዋሳ - ስ.ቁ (+251) 046 220-4500፣ ፖ.ሳ.ቁ 360

ሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና፡ባሕርዳር- ስ.ቁ (+251) 058 220-0240፣ ፖ.ሳ.ቁ 1115

ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና አዳማ - ስ.ቁ (+251 22 212- 6857፣ ፖ.ሳ.ቁ 463

ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና ሐረር - ስ.ቁ (+251) 025 411 6845፣ ፖ.ሳ.ቁ 2596

ጂግጂጋ- ስ.ቁ (+251) 025 2 78 42 40

ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀጠና፡አዲስ አበባ- ስ.ቁ (+251)011 551-7704፣ ፖ.ሳ.ቁ 2432

አጭር ዳሰሳ፡

ይህ የኢሰመጉ 40ኛ መደበኛ መግለጫ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ውስጥ በመጀመሪያ ዙር ከሐምሌ 09 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ 20 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ስድስት (6) የምርመራ ቡድን በማዋቀርና በሁለተኛው ዙር ጥቅምት ወር 2016 ዓ.ም እና ከጥር 29 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ የካቲት 01 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ አምስት (5) የምርመራ ቡድኖችን በማወቀር የምርመራ ስራው ተከናውኗል፡፡

ይህ ልዩ ዘገባ የተዘጋጀው ኢሰመጉ የሰብዓዊ መብት የምርመራ ባለሙያዎች ባደረጉት ቃለመጠይቆች (ከተጎጂዎች፣ ምስክሮች፣ የመንግስት እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አመራሮች፣ እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ያካትታል)፣ የደህንነት ስጋት ባለባቸው አካባቢዎች የርቀት የምርመራ ዘዴዎችን በመጠቀም፣ የቡድን ውይይቶች፣ የመስክ ምልከታ ስራዎች፣ የመንግስት እንዲሁም መንግስታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ውይይቶች እና ከእነዚህ አካላት የተገኙ አስረጂ ሰነዶችን በመጠቀም መረጃዎችን ኢሰመጉ አሰባስቧል፡፡

በእዚህ ልዩ መግለጫ ላይ ያሉ ግኝቶችን በአጭሩ ስንመለከት፤ በአማራ ክልል በሶስት መሰረታዊ ክስተቶች የተነሳ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ይዳስሳል፡፡ በመጀመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማዕከላዊ ጎንደር ዞን አለፋ ወረዳ አለፋ ከተማ የታጠቁ ኃይሎች ተጠርጣሪዎችን ለማስመለጥ በፈጸሙት ጥቃት በሰዎች ላይ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችና በዋግህምራ ልዩ ዞን ሰቆጣ ከተማ በአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ላይ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ይዳስሳል፡፡

ሁለተኛ በአማራ ክልል በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች ማለትም በእናርጅ እናውጋ ወረዳ በደብረወርቅ ከተማ፣ በደጅን፣ በደንበጫና በፍኖተሰላም ከተሞች ላይ ከሚያዚያ 2015 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 2015 ዓ.ም ከክልል ልዩ ሃይል አባላት መልሶ የማደራጀት እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ በተፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች የተፈጠሩትን የሰብዓዊ መብቶች እንደ ግድያ፣ የአካል ጉዳት፣ ንብረት ውድመት እና ሌሎችንም ጥሰቶች ይህ መደበኛ መግለጫ የሚዳስስ ይሆናል፡፡

ሶስተኛ በአማራ ክልል በምዕራብ ጎጃም ዞን ደቡብ አቸፈር ወረዳ እና መሸንቲ ከተማ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በእዚህ ልዩ መግለጫ የተሸፈኑ ሲሆን በክልል በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ አርሶ አደሮች ወቅቱን የጠበቀና በቂ የሆነ የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ባለማግኘታቸው የማዳበሪያ አቅርቦት እንዲደረግላቸው በሰላማዊ ሰልፍ የሚመለከተውን የመንግስት አካል የጠየቁ ሲሆን የመንግስት የፀጥታ አካላት በወሰዱት ተመጣጣኝ ያልሆነ የሀይል እርምጃ የተፈጸሙ ግድያዎችንና የአካል ጉዳቶችን ልዩ መግለጫው አካትቶ ይዟል፡፡

በአራተኛ ደረጃ በአማራ ክልል በክልሉ በሚንቀሳቀሱ የታጠቁ ኃይሎች እና በመንግስት የጸጥታ አካላት መካከል ግጭት የተነሳ ሲሆን በጊዜ ሂደት ይህ ግጭት መላውን የአማራ ክልል በሚባል ደረጃ ሊያካልል ችሏል፡፡ በእዚህ ክፍል ላይ ግጭቱ በሸፈናቸውና ኢሰመጉ የምርመራ ስራ ባከናወነባቸው በህርዳር ከተማ፣ ምዕራብ ጎጃም ዞን፣ አዊ ብሔረሰብ ልዩ ዞን፣ ሰሜን ጎጃም ዞን፣ ምስራቅ ጎጃም ዞንና ማዕከላዊ ጎንደር ዞን ጎንደር ከተማ እና ሌሎች አካባቢዎች ውስጥ የተፈጸሙ እንደ ግድያ፣ ጾታዊ ጥቃት፣ አካል ጉዳት፣ ንብረት ውድመት፣ አስገድዶ መሰወር እና ሌሎችም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ዝርዝር ሁኔታ አሳይቷል፡፡

በእዚህ መደበኛ መግለጫ ላይ ኢሰመጉ በትግራይ ክልል ከነበረው የሰሜኑ ኢትዮጵያ የትጥቅ ግጭት ጋር ተያይዞ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለመመርመር ያደረገው ሙከራ የሚገኝ ሲሆን ኢሰመጉ ከትጥቅ ግጭቱ መነሻ ጊዜ አንስቶ በክልሉ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለመመርመር ያደረገው ሙከራ፣ ከሰላም ስምምነቱ በመቀጠል ከህዳር 2016ዓ.ም ጀምሮ በክልሉ በአካል በመገኘት የምርመራ ስራን ለማድረግ የሞከረ ሲሆን ለተለያዩ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስዳደር ቢሮዎች የመረጃ ጥያቄን እና የፈቃድ ጥያቄን ያቀረበ ቢሆንም ይህ ሳይሳካ ቀርቷል፡ ፡ ነገር ግን የክልሉ ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የተፈናቃዮችን ቁጥር ለማጋራት ችሏል፡፡

የምርመራ ባለሙያዎች በትግራይ ክልል በአካል ተገኝተው በነበረበት ወቅት ካደረጉት ምልከታ መረዳት እንደተቻለው በክልሉ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የአገር ውስጥ ተፈናቃይ እንደነበረ እና እነዚህም ተፈናቃዮች ምንም አይነት እርዳታ እያገኙ እንዳልሆነ ይህም የሆነበት ዋነኛ ምክንያት ዓለም አቀፍ የሆኑት እርዳታ ሰጪ ተቋማት በክልሉ ይሰጡ የነበረውን ሰብዓዊ ድጋፍ ማቋረጣቸው እንደሆነ እንዲሁም የክልሉ ጊዜያዊ አስተዳደር እና የፌዴራል መንግስት በቂ እርዳታ ማቅረብ ባለመቻላቸው መሆኑንና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮችን በሪፖርቱ ውስጥ ተካትተው ይገኛሉ፡፡

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም መተከል ዞን ማንዱራ ወረዳ ግልገል በለስ ከተማ በልዩ ስሙ ቻይና ካምፕ በሚባለው ቦታ ማንነትን መሰረት ያደረገ ጥቃት በአካባቢው በሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች የተፈጸመ ሲሆን በእዚህም ጥቃት ግድያ፣ የአካል ጉዳት፣ ንብረት ውድመትና መፈናቀል ተከስቷል፡፡ ይህ ልዩ መግለጫም የጥቃቱ መነሻ ምክንያትን፣ የተፈጸመበትን ጊዜ፣ ጥቃት የፈጸሙትን አካላትና በመንግስት የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎችን አካትቶ በዝርዝር ይዟል፡፡

በአፋር ክልል በሚገኘው አዋሽ ወንዝ ላይ ለመገንባት ለተሞከረው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ መስኖ ይሆን ዘንድ የተገደበው አዋሽ ወንዝ ግድብ ማስተንፈሻ ወደ አሳይታ እና አፋንቦ ወረዳዎች በመለቀቁ ምክንያት በአሳይታ እና አፋንቦ ወረዳዎች ላይ የደረሱ ጉዳቶችን ኢሰመጉ ከሃምሌ 10 ቀን 2015ዓ.ም እስከ ሃምሌ 13 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በአካል በመገኘት ባደረገው ምርመራ ስራ ያገኛቸው ግኝቶች ሌላው በእዚህ መግለጫ ላይ ተካቶ የሚገኝ ሲሆን በተፈጠረው ክስተት ምክንያት በተባሉት ወረዳዎች ላይ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ንብረቶቻቸው ላይ ትምህርት ቤቶችን እንዲሁም የጤና ኬላዎችን ጨምሮ የደረሱ ጉዳቶች የተካተቱ ሲሆን ዝርዝር ጉዳዮችን ሪፖርቱ ይዳስሳል፡፡

አሰመጉ በሲዳማ ክልል ማዕከላዊ ሲዳማ ዞን ሎካ አባያ ወረዳ በሚገኙ አልቦ፣ ጭረቻ፣ ቡሬ ቡከቶ እና ፉልቃ በሚባሉ ቀበሌዎች በሲዳማ ክልል ማዕከላዊ ሲዳማ ዞን ውስጥ የሚገኘው የሎካ አባያ ወረዳ ፓርክ ካለበት በግምት 10 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከአጼ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ በአካባቢው ሰፍረው የሚገኙ ነዋሪዎች ፓርኩ በ2007 ዓ.ም ባደረገው የማካለል ስራ ምክንያት እነዚህ ነዋሪዎች በፓርክ ውስጥ በመከለላቸው ምክንያት በሚል በአልዳቦ ቀበሌ ታህሳስ 22 ቀን 2016 ዓ.ም፣ በጭረቻ ቀበሌ ታህሳስ 06 ቀን 2016 ዓ.ም፣ በቡራ ቡከቶ እና ፉልቃ ቀበሌዎች በታህሳስ 02 ቀን 2016 ዓ.ም በመንግስት አካላት በነዋሪዎች ላይ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን እና ከህግ አግባብ ውጪ በንብረት ላይ የደረሱ ከፍተኛ ውድመቶችን እንዲሁም በሀዋሳ ከተማ ሀዌላ ክፍለ ከተማ ጋራ ሪቀታ

ቀበሌ ነዋሪ በሆኑት አቶ ራቴ ዋኤና ቤተሰቦቻቸው ላይ የአካባቢው ነዋሪ በሆኑ ግለሰቦች በአካባቢው የሚገኙ ባለስልጣን ዘመዶቻቸውን መኪታ በማድረግ የተፈጸመ ድብደባ፣ ህገወጥ እስርና የንብረት ውድመት በልዩ መግለጫው ላይ በዝርዝር ተካተዋል፡፡በተጨማሪም ኢሰመጉ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በደራሼ ዞን በጋቶ፣ ኩሱሜ እና በአርጉባ ጣናአ አካባቢዎች የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ከ10/11/2015 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 14/11/2015 ዓ.ም ድረስ የምርመራ ባለሙያ በቦታው በመላክ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ምርመራ ያካሄደ ሲሆን በእዚም መሰረት በተደራጁ ቡድኖች አማካኝነት በአንድ ቤተሰብ አባላት ላይ በ11/06/2015 ዓ.ም የተፈጸሙ ግድያዎችንና በአካባቢው በሚኖሩ ሰዎች ላይ ማንነትን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችንና የተፈጸሙ የንብረት ማቅደም እንቅስቃሴዎችን በተጨማሪም ኮንሶ ዞን ደራሼ ወረዳ ጋቶ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ ገረሱ ከበደ ኩሴ የደረሰባቸውን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፥ ጋሞ ዞን አርባምንጭ ዙሪያ ወረዳ የሻራ ቀበሌን ወደ ክልል ከተማ ለማስገባት የጋሞ ዞን አስተዳደር፣ የአርባምንጭ ከተማ አስተዳደርና የአርባምንጭ ዙሪያ ወረዳ አስተዳደር ውሳኔ ጋር በተያያዘ የተከናወነውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዲሁም በቀድሞ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በአሁኑ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አማሮ ዞን ቡኒት ቀበሌ ጋር በተያያዘ የተከሰቱትን የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን መግለጫው በዝርዝር አካቶ ይዟል፡፡

ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ጋር በተያያዘ ጥር 14 ቀን 2015 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ተደርጎ በነበረው መግባባት ላይ ያልተደረሰበት የሀይማኖት አባቶች ሹመት ጋር ተያይዞ በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ግጭቶች የተፈጠሩ ሲሆን ይህንንም ግጭት ተከትሎ በሻሸመኔ ከተማ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ኢሰመጉ በአካል በመገኘት ምርመራ ያደረገ ሲሆን በእዚህ ልዩ መግለጫ ላይ በእዚህ ግጭት ምክንያት በመንግስት የጸጥታ አካላት እና በሌሎች በተደራጁ ቡድኖች የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን አካቶ ይዟል።

ኢሰመጉ በ27/12/2014 ዓ.ም በጋምቤላ ክልል የሚገኙ ተፈናቃዮችን የጎበኘ ሲሆን ተፈናቃዮቹ ከ2006ዓ.ም ጀምሮ ከደቡብ ሱዳን ከኑዌር ብሔረሰብ ዞን አኮቦ ወረዳ አራት ቀበሌዎች አካባቢያቸውን ለቀው ጎግ ወረዳ ፑኝዶ አቅራቢያ 04 ቀበሌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኙ ሲሆን በታህሳስ ወር በተፈጸመ ጥቃት በእነዚህ ተፈናቃዮች ላይ የተፈጸሙ ግድያ፣ የአካል ጉዳት እና ንብረት ውድመቶችን ይህ ልዩ መግለጫ አካቶ ይዟል።

ኢሰመጉ ከህዳር 28 ቀን 2016 ዓ.ም ዓ.ም እስከ ታህሳስ 02 ቀን 2016 ዓ.ም ዓ.ም ድረስ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ጢጆ ለቡ ቀበሌ፣ ሑላ ጢጆ ሴሮ ቀበሌ እና በሮቤ እንደቶ ቀበሌዎች ባለሙያዎችን በማሰማራት በተጠቀሱት አካባቢዎች ላይ ህዳር 14 ቀን፣ ህዳር 21 እና ህዳር 24 ቀን 2016 ዓ.ም ዓ.ም የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የምርመራ ስራን አከናውኗል በእዚህ ልዩ መግለጫ ላይም የምርመራ ስራው ግኝቶች በዝርዝር ተካተው ይገኛሉ፡፡

በእዚህ መደበኛ መግለጫ ላይ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ከላይ በተጠቀሱት ቦታዎች ላይ የተፈጸሙ ሲሆን እነዚህን በምርመራ የተገኙ የመብት ጥሰቶችን ከአገር አቀፍ፣ ከአህጉር አቀፍ እና ከዓለም አቀፍ ህጎች አንጻር በመዳሰስ የተፈጸሙትን የመብት ጥሰቶች ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በእዚህም መሰረት እንደ ግድያ፣ ጾታዊ ጥቃት፣ የአካል ጉዳት፣

አስገድዶ መሰወር፣ ንብረት ውድመት፣ አላግባብ በልማት ምክንያት የሚፈጸሙ ማፈናቀሎች እና ሌሎችም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በእዚህ መደበኛ መግለጫ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

ስለሆነም በእዚህ ልዩ መግለጫ ላይ የተዳሰሱ የሚመለከታቸው የፌደራል እና የክልል መንግስታት ለተፈጸሙት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በቂ ትኩረት በመስጠት ተገቢውን አስፈላጊ የምርመራ ስራ በማከናወን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የፈጸሙ አካላትን በህግ አግባብ ተጠያቂ እንዲያደርጉ፣ በግጭቶች ምክንያት ለተፈናቀሉ ሰዎች ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርጉ፣ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የበኩላቸውን አስተዋጾ እንዲያደርጉ፣ ለተጎጂዎች ተገቢውን ካሳ እንዲሰጡ እና ሌሎችም አስፈላጊ እርምጃዎችን እንዲወስዱ እንዲሁም ለሎች ባለድርሻ አካላት እንደ ሀይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ሲቪል ማህበራት፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሚዲያዎችና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በሙሉ የበኩላቸውን አስተዋጾ እንዲያደርጉ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል።

አገር አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ፡

በኢትዮጵያ ያለው የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ሁለት ገጽታ ያለው ሲሆን በጊዜ ሂደት ውስጥ መሻሻሎችንም ከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችንም ሲያስተናግድ ቆይቷል፡፡ ለእዚህ መግለጫ ይረዳ ዘንድ 2010 ዓ.ም እንደ መነሻ ነጥብ በመጠቀም አጭር የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ዳሰሳ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

2010 ዓ.ም (በዋናነት በኦሮሚያ ክልል) በመንግስት የውስጥ ለውጥ መቋጫነት ኢትዮጵያ ለተወሰኑ አመታት ከቆየ ውጥረት የወጣችበት ጊዜ ነበር፡፡ ከእዚህ የጊዜ ነጥብ ጀምሮ በአገሪቱ መንግስት አማካኝነት ልዩ ልዩ ከሰብዓዊ መብቶች ጋር ግንኙነት ያላቸው ሂደቶች ተከናውነዋል፡፡ በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት ከአገር ውጪ ይገኙ ለነበሩ ግለሰቦች እና የትጥቅ ትግል የነበሩ አካለት ጥሪ ተደርጓል፣ የፖለቲካ ምህዳሩ ጥሩ በሚባል ደረጃ መሻሻሎችን አሳይቷል፣ የህግ እና የተቋማት ማሻሻያ እና ሌሎችም እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡

ለማሳያነት ያክል ለረዥም ጊዜ ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በር ከፋች የነበረው የጸረ-ሽብር አዋጅ መሻሻል፣ የመገናኛ ብዙሀን አዋጅ ላይ የተደረገው ማሻሻያ፣ የሲቪል ማህበራትን የሚመለከተው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ መሻሻል፣ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ መሻሻል፣ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች መብቶችን በዝርዝር የሚይዘው የካምፓላ ስምምነትን ማጽደቅ በመንግስት በኩል የተወሰዱ መልካም የሚባሉ እርምጃዎች ናቸው፡፡ ከእዚህ በተጨማሪም በተቋማት ላይ ከፍተኛ የሚባል ተሀድሶ የተደረገ ሲሆን ከእነዚህም መካከል በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ላይ መቋቋሚያ አዋጁን ከማሻሻል ጀምሮ በተቋሙ ላይ የተደረገው ተሀድሶ እና በምርጫ ቦርድ ላይ የተደረገው ተሀድሶ ይገኙበታል፡፡

ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሱት መሻሻሎች የተደረጉ ቢሆንም በአገሪቱ በተደጋጋሚ (ከላይ እንደተጠቀሰው ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ) የሚነሱ ግጭቶች፣ በታጣቂ ቡድኖች የሚፈጸሙ ጥቃቶች፣ በመንግስት የጸጥታ አካላት ከህግ አግባብ ውጪ የሚፈጸሙ ግድያዎችና እስራቶች ከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እንዲፈጸሙ ምክንያት ሆነዋል፡፡

ለማሳያነት በኦሮሚያ ክልል በተደጋጋሚ በታጣቂ ኃይሎች የሚጸሙ ጥቃቶች፣ በሰሜኑ ኢትዮጵያ ክፍል ተነስቶ የነበረው የትጥቅ ግጭት፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሚፈጸሙ ማንነትን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች፣ በአማራ ክልል የተነሳው ግጭት፣ በተለያዩ አካባቢዎች በመንግስት የጸጥታ አካላት የሚፈጸሙ ከህግ አግባብ ውጪ የሆኑ ግድያዎች እና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል።

በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ሰዎች ለከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እየተጋለጡ ይገኛሉ። ምንም እንኳን በሰሜኑ ኢትዮጵያ ክፍል ተነስቶ የነበረው የትጥቅ ግጭት በፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት መባቻ ቢያገኝም ግጭቱን ተከትሎ የተነሱ ሰብዓዊ ቀውሶች አሁንም ድረስ በአስከፊ ሁኔታ እንደቀጠሉ ይገኛሉ። በአማራ ክልል የተነሳው ግጭት ደግሞ ሌላው አሳሳቢ ክስተት ሲሆን ግጭቱ አሁንም ድረስ መቀጠሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በአስከፊ ሁኔታ እንዲቀጥሉ ምክንያት ሆኗል።

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ - ኢሰመጉ በበጎ አድራጎትና ማኅበራት አዋጅ ቁጥር ፱፲3/20፱ መሠረት ሐገር በቀል ድርጅት ሆኖ በ 1984 ዓ.ም የተመሠረተና በምዝገባ ቁጥር ፲146 ከ 02/፲1/፲1 ዓ.ም ጀምሮ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ዳግም ተመዝግቦ በሕጋዊነት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅት ነው። ኢሰመጉ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ሲሆን፣ ዓላማውም በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የበኩሉን አስተዋጽዖ ማድረግ ነው።

ኢሰመጉ የተቋቋመበት ዋነኛ ዓላማው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የጎለበተባት፣ የሕግ የበላይነት የሰፈነባት እና ሰብዓዊ መብቶች የሚከበሩባት ኢትዮጵያን ማየት ነው። በሥራውም ከማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የኃይማኖት ተቋም፣ የብሔረሰብ ቡድን፣ ማኅበራዊ መደብ ወዘተ የማይወግን፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ነው። ኢሰመጉ ላለፉት 32 ዓመታት በቆመላቸው ዐበይት ዓላማዎች ላይ በመመርኮዝ ሁለንተናዊ፣ ሐገራዊና ሕዝባዊ ተልዕኮ በመያዝ በነደፋቸው በርካታ የመርሐ -ግብር ተግባራት አማካኝነት ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የሕግ የበላይነትና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲሰፍንና በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲኖር የበኩሉን አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ ይገኛል።

የኢሰመጉ ዋነኛ ተግባሩ የኢትዮጵያን የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝና ሁኔታ መከታተል፣ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በማጣራትና በመተንተን በማስረጃ የተደገፉ መግለጫዎችን ማውጣት ነው። ኢሰመጉ በሚያወጣቸው መግለጫዎች ሁሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕና ካሣ እንዲያገኙ፣ የጥሰት ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁና ወንጀል ሠርቶ በነጻ የመኖር ልማድ እንዲያበቃ፣ ከእያንዳንዱ ክስተት ትምህርት ተወስዶ ለወደፊቱ ጥንቃቄና ተገቢው የፖሊሲና የአፈጻጸም እርማት እንዲደረግ ሲወተውትና ሲጠይቅ ቆይቷል፣ አሁንም በመጠየቅ ላይ ነው፤ ለወደፊትም በዚሁ ይቀጥላል።

ከኢሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ክትትል ተግባራት መካከል፣ የሕግ ታራሚዎችን መጎብኘትና ሰብዓዊ መብቶቻቸው መጠበቃቸውን መከታተል፣ የፍርድ ቤቶችን ሒደት ፍትሐዊነት መከታተል እንዲሁም በመንግሥት የወጡና የሚወጡ ሕጎችን ይዘትና አፈጻጸማቸውን ከሰብዓዊ መብቶች አንጻር መመርመር ይገኙበታል። ከእነዚህ በተጓዳኝ ኢሰመጉ በተለይ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሰለባ ለሆኑ ሰዎች የተለያየ ደረጃና መልክ ያለው የሕግ ድጋፍ ይሰጣል።

በእስካሁኑ ቆይታው ኢሰመጉ 39 መደበኛ መግለጫዎችና 154 ልዩ መግለጫዎችን በተጨማሪም በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በርካታ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይፋ አድርጓል። ኢሰመጉ አሁን በሚገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም ቢሆን፣ ሁኔታና ዐቅም በፈቀደለት መጠን የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የሕግ የበላይነት እና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ካለው የጸና ዓላማ አኳያ በመሥራት ላይ ይገኛል።

ኢሰመጉ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ዘርፈ ብዙ ጫናዎች ሲደረግበት የነበረ እና አሁንም እየተደረገበት ያለ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋም ሲሆን እነዚህ ከመንግስት በኩል የሚደረጉ ጫናዎች በጊዜ ሂደት መጠናቸውን እየጨመሩ በመቀጠል ላይ ይገኛሉ፡፡ ኢሰመጉ በተቋሙ ላይ እንዲሁም በሰራተኞች፣ በአመራሮች፣ በአባላት እና መረጃ በሚያጋሩት ላይ ተደጋጋሚ የሚባል ጫና የሚደርስ ሲሆን ከእነዚህም ጫናዎች መካከል እንደ ግድያ፣ እስራት፣ ዛቻ፣ ማስፈራራት፣ የቢሮ ሰበራ፣ የመረጃ እና የፈቃድ ክልከላ የሚገኙት ሲሆን ኢሰመጉ አቅም በፈቀደ መጠን በእነዚህ ጫናዎች ውስጥም ጭምር የሰብዓዊ መብቶች ምርመራ፣ ክትትል፣ ስነዳ፣ ሪፖርት እና ውትወታ ስራዎችን አጠናክሮ በመስራት ላይ ይገኛል፡
:

የመደበኛ መግለጫው ወሰን እና ዋና አላማ

ይህ 40ኛ መደበኛ መግለጫ በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ማለትም በአማራ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ፣ በሲዳማ፣ በኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በትግራይ እና በአፋር ክልሎች ውስጥ የተፈጸሙ ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በመመርመር የደረሰውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት አጠቃላይ ሁኔታ እና በመንግስት በኩል ሊደረጉ የሚገባቸው ሁኔታዎች በመጠቆም ማስተካከያ እንዲደረግ ለሚመለከታቸው አካላት ጥሪ ማቅረብ፣ በተጠቀሱት አካባቢዎች ላይ እየደረሱ ያሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በአስቸኳይ እንዲቆሙና ለተጎጂዎችም አፋጣኝ ዘላቂ መፍትሄ እንዲሰጣቸው እንዲሁም ተመሳሳይ የመብት ጥሰቶች እንዳይፈፀሙ ተገቢ ስራዎች እንዲሰሩ ለማሳሰብና ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችም ተገቢውን ካሳ የሚያገኙበት መንገድ እንዲመቻች፣ በሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የተሳተፉትም አካላት በህግ እንዲጠየቁ እንዲሁም ተመሳሳይ የመብት ጥሰት እንዳይፈፀም አስተማማኝና ዘላቂ የሆነ የህግ፣ የፖሊሲና የተቋማት ዝግጅት እንዲደረግ ለመጠየቅና ለመወትወት ነው፡፡ በተጨማሪም ኢሰመጉ አቅም በፈቀደ መጠን በእዚህ መደበኛ መግለጫ ላይ የተዘረዘሩትን ግኝቶች የሰብዓዊ መብቶች ምርመራ የመረጃ ምዘና በሚጠይቀው መሰረት ያቀረበ ሲሆን ይህ መደበኛ መግለጫ በተሸፈኑት አካባቢዎች ያለውን የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ አጠቃላይ ምስልና መጠን የሚያይ ባለመሆኑ መንግስት እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት በእነዚህ ግኝቶች ላይ ተጨማሪ ምርመራን እንዲያከናውኑ እና ግኝቶቹን እንዲያጠናክሩ በእዚሁ አጋጣሚ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

ኢሰመጉ የዚህን መደበኛ መግለጫ ይዘትና ዓላማ በተፃረረ መልኩ፣ ከሕግና ከመልካም አስተሳሰብ ውጪ በሆነ መንገድ ማንም እንዲጠቀምበት አይፈቅድም። ይህንንም ዘገባ የአገር ሰላምን ለማደፍረስ፣ ግለሰቦችንም ሆነ ቡድኖችን ለማጥቃት፣ ከሕግ አግባብ ውጪ ሌሎች ሲጠቀሙበት ቢገኝ ኢሰመጉ ከወዲሁ አጥብቆ ያወግዛል፣ ኃላፊነቱንም እንደማይወስድ ያሳስባል።

በዚህ ምርመራ የተሸፈኑ አካባቢዎችና ምርመራው የተካሄደበት ጊዜ

ይህ 40ኛ መደበኛ መግለጫ የሚመለከተው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማዕከላዊ ጎንደር ዞን አለፋ ወረዳ አለፋ ከተማ፣ ጎንደር ዙሪያ ማክሰኝት ከተማ፣ ዋግህምራ ልዩ ዞን ሰቆጣ ከተማ፣ አበርገሊ እና አካባቢው፣ ደቡብ ጎንደር ዞን እብናት ከተማ፣ ሰሜን ጎጃም ዞን ደቡብ አቸፈር ወረዳ አንካስ ሙንግት ቀበሌ ስር በሉ መንደሮች፣ መርዓዊ ከተማ አስተዳደር፣ ባህርዳር ዙሪያ ወረዳ መሸንቲ ከተማ፣ ምስራቅ ጎጃም ዞን እናርጅ እና እናውጋ ወረዳ፣ ደብረወርቅ ከተማ፣ ደጀን ከተማ፣ ምዕራብ ጎጃም ዞን ደንበጫ ከተማ እና ፍኖተ ሰላም ከተማ፡፡ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መተከል ዞን ፓዌ ወረዳ፡፡

በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ፣ ቄለም ወለጋ ዞን ጊዳሜ ወረዳ እና ሻሸመኔ ከተማ፡፡ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አሳይታ ወረዳ ዋሙሌ፣ ኮሮዶራ፣ ካርቡደ፣ አዳደሊ፣ በርር እና ገላሌ ቀበሌዎች እንዲሁም አፋምቦ ወረዳ አለሰበቦሎ ቀበሌ እና ሆነጉቢ ቀበሌዎች፡፡ በጋምቤላ ክልል ጎግ ወረዳ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደራሼ ዞን አርጉባ ጣናኦ ቀበሌ እና ኮንሶ ዞን ፉጨጫ እና ጋቶ ቀበሌዎች፣በሲዳማ ክልል ማዕከላዊ ሲዳማ ዞን ውስጥ የሚገኘው የሎካ አባያ ወረዳ በእዚህ ልዩ መግለጫ የተሸፈኑ ናቸው፡፡

በተጨማሪም መነሻውን በ2015 ዓ.ም ማገባደጃ ላይ ያደረገውና መላውን የአማራ ክልል በሚባል ደረጃ ያካለለው ግጭት በእዚህ ልዩ መግለጫ የተሸፈነ ሲሆን አቅም በፈቀደ መጠን እና የአካባቢዎች የጸጥታ ሁኔታ ለምርመራ ምቹ በሆነበት ጊዜ በግጭቱ በዋናነት የተሸፈኑትን በህር ዳር ከተማ፣ ምዕራብ ጎጃም ዞን፣ አዊ ብሔረሰብ ልዩ ዞን፣ ሰሜን ጎጃም ዞን፣ ምስራቅ ጎጃም ዞንና ጎንደር ከተማ እና አካባቢው ውስጥ በሚገኙ በተለያዩ አካባቢዎች ላይ የምርመራ ስራ የተሰራ ሲሆን ኢሰመጉ እነዚህን አጠቃላይ የምርመራ ስራዎች ለማከናወን በመጀመሪያ ዙር ከሐምሌ 09 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ 20 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ስድስት (6) የምርመራ ቡድን በማዋቀርና በሁለተኛው ዙር በጥቅምት ወር 2016 ዓ.ም፣ ከህዳር 28 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 02 ቀን 2016 ዓ.ም እና ከጥር 29 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ የካቲት 01 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ስድስት (6) የምርመራ ቡድኖችን በማዋቀር የምርመራ ስራው ተከናውኗል፡፡

የመረጃ ምንጮችና የማሰረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

ይህ ልዩ ዘገባ የተዘጋጀው ኢሰመጉ የሰብዓዊ መብት የምርመራ ባለሙያዎች ባደረጉት ቃለመጠይቆች (ከተጎጂዎች፣ ምስክሮች፣ የመንግስት እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አመራሮች፣ እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ያካትታል)፣ የቡድን ውይይቶች፣ የመስክ ምልከታ ስራዎች፣ የመንግስት እንዲሁም መንግስታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ውይይቶች እና ከእነዚህ አካላት የተገኙ አስረጂ ሰነዶችን በመጠቀም መረጃዎችን ኢሰመጉ

አሰባስቧል፡፡ በተጨማሪም የኢሰመጉ የምርመራ ባለሙያዎች በተሰማሩባቸው አካባቢዎች ላይ ያደረጉትን ምልከታ እንደ ማስረጃነት ለመጠቀም ተሞክሯል፡፡

የምርመራ ቡድኑ በተጠቀሱት አካባቢዎች ተዘዋውሮ የሚች ቤተሰቦችን፣ በጥቃቱ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን፣ የዓይን ምስክሮችን፣ የመንግሥት ተቋማት የሥራ ኃላፊዎችንና ሌሎችም የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሞ ልዩ ልዩ መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን አሰባስቧል፡፡

የምርመራው ስራ ውስንነትና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ ያለው ውስን የሆነ የሰው ሀይል፣ ምርመራ ቁሳቁስ አቅምና እጥረት እንዲሁም በበርካታ አካባቢዎች በነበሩ የፀጥታ ችግሮች ምክንያት በተጠቀሱት ክልሎች ላይ ሊሸፈኑ የሚገባቸውን ተጨማሪ ቦታዎችን በጥልቀት ለመሸፈን ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ሌላው ምርመራ ስራው ላይ ያጋጠመው ውስንነት የመንግስት ተቋማት መረጃ ማጋራት ፈቃደኛ ያለመሆን ሲሆን ኢሰመጉ ለአንዳንድ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተደጋጋሚ የሆነ የመረጃ ጥያቄ ቢያቀርብም መረጃዎችን ለማግኘት አልተቻለም፡፡ በእዚህ ልዩ መግለጫ ላይ መረጃ ያልተገኘባቸውን የመንግስት ተቋማት ዝርዝር ከታች እንደየ አግባብነቱ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

የምርመራ ስራው ዋና ዋና ግኝቶች

አማራ ክልል፡

<u>በዋግምራ ልዩ ዞን እና ማዕ/ን/ዞን አለፋ ከተማና አካባቢው የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች</u>

ኢሰመጉ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማዕከላዊ ጎንደር ዞን አለፋ ወረዳ አለፋ ከተማ፡ ጎንደር ዙሪያ ማክሰኝት ከተማ ፤ ዋግህምር ልዩ ዞን ሰቆጣ ከተማ ፤ አበርገሊ እና አካባቢው ላይ የምርመራ ቡድን ከ 10/11/2015 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 20/11/2015 ዓ.ም ድረስ በማሰማራት በአካባቢው የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለመመርመር ችሏል፡ :

በማዕከላዊ ጎንደር ዞን አለፋ ወረዳ አለፋ ከተማ የአለፋ ወርዳ ፖሊስ ጣቢያ ግንቦት 19/2015 ዓ.ም በከባድ ውንብድና የተጠረጠሩ ተጠርጣሪዎችን ለማስለቀቅ ማንነታቸው ያልታወቁ የታጠቁ ቡድኖች በፖሊስ ጣቢያው ላይ ከለሊቱ 7፡ 30 አካባቢ የተጠርጣሪዎች ማቆያ ላይ ፈንጅ በመወርወር እና ከፖሊስ ጋር ከፍተኛ የተኩስ ልውውጥ በማድረግ 4 (አራት) በከፍተኛ ውንብድና የተጠረጠሩ ግለሰቦችን ማስለቀቅ የቻሉ ሲሆን በወቅቱም በፖሊስ ጣቢያው ተይዘው የነበሩ ተጠርጣሪዎች የነበሩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በተጣለው ፈንጅ እና በነበረው የተኩስ ልውውጥ ምክንያት 4 (አራት) ተጠርጣሪወች ማለትም

- 1ኛ.አቶ መሳፍንት በላይ
- 2ኛ.አቶ ሲሳይ ወርቁ

- 3ኛ.አቶ ዳምጣ አብች
- 4ኛ. አቶ መዝን ስጦታው

የተባሉ ግለሰቦች የተገደሉ ሲሆን በ 19 (አስራ ዘጠኝ) ተጠርጣሪዎች ላይ ደግሞ በ 2 (ሁለቱ) ሰዎች ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት እና በ17 (አስራ ሰባት) ሰዎች ላይ የአካል ጎዳት ደርሷል። የወረዳው ፖሊስም የተፈጸመውን ድርጊት በመዘርዘር ማስረጃ በደብዳቤ ቁጥር መ/ከ/ፀ/2015 በቀን ፀ/ፀ/2015 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ እና የማዕ/ጎ/ዞን ፖሊስ መማሪያም በደብዳቤ ቁጥር 0555/68/22 በቀን 20/ፀ/2015 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የሟቾችን ማንነት በመዘርዘር መረጃ አጋርቷል። እንዲሁም የፖሊስ ጣቢያው ሰራተኞች ኃላፊውን ጨምሮ 7 (ሰባት) ስራተኞች በቸልተኝነት እና የስራ ሃላፊነትን በአግባቡ አለመወጣት ወንጀል ተጠርጥረው እንደታሰሩ እና አሁን በዋስትና እንደተለቀቁ እና ምርመራ እየተጣራባቸው መሆኑን ኢሰመጉ በወቅቱ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል።

በአጠቃላይ አለፉ ፖሊስ ጣቢያ ላይ በደረሰው ጥቃት 4 (አራት) በፖሊስ ጣቢያው ተይዘው የነበሩ ተጠርጣሪዎች በተያዙበት በታጠቁ አካላት እንደተገደሉ እና 19 (አስራ ዘጠኝ) ሰዎች ላይ የአካል ጎዳት እንደደረሰ፣ ሁለቱ ላይ ከፍተኛ የአካል ጎዳት እንደደረሰ እና ጥቃት አድረሾችም እስካሁን እንዳልተያዙና ለህግ እንደልቀረቡ እንዲሁም ለተጎጅዎች ቤተሰብም ሆነ ለተጎጅ ዎች ምንም አይነት ካሳም እንዳልተሰጠ ኢሰመጉ ባደረገው ምርመራ ለመረዳት ችሏል።

በዋግምህራ ልዩ ዞን በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ተከስቶ በነበረው የትጥቅ ግጭት ጋር በተያያዘ በሰቆጣ እና አካባቢው ከአበርገሊ እና ፃግብጅ አካባቢ የተፈናቀሉ 67ሺ (ስልሳ ሰባት ሺ) ተፈናቃዮች የነበሩ ሲሆን ሃምሌ 29/2015 ዓ.ም የታጠቁ ቡድኖች (ኢሰመጉ በወቅቱ ያነጋገራቸው ሰዎች የህወሀት ታጣቂ ቡድኖች መሆናቸውን ገልጸዋል) ከተማዋን ለመያዝ ከመንግስት የጸጥታ ኃይሎች ጋር በነበረ ውጊያ ወለህ መጠለያ ካምፕ የነበሩ ተፈናቃዮች ካምፑን ጥለው ለመሸሽ በሚሞክሩበት ጊዜ አንድ ሰው እንደሞተ እና አንድ ሰው ከፍተኛ ጎዳት እንደደረሰበት በማይ ብሊት የሚገኙ ተፈናቃዮች ከሰጡት መረጃ ለመረዳት ተችሏል።

ነገር ግን የዞኑ አደጋ ስጋት መከላከል እና የምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ በወቅቱ ተፈናቃዮች ከመጠለያ ጣቢያ እንዲወጡ የተደረገ መሆኑን እና ምንም አይነት ጎዳት በካምፑ ውስጥ በነበሩ ሰዎች ላይ እንዳልደረሰ እና በአካባቢው የምርመራ ስራ እስከተሰራበት ጊዜ ድረስ በሰቆጣ ወረዳ፣ በአበርገሊ ወረዳ፣ በፃግብጅ ወረዳ፣ በዛታ ወረዳ፣ በዳሃና ወረዳና በአማደወርቅ ከተማ እና በሰቆጣ ከተማ ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ተያይዞ ተፈናቅለው የነበሩ እና በትጥቅ ግጭቱ የተነሳ ባለፈው ክረምት መሬታቸውን ማረስና መዝራት ያልቻሉ 253,555.00 (ሁለት መቶ ሀምሳ ሶስት ሺ አምስት መቶ ሀምሳ አምስት) ሰዎች የምግብ እርዳታ፣ የቤት ውስጥ ቁሣቁሥ ድጋፍና የቤት ጥገና የሚፈልጉ ወገኖች በከፍተኛ ችግር ውስጥ የሚገኙ መሆናቸውን በደብዳቤ ቁጥር ዞአመምም/06-5/03/15 በቀን 14/ፀ/2015 ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጡት መረጃ ገልጸዋል።

ኢሰመጉ በማይብሊት ሰቆጣ ከተማ አካባቢ የሚገኙ ተፈናቃዮችን ቦታው ድረስ በመገኘት የነበኘን ቢሆንም በወቅቱም ጉዳት ደረሰባቸው የተባሉት ተፈናቃዮች ቤተሰቦች በአበርገሊ ወረዳ የሚገኙ ሲሆን ምርመራ በተደረገበት ወቅት አበረገሊ ለመንቀሳቀስ መንገዱ በታጠቁ ሀይሎች በመከልከሉ እና መንገድ በመዘጋቱ ወደ ቦታው በመሄድ ለማጣራት አልተቻለም። ነገር ግን ኢሰመጉ ከአይን እማኞች ባደረገው ማጣራት በአጠቃላይ በዋግምህራ ልዩ ዞን ወለህ ማቆያ ካምፕ ላይ እያሉ የደረሰ ጉዳት እንደ ሌለ ነገር ግን ተፈናቃዮች በሸሽት ላይ እያሉ አንድ ሰው እንደተገደለ እና አንድ ሰው ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰባቸው ለመረዳት ተችሏል።

ምስራቅ ጎጃም፣ ምዕራብ ጎጃም፣ በደቡብ ጎንደር ዞኖች፡

መነሻ ታሪክ ፤

መንግስት በ28/7/2915 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት እና የግዛት አንድነትን ለመጠበቅ አንድ የተማከለ ጠንካራ ሰራዊት ለመገንባት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በሁሉም ክልሎች የሚገኙ የልዩ ኃይል አባላት እንደየምርጫቸው በመከላከያ፣በፌደራል ፖሊስና በክልል ፖሊስ አባልነት መካተት እንደሚችሉ መግለጹን ተከትሎ በመንግስት እየተወሰደ ከነበረው የልዩ ኃይል አባላትን መልሶ የማደራጀት እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የአፈጻጸም ተገቢነት ላይ የተለያየ ግንዛቤ በመኖሩ ምክንያት በወቅቱ በአማራ ክልላዊ መንግስት በተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች ይህንን ድርጊት በመቃወም ሰልፎች የተደረጉ ሲሆን እነዚህንም ሰልፎች ተከትሎ መንገዶች ተዘግተዋል፣ ትራንስፖርት ተቋርጧል እንዲሁም የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተፈጽመዋል።

ይህንን ክስተት ተከትሎ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ(ኢሰመጉ) በአማራ ክልል በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች ማለትም በእናርጅ እናውጋ ወረዳ በደብረወርቅ ከተማ፣ በደጀን፣ በደንበጫና በፍኖተሰላም ከተሞች ላይ ከሚያዚያ 2015 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 2015 ዓ.ም ከክልል ልዩ ሃይል አባላት መልሶ የማደራጀት እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ በተፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች የተፈጠሩትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ከሚያዚያ 9/2015 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 16/2015 ዓ.ም እንዲሁም በደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን እብናት ከተማ እና በምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን መርዓዊ ከተማ የተፈፀመውን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ከሃምሌ 10/11/2015 እስከ 17/11/2015 ዓ.ም በመመርመር ግኝቶችን እንደሚከተለው አቅርቧል ።

1. **ደብረወርቅ ከተማ**

በምስራቅ ጎጃም ዞን እናርጅ እና እናዉጋ ወረዳ እና በከተማዉ መስተዳደር ደብረወርቅ ከተማ ሰኔ 20/2015 ዓ.ም የመንግስት የጸጥታ አባላት እንዳያልፉ መንገድ ዘግታችኋል በሚል ምክንያት በርካታ ወጣቶች በፖሊስ ታስረዉ የነበረ ሲሆን ለ2 ቀናትም ያህል ምግብ እንዳይበሉ እና ቤተሰብ፣ ዘመድና ጓደኛም እንዳይጠይቃቸዉ በመደረጉ ምክንያት ይህን ለመቃወም በወጡ የከተማው ማህበረሰብ ላይ ፖሊስ በወሰደው ተመጣጣኝ ያልሆነ የሀይል እርምጃ 1 ሴትና 1 ወንድ በድምሩ 2 ሰዎች መገደላቸውን እንዲሁም በ እናርጅ እና እናዉጋ ወረዳ ጎል ቀበሌ 2 አርሶ አደሮች ከመንግስት የጸጥታ አካላት በተተኮሰ ጥይት የተገደሉ ሲሆን 2ቱም ወንድ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል።

በተጨማሪም የምስራቅ ጎጃም ዞን ጤና መምሪያ የደብረወርቅ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል በደብዳቤ ቁጥር ፈ/ህ/ተ/0051 በቀን 10/11/2015 ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጡት መረጃ መሰረት በወቅቱ በነበረው ግጭት ምክንያት **አቶ እያየሁ ቸኮል** የተባለ የ43 ዓመት ግለሰብ ህምሌ 01/2015 ዓ.ም ሁለት ቦታ ደረቱ ላይ፣ 3 ቦታ ሆዱ አካባቢ እና ከእምብርቱ በታችም በጥይት ተመትቶ መሞቱን ማወቅ የተቻለ ሲሆን በተመሳሳይ **አቶ ደሴ ሰለሞን** የተለያዩ የሰውነት አካሉ ላይ በጥይት ተመትቶ ህይወቱ ማለፉን ከምስራቅ ጎጃም ዞን ጤና መምሪያ የደብረወርቅ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል በደብዳቤ ቁጥር ፈ/ህ/ተ/0050 በቀን 10/11/2015ዓ.ም በተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል::

በደብረወርቅ ከተማ ከተገደሉ ሰዎች መካከል በምስል፡

	
ስም፡ እውነቱ ንጉሴ	ስም፡ ደሴ ሰለሞን
ዕድሜ፡40	ዕድሜ፡34

2. ደጅን ከተማ

በምስራቅ ጎጃም ዞን ደጅን ከተማ በመነሻ ታሪኩ ላይ የተገለጸውን የመንግስት ውሳኔ ማህበረሰቡ በመቃወም የካቲት 29 - ሚያዝያ 03/2015 ዓ.ም ሰላማዊ ሰልፍ ያደረገ ሲሆን የመንግስት የጸጥታ ሃይሎች ሚያዚያ 02/2015 ዓ.ም በወሰዱት ተመጣጣኝ ያልሆነ የሀይል እርምጃ 2 ሰዎች የሞቱ ሲሆን 2 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት መድረሱን እንዲሁም ሚያዝያ 23/2015 ዓ.ም ፲፩ ሰዎች ከህግ አግባብ ውጪ ለረጅም ጊዜ ፍ/ቤት ሳይቀርቡ ቆይተው ከ14 ቀናት በኋላ በዋስትና መፈታታቸዉን ታስረው ከነበሩ ግለሰቦች እና ከተጎጅ ቤተሰቦች ለማወቅ ተችሏል:: በምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር የደጅን የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል በደብዳቤ ቁጥር ሜድ-582/ለደ-ነ/15 በቀን 12/11/2015ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጡት መረጃ መሰረት 7 ሰዎች ጉዳት ደርሶባቸው ወደ ሆስፒታል የገቡ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ነ ሰው መሞቱን እና 6 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት መድረሱን ለማወቅ ተችሏል::

በደጅን ከተማ ከተገደሉ ሰዎች መካከል በምስል፡



ስም፡ አዲሱ አለወንድ ስራው

ዕድሜ፡ 18

3. **ደምበጫ**

በምዕራብ ጎጃም ዞን ደምበጫ ከተማ ሰኔ 4 ቀን 2015 ዓ.ም የመንግስት የፀጥታ ሃይሎች ህግ ለማስከበርና "በአካባቢው የሚንቀሳቀሰውን የታጠቀ ኃይልን ትጥቅ ለማስፈታት" በሚል ምክንያት በተፈጠረዉ አለመግባባት በመንግስት የጸጥታ ሃይሎች በተወሰደ ተመጣጣኝ ያልሆነ የሀይል እርምጃ ከ4 በላይ ሰዎች የሞቱ ሲሆን 16 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት የደረሰባቸዉ መሆኑን ከተጎጅ ቤተሰቦች እና ከምስክሮች ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደንበጫ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል በደብዳቤ ቁጥር ደም/መ/ደ/ሆ/15/15 በቀን 1/11/2015ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጡት መረጃ መሰረት በወቅቱ በነበረው ግጭት ምክንያት 18 ሰዎች ጉዳት ደርሶባቸው ወደ ሆስፒታላቸው የገቡ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 2 ሰዎች መሞታቸውን ለማወቅ ተችሏል::

በደንበጫ ከተማ ከተገደሉ ሰዎች መካከል በምስል፡



ስም፡ መላኩ ሰማ ፈንታ

ዕድሜ፡ 23

4. **ፍኖተ ሰላም**

በምዕራብ ጎጃም ዞን ፍኖተ ሰላም ከተማ በመነሻ ታሪኩ ላይ የተገለጸውን የመንግስት ውሳኔ ማህበረሰቡ በመቃወም ሰኔ 05/2015 ዓ.ም ባደረጉት ሰላማዊ ሰልፍ ከመንግስት የጸጥታ ሃይሎች በተተኮሰ ጥይት 2 ሰዎች የሞቱ ሲሆን ከ 7 በላይ የሚሆኑት ደግሞ አካል ጉዳት የደረሰባቸዉ መሆኑን ከአቤቱታ አቅራቢዎች እና ከምስክሮች ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በምዕራብ ጎጃም ዞን ፍኖተሰላም የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ለኢሰመጉ በሰጡት መረጃ መሰረት በወቅቱ በነበረው ግጭት 9 ሰዎች ጉዳት ደርሶባቸው ወደሆስፒታላቸው የገቡ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የ 1 ሰው ህይወት ማለፉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- *ከታች የተቀመጠዉ ሰንጠረዥም ከላይ ለተጠቀሱት የመብት ጥሰት ማሳያዎች በጥቂቱ ሰፅል የሚሰጥ በመሆኑ እንደሚከተለዉ ተዘጋጅቷል፡፡*

ተ.ቁ	ስም	ጾታ	ዕድሜ	ቦታ	የመብት ጥሰት የተፈጸመበት ወረዳ	ቀን	የመብት ጥሰቱ ዓይነት
1.	ምንይልክ መሌ ከበደ	ወንድ	60	ምስ/ጎጃም	እናርጅ/እናውጋ ጎል ቀበሌ	20/10/2015 ዓ.ም	ግድያ
2.	እዉነቱ ንጉሴ	ወንድ	40	ምስ/ጎጃም	እናርጅ/እናዉጋ ጎል ቀበሌ	20/10/2015 ዓ.ም	ግድያ
3.	ደሴ ሰለሞን አይቸህ	ወንድ	34	ምስ/ጎጃም	ደ/ወርቅ ከተማ	-------	ግድያ
4.	ሀረግ አሰፋ	ሴት	25	ምስ/ጎጃም	ደ/ወርቅ ከተማ	20/10/2015 ዓ.ም	ግድያ
5.	እያየሁ ቸኮል	ወንድ	43	ምስ/ጎጃም	ደ/ወርቅ ከተማ	01/11/2015ዓ.ም	ግድያ
6.	ሀብታሙ የሸዋስ	ወንድ	24	ምስ/ጎጃም	ደ/ወርቅ ከተማ	20/10/2015 ዓ.ም	ህገ ወጥ እስር
7.	ምሬ ገሰሰ ዘለቀ	ወንድ	26	ምስ/ጎጃም	ደ/ወርቅ ከተማ	20/10/2015 ዓ.ም	ህገ ወጥ እስር
8.	ጸሃይነህ ባየ	ወንድ	28	ምስ/ጎጃም	ደ/ወርቅ ከተማ	20/10/2015 ዓ.ም	ህገ ወጥ እስር
9.	ሙሉቀን ወነድምነህ	ወንድ	34	ምስ/ጎጃም	ደ/ወርቅ ከተማ	20/10/2015 ዓ.ም	ህገ ወጥ እስር
10.	ደቢያዉ አንዳርጌ	ወንድ	34	ምስ/ጎጃም	ደ/ወርቅ ከተማ	20/10/2015 ዓ.ም	ህገ ወጥ እስር

11.	አዲሱ አለወንድ ስራዉ	ወንድ	18	ምስ/ጎጃም	ደጀን	02/08/2015 ዓ.ም	ግድያ
12.	ታሪኩ ስለሸ አበበ	ወንድ	25	ምስ/ጎጃም	ደጀን	02/08/2015 ዓ.ም	ጀርባዉን በጥይት ተመትቶ ከፍተኛ የአካል ጉዳት የደረሰበት
13.	ተሻገር ታምሩ ታደሰ	ወንድ	24	ምስ/ጎጃም	ደጀን	02/08/2015	የአካል ጉዳት
14.	ሃኑር ጋሹ ኡስማን	ወንድ	28	ምስ/ጎጃም	ደጀን	02/08/2015	የአካል ጉዳት
15.	ተመስገንጣሰዉ ጌታቸዉ	ወንድ	25	ምስ/ጎጃም	ደጀን	02/08/2015	የአካል ጉዳት
16.	አማረ በለጠ እዉነቱ	ወንድ	21	ምስ/ጎጃም	ደጀን	02/08/2015	የአካል ጉዳት
17.	አዲሱ አበበ ስራዉ	ወንድ	25	ምስ/ጎጃም	ደጀን	02/08/2015	የአካል ጉዳት
18.	ተመስገን ብሩ ጓዴ	ወንድ	32	ምስ/ጎጃም	ደጀን	02/08/2015	የአካል ጉዳት
19.	እንደግ ሞሱ	ወንድ	34	ምስ/ጎጃም	ደጀን	23/08/2015 ዓ.ም	ህግ ወጥ እሰር
20.	አገሩ ጓንቼ	ወንድ	26	ምስ/ጎጃም	ደጀን	23/08/2015 ዓ.ም	ህገ ወጥ እሰር
21.	ስለሸ አለጎን	ወንድ	28	ምስ/ጎጃም	ደጀን	23/08/2015 ዓ.ም	ህገ ወጥ እሰር
22.	አባትነህ ገዳሙ	ወንድ	28	ምስ/ጎጃም	ደጀን	23/08/2015 ዓ.ም	ህገ ወጥ እሰር
23.	እንግዳ ደምሌ	ወንድ	29	ምስ/ጎጃም	ደጀን	23/08/2015 ዓ.ም	ህገ ወጥ እሰር
24.	አያሌዉ አሰግድ	ወንድ	38	ምስ/ጎጃም	ደጀን	23/08/2015 ዓ.ም	ህገ ወጥ እሰር
25.	መኩሪያዉ	ወንድ	38	ምስ/ጎጃም	ደጀን	23/08/2015 ዓ.ም	ህገ ወጥ እሰር
26	ባሴ	ወንድ	36	ምስ/ጎጃም	ደጀን	23/08/2015 ዓ.ም	ህገ ወጥ እሰር

27.	ዘላለም አበዉ	ወንድ	27	ምስ/ጎጃም	ደጀን	23/08/2015 ዓ.ም	ህገ ወጥ እሰር
28	ካሳዬ ጌታቸዉ	ወንድ	29	ምስ/ጎጃም	ደጀን	23/08/2015 ዓ.ም	ህገ ወጥ እሰር
29	አበባዉ መረዋ	ወንድ	60	ምስ/ጎጃም	ደጀን	23/08/2015 ዓ.ም	ህገ ወጥ እሰር
30.	መላኩ ሰማ ፈንታ	ወንድ	23	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	ህገ ወጥ እሰር
31.	ሁኔ ማኔ አወቀ	ወንድ	45	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	ህገ ወጥ እሰር
32.	ይነበብ መለሰ	ወንድ	30	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	ህገ ወጥ እሰር
33.	ይናገር ጥላሁን አወቀ	ወንድ	23	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	የአካል ጉዳት
34	ዘላለም ንብረት	ወንድ	24	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	አካል ጉዳት
35.	ተመስገን ገደፋዉ	ወንድ	20	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	አካል ጉዳት
36	ጣሳቸዉ እስካሁን	ወንድ	30	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	አካል ጉዳት
37.	ይከበር ዳኛዉ	ወንድ	32	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	አካል ጉዳት
38	ሃብታሙ ግዛቸዉ	ወንድ	27	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	አካል ጉዳት
39	ስሜነህ ከፋለ	ወንድ	30	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	አካል ጉዳት
40	መልሰዉ ተመስገን	ወንድ	38	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	አካል ጉዳት
41.	ዘገዬ ሃይሉ	ወንድ	30	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	የአካል ጉዳት
42.	ሙሉዬ ጸጋዉ	ወንድ	25	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	የአካል ጉዳት
43	አሸብር አባትይሁን	ወንድ	28	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	የአካል ጉዳት
44	ይላቸዉ አባትይሁን	ወንድ	35	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	የአካል ጉዳት
45	አበባዉ አጥናፉ	ወንድ	35	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	የአካል ጉዳት
46	ምስጋናዉ ጌትነት	ወንድ	30	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	የአካል ጉዳት
47	አዛናዉ አየሁ	ወንድ	35	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	የአካል ጉዳት
48	አማረ አዲስ	ወንድ	35	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	የአካል ጉዳት
49	ሃብታሙ በላይ	ወንድ	21	ምዕ/ጎጃ	ደምበጫ	04/10/2015	የአካል ጉዳት
50	አያኑ አማኑ አድማስ	ወንድ	20	ምዕ/ጎጃ	ፍኖተ ሰላም	05/10/2015	ግድያ
51.	የኔአካል አለሙ ሰንደቅ	ወንድ	21	ምዕ/ጎጃ	ፍኖተ ሰላም	05/10/2015	የአካል ጉዳት
52.	ሙሉቀን ጥላሁን	ወንድ	25	ምዕ/ጎጃ	ፍኖተ ሰላም	05/10/2015	የአካል ጉዳት

53	ገናናዉ መንግስቱ ባለዉ	ወንድ	29	ምዕ/ጎጃ	ፍኖተ ሰላም	05/10/2015	የአካል ጉዳት
54	አንሙት አማኑ ዋሲሁን	ወንድ	23	ምዕ/ጎጃ	ፍኖተ ሰላም	05/10/2015	የአካል ጉዳት
55	የቻለ ደመቀ አድማስ	ወንድ	22	ምዕ/ጎጃ	ፍኖተ ሰላም	05/10/2015	የአካል ጉዳት
56	አንተነህ መኩሪያዉ አለማየሁ	ወንድ	28	ምዕ/ጎጃ	ፍኖተ ሰላም	05/10/2015	የአካል ጉዳት
57	ሽባባዉ ንብረት ወርቁ	ወንድ	31	ምዕ/ጎጃ	ፍኖተ ሰላም	05/10/2015	የአካል ጉዳት
58	አስረስ አንዷለም ወለላዋ	ሴት	22	ምዕ/ጎጃ	ፍኖተ ሰላም	05/10/2015	የአካል ጉዳት

በደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር እብናት ከተማ

በደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን በመነሻ ታሪኩ ላይ የተገለጸውን የመንግስት ውሳኔ ለማስፈጸም በወሰደው እርምጃ በቀን 20/10/2015 ዓ.ም ከማዕከላዊ ጎንደር ከተማ ተነስተው ወደ እብናት ከተማ የሄዱ የታጠቁ አካላት /በማህበረሰቡ ፋኖ ተብለው በሚጠሩት ኃይሎች/ ከመንግስት የፀጥታ ኃይል ጋር እብናት ከተማ ውስጥ በተነሳ የተኩስ ልውውጥ በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ ከፍተኛ የሆነ ድንጋጤን ፈጥሮ የነበር ሲሆን በእነዚህ የታጠቁ አካላት የመሳሪያ ተኩስ ልውውጥ አስመልክቶ በሰዎች ላይ ግድያና የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡

በዚህም 4 ሰው የሞተ ሲሆን ከ2 በላይ በሚሆኑ ሰዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የአካል ጉዳትና የስነ ልቦና ጉዳት መድረሱን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን የተኩስ ልውውጡ በ21/10/2015ዓ.ም ቀጥሎ የነበረ በመሆኑና በእዕለቱም በእብናት ከተማ የማርያም ከብረ በአልን ለማክበር ብዛት ያለው የማህበረሰብ ክፍል በማሪያም ቤተክርስትያን የተገኘበት አጋጣሚ በመሆኑና የተኩስ ልውውጡም የተፈጠረው በዚያው ቦታ በመሆኑ ድርጊቱ በሰዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የአካል ጉዳት እንዲደርስ ምክንያት ሆኗል፡፡

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሠላምና ደህንነት መምሪያ የእብናት ከተማ አስተዳደር ሠላምና ደህንነት ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር እብከ/አስ/ሠ/ደ/104/2015 ዓ.ም በቀን11/11/2015 ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ መሰረት በቀን 20/10/2015 ዓ.ም በእብናት ከተማ በተፈጠረው የጸጥታ ችግር 4 ሰዎች የሞቱ ሲሆን በ2 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት መድረሱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ተ.ቁ	ስም	ጾታ	ቦታ	ቀን	የደረሰ ጉዳት
1	ሲሳይ ገበየሁ	ወንድ	እብናት ከተማ	20/10/2015 ዓ.ም	ግድያ

2	እንደሰው ካሴ	ወንድ	እብናት ከተማ	20/10/2015 ዓ.ም	ግድያ
3	አበበው ተስፋዬ	ወንድ	እብናት ከተማ	20/10/2015 ዓ.ም	የአካል ጉዳት
4	ታምሩ	ወንድ	እብናት ከተማ	20/10/2015 ዓ.ም	የአካል ጉዳት

በእዚሁ አካባቢ የሚገኙ ነገር ግን ስማቸው ሊገኝ ያልቻሉ ሰዎች ሰም ዝርዝር ከእዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡ ፡

1	-	ወንድ	እብናት ከተማ	20/10/2015 ዓ.ም	ግድያ
2	-	ወንድ	እብናት ከተማ	20/10/2015 ዓ.ም	ግድያ

በምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን መርዓዊ ከተማ

በመነሻ ታሪኩ ላይ የተገለጸውን የመንግስት ውሳኔ በመርዓዊ ከተማ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታን ፈጥሮ የነበረ ሲሆን ይህንን አስመልክቶም ሚያዚያ 2/8/2015 ዓ.ም በመርዓዊ ከተማ ነዋሪዎችና በመንግስት የጸጥታ አካላት መካከል ከፍተኛ የሆነ አለመግባባት ተከስቶ ህፃናትን ጨምሮ በርካታ ሰዎችተገድለዋል፣ እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ የአካል ጉዳትም ደርሷል፡፡

በእለቱ የመንግስት የጸጥታ አካላት ከመርዓዊ ከተማ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ እንቅስቃሴ በሚያደርጉበት ጊዜ አንዳንድ የአካባቢው ወጣት መንገድ በመዝጋቱ ምክንያት መደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት ተስተጓጉሎ የነበረ ሲሆን በእዚህም ምክንያት በመንግስት የጸጥታ አካላት እና መንገድ በዘጉ ወጣቶች መካከል ከፍተኛ የሆነ ግጭትን የተፈጠረ ሲሆን በዚህም ምክንያት በተተኮሰ ጥይት 3 ሰዎች የሞቱ ሲሆን በ11 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳትና ስነልቦና ጫና እንደደረሰባቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

በተጨማሪም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምዕራብ ጎጃም መስተዳድር ዞን የመርዓዊ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር መ/ከ/አስ/36/መለ-1 በቀን14/11/2015ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጡት መረጃ መሰረት በመርዓዊ ከተማና አጎራባች ወረዳ ከላይ በተገለጸው ግጭት ምክንያት 3 ሰዎች መሞታቸውን፣ 12 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት መድረሱን እና 2 የንብረት ውድመት መድረሱን ገልጿል፡፡

ተ.ቁ	ስም	ጾታ	አድራሻ	ቀን	የደረሰ ጉዳት
1	አባተ መስፍን አበረ	ወንድ	መርዓዊ	2/8/2015 ዓ.ም	ግድያ
2	ይታያል ደሳለኝ አይናለም	ወንድ	ሰ/ሜጫ	2/8/2015 ዓ.ም	ግድያ
3	አምላኬ እንደሻው አንዱዓለም	ወንድ	ሰ/ሜጫ	2/8/2015 ዓ.ም	ግድያ
4	ማመይ ማምዋ	ሴት	ሰ/ሜጫ	2/8/2015 ዓ.ም	የአካል ጉዳት
5	መንግስቱ ዳርጌ	ወንድ	ሰ/ሜጫ	2/8/2015 ዓ.ም	የአካል ጉዳት
6	የበላይ አዳሙ	ወንድ	ሰ/ሜጫ	2/8/2015 ዓ.ም	የአካል ጉዳት
7	እንኳሆነ አጣናው	ወንድ	መርዓዊ	2/8/2015 ዓ.ም	የአካል ጉዳት
8	ዘመኑ ጫኔ ብርሌ	ወንድ	መርዓዊ	2/8/2015 ዓ.ም	የአካል ጉዳት
9	አለቤ መጣልኝ	ወንድ	ሰ/ሜጫ	2/8/2015 ዓ.ም	የአካል ጉዳት
10	የጸዳው ሁልጊዜ ተመስገን	ወንድ	መርዓዊ	2/8/2015 ዓ.ም	የአካል ጉዳት
11	ልይህ አሰማ	ወንድ	ሰ/ሜጫ	2/8/2015 ዓ.ም	የአካል ጉዳት
12	ሳሙኤል አለፈ ካሴ	ወንድ	መርዓዊ	2/8/2015 ዓ.ም	የአካል ጉዳት
13	ከሳሁን ልየው	ወንድ	ሰ/ሜጫ	2/8/2015 ዓ.ም	የአካል ጉዳት
14	ታምራት ተረፈ	ወንድ	ባ/ዳር ዙሪያ	2/8/2015 ዓ.ም	የአካል ጉዳት
15	ማንደፍሮ ሙጨ	ወንድ	ሰ/ሜጫ	2/8/2015 ዓ.ም	የአካል ጉዳት

መነሻ ታሪክ 2

ከእዚህ በታች በምዕራብ ጎጃም ዞን ደቡብ አቸፈር ወረዳ እና መሸንቲ ከተማ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መነሻ ታሪካቸው የሆነው በአማራ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ አርሶ አደሮች ወቅቱን የጠበቀና በቂ የሆነ የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ባለማግኘታቸው የማዳበሪያ አቅርቦት እንዲደረግላቸው በሰላማዊ ሰልፍ የሚመለከተውን የመንግስት አካል የጠየቁ ሲሆን የመንግስት የፀጥታ አካላት በወሰዱት ተመጣጣኝ ያልሆነ የሀይል እርምጃ ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ደርሷል፡፡

ኢሰመጉ በእነዚህ አካባቢዎች የምርመራ ቡድኖችን በማሰማራት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ምርመራ ያካሄደ ሲሆን ግኝቶቹም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በምዕራብ ጎጃም ዞን ደቡብ አቸፈር ወረዳ

በደቡብ አቸፈር ወረዳ አንካሻ ሙንገት ቀበሌ ልዩ ቦታው ሳንቅ በተባለ አካባቢ በቀን 2/10/2015 ዓ.ም ለአንካሻ ሙንገት ቀበሌ አርሶ አደሮች በመንግስት ተወካዮች አማካኝነት የአፈር ማዳበሪያ ሲሰራጭ ከቆየ በኋላ ከቀኑ 10፡00

ሰዓት አካባቢ የአፈር ማዳበሪያውን ሲያሰራጩ የነበሩት የመንግስት ተወካዮች በእለቱ ለማሰራጨት በእቅድ ደረጃ የያዙትን ያህል ማሰራጨት እንደቻሉ እና ቀሪውን በሚቀጥሉት ቀናት ለማሰራጨት እቅድ መያዛቸውን በእለቱ ማዳበሪያ ለመውሰድ ሲጠባበቅ የነበረውን አርሶ አደር ለማግባባት በመሞከር በእለቱ የነበረውን የማዳበሪያ ስርጭት ያቆሙ ሲሆን አርሶ አደሩም የማዳበሪያ ስርጭቱ በእለቱ የሚሰጣቸው ካልሆነ በሚቀጥሉት ቀናቶች የመዳበሪያ አቅርቦት ላይኖር ይችላል የሚል ስጋት ያለባቸው በመሆኑ በእለቱ እንዲሰጣቸው በመጠየቃቸው ለአርሶ አደሩ በሚያሰራጩ የመንግስት ተወካዮችና ማዳበሪያውን ለመውሰድ በሚጠባበቁ አርሶ አደሮች መካከል ከፍተኛ የሆነ አለመግባባት የተፈጠረ ሲሆን ይህንን አለመግባባት ተከትሎ በወቅቱ ከአርሶ አደሩ በኩል የተውጣጡ ወጣቶች ማዳበሪያውን ሲያሰራጩ የነበሩ የመንግስት ተወካዮች እንዳይወጡ የአካባቢውን መንገድ በድንጋይ ለመዝጋት ሙከራ ሲያደረጉ መንግስት የፀጥታ አካል ወደ ቦታው በመድረስ አርሶ አደሩ ላይ ተኩስ በመክፈት 2 አርሶ አደሮች ሲገደሉ 4 አርሶ አደሮች ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የአካል ጉዳት እንደደረሰባቸው እና አንድ የመንግስት መኪና በወጣቶች ሙሉ በሙሉ መቃጠሉን ኢሰመጉ ከአካባቢው ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለማወቅ ችሏል።

በተፈጠረው ግጭት ምክንያት የተገደሉ ሰዎች ምስል፡

	
ስም፡ ደርበ አቤ	ስም፡ ቄስ ወለላው ታደለ እንየው
ዕድሜ፡ 49	ዕድሜ፡ 48

መሸንቲ ከተማ

በመሸንቲ ከተማ ግንቦት 29 ቀን 2015 ዓ.ም ከአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ጋር በተያያዘ ማዳበሪያ ለመከፋፈል በቦታው የተገኙ የአካባቢው ወጣቶች የህብረት ስራ ዩኒየን በሚጠብቁ የመንግስት የጸጥታ አባላት ጋር በነበራቸው አለመግባባት የጸጥታ ኃይሎቹ በወሰዱባቸው ተመጣጣኝ ያልሆነ የሃይል እርምጃ የ2 ሰዎች ህይወት ማለፉን እና ከ6 ሰዎች በላይ የአካል ጉዳት መድረሱን እንዲሁም በ 1 መኪና ላይ ቃጠሎ መድረሱን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በባህርዳር ከተማ አስተዳደር የመሸንቲ ንዑስ ማዘጋጃ አስተዳደር ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር መሸ/30/ማዘ/05/15 በቀን 14/11/2015ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ እና ኢሰመጉ ባከናወነው የምርመራ ስራ ለማወቅ ተችሏል።

ተ.ቁ	ስም	ጾታ	ቦታ	ቀን	የደረሰ ጉዳት
1	ካሳሁን ጨቅሌ አድማሴ	ወንድ	ባህርዳር ዙሪያ ኢሳላ ጉላ ጉልማ ቀበሌ	29/09/2015 ዓ.ም	ግድያ
2	ስማቸው አንተነህ አጥናፉ	ወንድ	ባህርዳር ዙሪያ ወርቀምሳ ቀበሌ	29/09/2015 ዓ.ም	ግድያ

በአማራ ክልል በተከሰተው ግጭት ምክንያት የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፡

የግጭቱ መነሻ ምክንያት፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ክልሎች ውስጥ ያለውን የልዩ ኃይል አደረጃጀት አስመልክቶ መንግስት በ28/07/2015 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ መሰረት የኢትዮጵያን ሉአላዊነት እና የግዛት አንድነት ለመጠበቅ የሚያስችል አንድ ጠንካራ የተማከለ ሰራዊት ለመገንባት አቅጣጫ በማስቀመጥ በሁሉም ክልሎች የሚገኙ የልዩ ኃይል አባላት እንደየምርጫቸው በመከላከያ፣ በፌደራል ፖሊስና በክልል ፖሊስ አባልነት መካተት እንደሚችሉ መግለጹንና ይህንን የድርጊት አፈጻጸም ተከትሎ በአማራ ክልል ተቃውሞዎች ተነስተው እንደነበረ ይታወሳል፡፡

ይህንንም ተከትሎ በክልሉ በሚንቀሳቀሱ የታጠቁ አካላት (በአካባቢው ነዋሪ ፋኖ ተብለው የሚጠሩ) እና በመንግስት የጸጥታ አካላት መካከል ግጭት የተነሳ ሲሆን በጊዜ ሂደት ይህ ግጭት መላውን የአማራ ክልል በሚባል ደረጃ ሊያካልል ችሏል፡፡

በግጭቱ የተሸፈኑ አካባቢዎች እና የደረሱ የመብት ጥሰቶች፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተነሳው ግጭት በተለያዩ የጊዜ ምዕራፎች ውስጥ ሙሉ ክልሉን ያደረሰ ነው ሊባል የሚቻል ሲሆን ግጭቱ የነበረባቸው አካባቢዎች እና የግጭቱ መጠን ግን ከቦታ ቦታ የሚለያይ ነው፡፡ ከሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች አንጻር ይህንን ግጭት ስንመለከተው ግጭቱ በተደረገባቸው የክልሉ አካባቢዎች ውስጥ በሁሉም በሚባል ደረጃ የተለያየ መጠን እና ስፋት ያላቸው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተፈጽመዋል፡፡

ኢሰመጉ ባደረጋቸው የክትትል እና የምርመራ ስራዎች መሰረት ይህ ግጭት ሙሉ የአማራ ክልልን በሚባል ደረጃ የሸፈነ ሲሆን በዋናነት በጎጃም አካባቢዎች ደጋዳሞት፣ መርዓዊ ፣ ቋሪት፣ ቡሬ ዙሪያ ወረዳ ቁጭ ቀበሌ፣ ደንበጫ፣ ፍኖተሰላም አማኑኤል፣ ደብረ ማርቆስ፣ መርጦለማሪያም፣ አዴት፣ ባህርዳር ከተማና ዙሪያ ወረዳ፣ ዳንግላ፣ ዱርቤቴ፣ አዲስ ቅዳም፣ ቲሊሊ፣ ቢቸና፣ ደብረ ወርቅ፣ ግንደ ወይን፣ አዋበል፣ ጂጋ እና ሰከላ ወረዳዎች፤ ደቡብ ጎንደር ዞን ላይ ጋይንት፣ ክምር ድንጋይ፣ እስቴ፣ እብናት፣ ደብረ ታቦር ወረዳዎች፤ ማዕከላዊ ጎንደር ዞን በለሳ፣ ደምቢያ እና ጨጊት፣ ዳባት፣ አላፋ ጣቁሳ ወረዳዎች፤ ደቡብ ወሎ ዞን መካነ ሰላም፣ ወግዲ፣ ወረኢሉ፣ ጃማ፣ አምባሰል፣ ኩታበር፣ ውጫሌ፣

ወረባቦ እና ድላንታ ወረዳዎች፤ ሰሜን ወሎ ዞን ኡርጌሳ፣ ባሶሚሌ፣ መርሳ፣ ላሊበላ፣ ወልድያ ዙሪያ፣ ቆቦ፣ ወግዲ፣ መካነ ሰላም፣ አማራ ሳይንት ወረዳዎች፤ ሰሜን ሸዋ ዞን አፍራታ ግድም፣ አንጾኪያ ገምዛ፣ ቀወት፣ ጣርማበር፣ ጌራ ምድር፣ ላሎ ምድር፣ መዘዞ፣ ባሶና ዎራና፣ ደብረ ብርሀን ከተማ፣ ሞረትና ጅሩ፣ እንሳሮ፣ መራቤቴ፣ አጎላላና ጣራ፣ ሀገረማሪያም፣ ምንጃር ሸንኮራ፣ አንኮበር እና የተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ በተደጋጋሚ ግጭቶች ያሉና አንዳንድ ጊዜ ሰላም የሚሆንባቸው ሲሆን በዘለቂነት ግን ከግጭት ነጻ ሊሆኑ ያልቻሉ ቦታዎች ናቸው፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች ላይ ከፍተኛ የሚባል የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በነዋሪዎች እና ንብረቶች ላይ አስከትሏል፡፡

በአማራ ክልል የተነሳውን ግጭት ተከትሎ በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች ላይ በመንግስት የጸጥታ አካላት እንዲሁም በታጠቁ ቡድኖች በተፈጸሙ ጥቃቶች ምክንያት በሰዎች ላይ ግድያ ተፈጽሟል፡፡ በእዚህ ግጭት ምክንያት በመንግስት የጸጥታ አካላት የታጣቂ ቡድን አባላት ናችሁ፣ የታጣቂ ቡድኑን ትደግፋላችሁ፣ ትደብቃላችሁ፣ የታጣቂ ቡድኑን ትቀላቀላላችሁ በሚል እና በሌሎች ምክንያቶች በርካታ ቁጥር ያላቸው በሰዎች በመኖሪያ ቤቶች በሚደረጉ ፍተሻዎች፣ በመንገድ ላይ በማስቆም፣ ከተሸከርካሪዎች ውስጥ በማውጣት እና በሌሎችም መንገዶች ከህግ ውጪ የሆኑ ግድያዎች ተፈጽመዋል፡፡

ግጭቱ በተካሄደባቸው አካባቢዎች ላይ በሴቶች ላይ ጾታዊ ጥቃቶች የተፈጸሙ ሲሆን አንዳንድ አካባቢዎች ላይ በቡድን በመሆን ሴቶች ላይ አስገድዶ መድፈር ተፈጽሟል፡፡

በታጣቂ ቡድኖችም ግድያዎች የተፈጸሙ ሲሆን እነዚህ ግድያዎች በመንግስት አመራር ውስጥ ያሉ ሰዎችን ኢላማ ያደረገ ነበር። ለእዚህም ማሳያነት በደቡብ ጎንደር ዞን ልዩ ስሙ አለም በር ወይም አሞራ ገደል በሚባል አካባቢ መስከረም 28 ቀን 2015 ዓ.ም በታጣቂ ቡድኖች በተፈጸመ ጥቃት ከ15 በላይ የመንግስት አመራሮች እና ጠባቂዎቻቸው ላይ ጥቃት በመፈጸም ግድያ ተፈጽሟል፡፡

በእዚህ ግጭት ላይ ከባድ የጦር መሳሪያዎች በዋናነት በመንግስት የጸጥታ ኃይሎች ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን እነዚህም ከባድ መሳሪያዎች በሰዎች መኖሪያ ቤቶች ላይ በመውደቅ በሰዎች ላይ ሞትን አስከትለዋል፡፡

በሰዎች ላይ ግድያ እና አካል ጉዳት ያደረሰው ሌላው በመንግስት የጸጥታ አካላት የሚፈጸም የሰው አልባ አውሮፕላን ጥቃት ሲሆን በእዚህም ጥቃት በተመሳሳይ በሰዎች ላይ ሞት እና ከፍተኛ የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡

ኢሰመጉ በእነዚህ አካባቢዎች የደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በአካል በመገኘት ምርመራ ያደረገ ሲሆን ነገር ግን በተወሰኑት ማለትም ምዕራብ ጎጃም ዞን ቡሬ ከተማ፣ ቋሪት ከተማ፣ ፍኖተ ሰላም ከተማ፣ ደምበጫ ከተማ፣ ደጋ ዳሞት ወረዳ፣ ምስራቅ ጎጃም ዞን ደብረ ማርቆስ ከተማ፣ እነማይ ወረዳ እና ቢቸና ከተማ፣ መርጦ ለማርያም ወረዳ፣ ግንደ ወይን ከተማ፣ ደጀን ወረዳዎች ላይ የምርመራ ስራው በተሰራበት ወቅት በአካባቢው በነበረው ግጭት ምክንያት በአካል ተገኝቶ የምርመራ ስራን መስራት የማይቻል የነበረ በመሆኑ ኢሰመጉ የርቀት የምርመራ ዘዴን በመጠቀም መረጃ እና

ማስረጃዎችን ከተጎጂዎች፣ ከተጎጂ ቤተሰቦች፣ ከአይን እማኞች እና ከሌሎችም የመረጃ እና የማስረጃ ምንጮች መረጃዎችን በመሰብሰብ ይህንን በሁለት ክፍል አጠናቅሯል።

ክፍል አንድ፡

ይህ ክፍል በክልሉ በግጭቱ የተሸፈኑ አካባቢዎችን የሚዳስስ ሲሆን እነዚህን አካባቢዎች ኢሰመጉ በአካል በመገኘት የምርመራ ስራን በማከናወን መረጃ እና ማስረጃዎችን በማሰባሰብ መግለጫውን ለማጠናቀር ችሏል።

ሀ. ባህርዳር ከተማ፡

ኢሰመጉ በባህር ዳር ከተማ ጥቅምት ወር 2016 ዓ.ም ባደረገው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የምርመራ ስራ በከተማው ከሀምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም አመሻሽ እስከ ነሀሴ 04 ቀን 2015 ዓ.ም በነበረው ግጭት ምክንያት ከ 140 በላይ ሰዎች የተገደሉ ሲሆን ከ 300 በላይ ሰዎች ላይ ደግሞ የአካል ጉዳት መድረሱን በከተማው ካሉ የመንግስት እና የግል የህክምና ተቋማት እንዲሁም ከሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤቶች ባገኘው መረጃ ለመረዳት ችሏል። በባህር ዳር ከተማ እና ዙሪያ ወረዳዎች ላይ ከላይ በተጠቀሰው ቀን በነበረው ግጭት ምክንያት ከ 4 ወር ጨቅላ ህጻን ጀምሮ እስከ 88 አመት እድሜ ያሉ አዛውንቶች ተገድለዋል።

በእዚህ ግጭት ምክንያት በሴቶች ላይ ከፍተኛ የሚባል ጾታዊ ጥቃት የተፈጸመ ሲሆን ለማሳያነት ያክል በባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 14 አቡነ ሃራ ተብሎ በሚጠራ ሰፈር እና ሳባታሚት በሚባል አካባቢዎች ውስጥ በመንግስት የጸጥታ ኃይሎች አማካይነት በርካታ ሴቶች ላይ በቡድን የአስገድዶ መድፈር ጥቃት መፈጸሙን ለመረዳት ተችሏል።

በክልሉ ያለውን ግጭት ተከትሎ ከፍተኛ የሆነ የንብረት ውድመት እየደረሰ ያለ ሲሆን በግጭቱ ላይ እየዋሉ ያሉ ከባድ የጦር መሳሪያዎች እና የሰው አልባ አውሮፕላን ጥቃት ለእዚህ ዋነኛ ምክንያት ሆነዋል። በእዚህ ግጭት ምክንያት የግለሰቦች መኖሪያ ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የጤና ተቋማት እና ሌሎችም ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚገቡ ንብረቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል። በተመሳሳይ በታጠቁ ቡድኖች አማካኝነት በፖሊስ ጣቢያዎች ላይ፣ በፍርድ ቤቶች እና በማረሚያ ቤቶች ላይ ጥቃት የተፈጸመ ሲሆን በእዚህም ምክንያት ከፍተኛ የሆነ ንብረት ሊወድም ችሏል።

በእዚህ ግጭት ላይ የተስተዋለው ሌላው ከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የአስገድዶ የመሰወር ድርጊት ሲሆን ይህ ድርጊት በመንግስት የጸጥታ አካላት እንዲሁም በታጠቁ ቡድኖች እየተፈጸመ ይገኛል። ቤት ለቤት በሚደረጉ ፍተሻዎች እና ከመንገድ ላይ በሚደረጉ አፈናዎች የደረሱበት ያልታወቁ ሰዎች መኖራቸውንም ለማወቅ ተችሏል።

በተጨማሪም በክልሉ ያለውን ግጭት ተከትሎ በመንግስት በኩል የሚደረጉ የስልክ እና ኢንተርኔት ግንኙነት ገደቦች በአካባቢው ያለው ነዋሪ እርስ በእርስ እንዳይገናኝ አንዲሁም በክልሉ ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ውስጥ ቤተሰብ ያላቸው ሰዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዳይገናኙ ምክንያት ሆኗል። በተመሳሳይ በታጠቁ ቡድኖች እንዲሁም በመንግስት የጸጥታ አካላት አማካኝነት የሚፈጸሙ የመንገድ መዘጋቶች ነዋሪው ከቦታ ቦታ በነጻነት እንዳይንቀሳቀስ ምክንያት እየሆኑ ይገኛሉ።

በመጨረሻም በክልሉ ባለው ግጭት ምክንያት የግጭቱ መጠን በሰፋባቸው አካበቢዎች ላይ ብዛት ያላቸው ሰዎች ግጭት ወደሌለባቸው አካባቢዎች እየተፈናቀሉ ያሉ ሲሆን ይህም የመፈናቀል ሂደት ከግጭቱ ባህሪ ጋር ተያይዞ አብዛኛውን ጊዜ ቋሚ የሆኑ መጠለያ ጣቢያዎች ባለመኖራቸው ምክንያት ተፈናቃዮች ችግር ላይ እየወደቁ ይገኛሉ። ለተፈናቃዮችም የሚደረገው ድጋፍ እጅግ አነስተኛ መሆኑን እና ከመንግስት በኩል አንዲሁም ዓለም አቀፍ እና አገር በቀል ከሆኑ ግብረ ሰናይ ተቋማት የሚደረጉ ድጋፎች አነስተኛ ከመሆናቸው የተነሳ ተፈናቃዮች ከፍተኛ ችግር ውስጥ ይገኛሉ።

ባህርዳር ከተማ ከሚገኙ የተለያዩ ሆስፒታሎች እና ከቤተክርስቲያን የተገኘ ግድያ እና የአካል ጉዳትን በተወሰነ መልኩ የሚያሳይ ዝርዝር።

ግደያ የተፈጸመባቸው ሰዎች ዝርዝር						
ተ.ቁ	ስም	ጾታ	ዕድሜ	ቦታ	የጥሰቱ ዓይነት	ቀን
1	ሞላ ጌታቸዉ	ወንድ	18	ባ/ዳር፣ቀ. 11	ግድያ	--------
2	ታደለ በላይ	ወንድ	34	ባ/ዳር፣ቀ. ዘንዘልማ	ግድያ	--------
3	ወንዴ አበባይ	ወንድ	20	ባ/ዳር፣ቀ. 11	ግድያ	--------
4	ዘመኑ ይግዛዉ	ወንድ	28	ባ/ዳር፣ቀ. 11	ግድያ	--------
5	ዘመኑ ይግዛዉ	ወንድ	44	ባ/ዳር፣ቀ. ኮኪታ ማሪያም	ግድያ	--------
6	ሃይሌ ተሰማ	ወንድ	25	ባ/ዳር	ግድያ	--------
7	አወቀ አገኘሁ	ወንድ	26	ባ/ዳር	ግድያ	--------
8	በላይነህ ደሴ	ወንድ	35	ባ/ዳር	ግድያ	--------
9	አሸናፊ መኩሪያዉ	ወንድ	40	ባ/ዳር	ግድያ	--------
10	ማሩ ምህረት	ወንድ	26	ባ/ዳር	ግድያ	--------
11	ይርጋለም አዱኛ	ወንድ	25	ባ/ዳር	ግድያ	--------
12	ብርሃኑ ይትባረክ	ወንድ	20	ባ/ዳር	ግድያ	--------
13	ጌታቸዉ አዲሱ	ወንድ	35	ባ/ዳር ቀ 13	ግድያ	--------
14	እንየዉ አጠቃ	ወንድ	-----	ባ/ዳር፣ቀ. በዓታ	ግድያ	2/12/2015

15	አየሁ ተስፋ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ 3	ግድያ	1/12/2015
16	ጌታቸዉ ሃይለስላሴ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ 16	ግድያ	4/12/2015
17	ወልደጊዮርጊስ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ 14	ግድያ	2/12/2015
18	ገብረስላሴ	ወንድ	-----	ባ/ዳር፣ቀ. በዓታ	ግድያ	2/12/2015
19	ገብረስላሴ	ወንድ	-----	ባ/ዳር፣ቀ. በዓታ	ግድያ	2/12/2015
20	ገብረስላሴ	ወንድ	-----	ባ/ዳር፣ቀ. በዓታ	ግድያ	2/12/2015
21	ገብረስላሴ	ወንድ	-----	ባ/ዳር፣ቀ. በዓታ	ግድያ	2/12/2015
22	ገብረስላሴ	ወንድ	-----	ባ/ዳር፣ቀ. በዓታ	ግድያ	2/12/2015
24	ወልደስንት	ወንድ	-----	ባ/ዳር፣ቀ. በዓታ	ግድያ	2/12/2015
25	ገብረስላሴ	ወንድ	-----	ባ/ዳር፣ቀ. በዓታ	ግድያ	2/12/2015
26	ፋንታሁን ይፍረድ	ወንድ	-----	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015
27	አድና ፈጠነ	ሴት	25	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015
28	ሞላ ደብሩ	ወንድ	-----	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015
29	አብራራዉ ይርጋ	ወንድ	40	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015
30	ተመስገን ዉበት	ወንድ	40	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015
31	ዉነቴ ደሴ	ወንድ	40	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015
32	ይትንን ታገለ	ወንድ	-----	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015
33	ሙላት ባይህ	ወንድ	28	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015
34	ፍሬዉ ዉነቴ	ወንድ	28	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015
35	አንሙት አንበዉ	ወንድ	32	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015
36	አበበ አያሌዉ	ወንድ	-----	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015
37	ፈንቴ	ወንድ	35	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015
38	አዳፋሪ ማሩ	ወንድ	41	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015
39	አሳምነዉ ገብሬ	ወንድ	28	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015
40	ደሴ ለይኩን	ወንድ	-----	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015

41	መልካም ተስፋ	ወንድ	-----	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015
42	ጌትነት ባሳዝነዉ	ወንድ	-----	ባ/ዳር፣ቀ. ሰባታሚት	ግድያ	2/12/2015
43	አስተዉል ወርቁ	ወንድ	60	-----	ግድያ	2/12/2015
44	ብርሃን ክንዱ	ወንድ	35	-----	ግድያ	2/12/2015
45	ሞላ	ወንድ	35	-----	ግድያ	2/12/2015
46	ወርቁ	ወንድ	70	-----	ግድያ	2/12/2015
47	ደሴ ጌቴ	ወንድ	30	-----	ግድያ	2/12/2015
48	አብራራዉ አየሁ	ወንድ	42	-----	ግድያ	2/12/2015
49	እንበለዉ ገረመዉ	ወንድ	29	-----	ግድያ	2/12/2015
50	ገብሩ ተባባል	ወንድ	32	-----	ግድያ	2/12/2015
51	አማኑኤል ደሴ	ወንድ	6 ወር	-----	ግድያ	2/12/2015
52	አዳነ ምህረት	ወንድ	30	-----	ግድያ	2/12/2015
53	አብዮት ይመኑ	ወንድ	-----	-----	ግድያ	2/12/2015
54	ይታይህ	ወንድ	-----	-----	ግድያ	2/12/2015
55	ታደለ መስፍን	ወንድ	-----	-----	ግድያ	2/12/2015
56	ይታየዉ ፈንቴ	ወንድ	-----	-----	ግድያ	2/12/2015
57	ግርማ ዳኛዉ	ወንድ	-----	-----	ግድያ	2/12/2015
58	ዘዉዱ መልሰዉ	ወንድ	-----	-----	ግድያ	2/12/2015
59	አለምነዉ አስማረ	ወንድ	-----	-----	ግድያ	2/12/2015
60	ይታጠቁ አያለዉ	ሴት	-----	-----	ግድያ	2/12/2015
61	አምሳሉ ወንድም	ወንድ	-----	-----	ግድያ	2/12/2015
62	ጌታቸዉ ጠብቀዉ	ወንድ	-----	-----	ግድያ	3/12/2015
63	ብርሃኑ የሺጥላ	ወንድ	-----	-----	ግድያ	3/12/2015
64	በሪሁን ወርቁ	ወንድ	-----	-----	ግድያ	3/12/2015

65	ነጻነት ተዋቸዉ	ወንድ	-----	-----	ግድያ	3/12/2015
66	ኪዳኔ በላይ	ወንድ	40	ባ/ዳር ቀ 16	ግድያ	2/12/2015
67	ፍቃዱ ጌትነት	ወንድ	42	ባ/ዳር ቀ 16	ግድያ	2/12/2015
68	መንግስቱ ዋለልኝ	ወንድ	35	ባ/ዳር ቀ 16	ግድያ	2/12/2015
69	እንዳሻዉ አማረ	ወንድ	40	ባ/ዳር ቀ 16	ግድያ	2/12/2015
70	አያሌዉ ደፈርሻ	ወንድ	58	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
71	ካሳሁን አያሌዉ	ወንድ	29	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
72	አብርሃም አያሌዉ	ወንድ	26	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
73	ገበያዉ ሞላ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
74	ሁልግዜ ተመስገን	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
75	አዲሱ ያለዉሁን	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
76	አስማማዉ ዋለ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
77	ይበልጣል አድማሴ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
78	ሰለሞን ሙሉዓለም	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
79	ሙጨ አ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
80	ምግባር አበበ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
81	ገበያዉ አለሙ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
82	ማማር መኪታዉ	ወንድ	20	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
83	ዮሃንስ ባይህ	ወንድ	17	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
84	አበጀ ዋሴ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
85	ባይህ አዳም	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
86	አገኘሁ ጌታሁን	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
87	ወጋየሁ ሞላ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
88	ይልቃል አሰፋ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015

89	ደስታዉ አስማማዉ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
90	እታባ አይቸዉ	ሴት	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
91	የሻንበል ድንበሩ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
92	ቢኒያም መለሰ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
93	እዮኤል ግርማ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
94	ይትባረክ ግርማ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
95	ያሬድ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
96	ጸዳል ዘሩ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015
97	ወንድሙ ብርሃኔ	ወንድ	-----	ባ/ዳር ቀ አቡነ ሃራ	ግድያ	2/12/2015

በባህርዳር ከተማ ከሃምሌ 28 - ነሃሴ/ 04 2015 ዓ/ም የአካል ጉዳት የደረሰባቸዉ ሰዎች ዝርዝር					
ተ.ቁ	ሙሉ ስም	ጸታ	ዕድሜ	ቦታ	የመብት ጥሰቱ ዓይነት
1	ሁንልኝ ዉበት	ወንድ	30	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
2	ገዛኻኝ ዋሴ	ወንድ	18	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
3	ጌታሰዉ አባይ	ወንድ	25	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
4	አንዷለም አለልኝ	ወንድ	23	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
5	ሁናቸዉ ሞገስ	ወንድ	20	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
6	አንተነህ ጓዴ	ወንድ	17	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
7	ወይንአረግ አበባዉ	ሴት	25	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
8	መንግሻ አታለል	ወንድ	30	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
10	ጥሩአለም አየነዉ	ወንድ	30	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
12	ፍቅሬ መለሰ	ወንድ	20	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
13	አማረ መስፍን	ወንድ	26	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት

14	ሀብታሙ ደርሶ	ወንድ	27	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
15	ያሬድ በሃይሉ	ወንድ	21	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
16	ወረደ ጥላዬ	ወንድ	45	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
17	አስረስ ክንዴ	ሴት	35	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
18	ማስተዋል ካሴ	ሴት	36	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
19	ቻላቸዉ አልኸኝ	ወንድ	22	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
20	ሙላት ተመስገን	ወንድ	22	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
21	አላምር ገዳሙ	ወንድ	30	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
23	አብርሃም ሃብታሙ	ወንድ	30	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
24	ያብባል ገድፍ	ወንድ	25	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
25	ተመስገን አልታሰብ	ወንድ	20	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
26	ጌትነት ይታዉ	ወንድ	20	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
27	ጥጋብ አስማማዉ	ወንድ	25	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
28	አንተሁን አበረ	ወንድ	47	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
29	አወቀ ቸኮል	ወንድ	35	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
30	መሞሃመድ አሚኑ	ወንድ	38	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
31	ፋሲካዉ ይደርሳል	ወንድ	33	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
32	ተመስገን ታከለ	ወንድ	47	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
33	ሀሁሉአገር ምስጋን	ሴት	17	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
34	ገቢዜዉ ጌትነት	ወንድ	24	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
35	ደጉ ወለላዋ	ወንድ	30	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
36	ካሳሁን ፈንቴ	ወንድ	32	ባ/ዳር	የአካል ጉዳት
በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ውስጥ ባሉ ቀበሌዎች በታጣቂዎች በተፈጸመ ጥቃት ሌላው የደረሰው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት አይነት እገታ ሲሆን ኢሰመጉ በአካባቢው በመገኘት ባደረገው ምርመራ መሰረት በእዚህ ጥቃት አንድ ግለሰብ በ24/03/2016 ዓ.ም ታግቶ ለ8 ቀን ያህል ከተያዘ በኋላ የተለቀቀ ሲሆን ኢሰመጉ በአካባቢዎች ከተጎጂዎች እና ከነዋሪዎች ጋር ባደረጋቸው ቃለመጠይቆች በተደጋጋሚ ጊዜ በታጠቁ ቡድኖች በአካባቢው እገታ እንደሚፈጸም እና ለታጋች ቤተሰቦች በመደወል የተመዘገቡና በባንኮችና በጸጥታ ኃይሎች ምርመራ ሊገኙ የሚችሉ የባንክ አካውንት በመንገር ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ መጠን እንዲያስገቡ እንደሚነገራቸውና ይህ ካልሆነ ግን የታገቱ ሰዎችን እንደሚገድሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ኢሰመጉ ይህንን የእገታ ድርጊት አስመልክቶ በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎችና አውራ ጎዳና መንገዶች ላይ እና በአማራ ክልል ባሉ አንዳንድ አካባቢዎች በስፋት እየተፈጸመ ያለ የሰብዓዊ መብት ጥሰት መሆኑን በተደጋጋሚ ጊዜያት መግለጹ የሚታወቅ ሲሆን ነገር ግን ለእዚህ ድርጊት ተገቢው ትኩረት እና ህጋዊ ዘላቂ መፍትሄ ባለመሰጠቱ ምክንያት ድርጊቱ በተጠናከረ መልኩ እየቀጠለ መገኘቱ የሚያሳስበው መሆኑን መግለጽ ይወዳል፡፡

ቄለም ወሊጋ ዞን፡

ኢሰመጉ በኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን፣ ጊዳሚ ወረዳ ልዩ ስሙ ቶኩማ መነሃሞ በተሰኘ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ አካል በሆነችው ጸሎት ቤት ህዳር 14 ቀን 2016 ዓ.ም ዓ.ም በታጠቁ ቡድኖች ጥቃት መፈጸሙን የሚያሳዩ መረጃዎች የደረሱት ሲሆን ይህንንም አስመልክቶ መረጃ እና ማስረጃ እንዲቀርብለት በደብዳቤ ቁጥር ER3-N35-ll2-23 በቀን ll/04/2016 ዓ.ም ዓ.ም ለኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ዋናው ጽ/ቤትን የጠየቀ ሲሆን ጽ/ቤቱ በደብዳቤ ቁጥር COO/5878/l03/16 በቀን l5/04/2016 ዓ.ም በሰጠው መረጃ መሰረት ከሌሊቱ 8፡00 ሰዓት ለይ በጸሎት ላይ ከነበሩ l7 ሰዎች በታጠቁ ቡድኖች 9 የቤተክርስቲያኒቱ አባላት ላይ የጅምላ ግድያ መፈጸሙን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ኢሰመጉ በአካባቢው በአካል የምርመራ ሰራተኞችን በማሰማራት የደረሰውን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ምርመራ ለማከናወን በአካባቢው ባለው የጸጥታ ሁኔታ ምክንያት ማከናወን ባይቻልም ይህንን ድርጊት ኢሰመጉ ህዳር 28 ቀን 2016 ዓ.ም ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ ማሳወቁ የሚታወስ ሲሆን አሁንም ከላይ እንደተገለጸው ከኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ዋናው ጽ/ቤት ያገኘነውን ዝርዝር እንደሚከተለው አቅርበናል፡፡

ተ.ቁ	ሙሉ ስም	ጾታ
1	ተሊላ ላሜሳ ታሲሳ	ወንድ
2	ቶሊና ላሜሳ ታሰሳ	ወንድ
3	ታምራት ላሜሳ ታሲሳ	ወንድ
4	ቃባና ቡልቻ ጉተማ	ወንድ
5	ጌታቸው ቤካታ ታይሳ	ወንድ
6	ሂካ አያና ያደሳ	ሴት
7	ጅረኛ ድንጋታ ቴሶ	ወንድ
8	ሰለሞን ድንጋታ ቴሶ	ወንድ
9	ሲራጅ ዳኑ	ወንድ

ከላይ በሰንጠረዡ ላይ ከተቀመጡት መካከል ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 ያሉት ሰዎች የአንድ ቤተሰብ አባላት የሆኑ ወንድማማቾች ሲሆኑ ተራ ቁጥር 7 እና 8 ላይ የተጠቀሱትም እንዲሁ የአንድ ቤተሰብ አባል የሆኑ ወንድማማቾች ናቸው፡፡

ሻሸመኔ ከተማ፡

ከጥር 14 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምዕመናንና ንብረቶች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና በኦሮሚያ ክልል ማለትም ሻሸመኔ፣ አርሲ ነገሌ፣ ነቀምት፣ ሰበታ፣ ወለቴ፣ በደሌ፣ አዳማ፣ አሰላ፣ ሽኪሶ፣ ቦሬ፣ ዶላ፣ ሻምቡ፣ በደሌ ፣ ቡሌሆራና አሰበተፈሪ ተፈጸሙትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ሲሆን የኢሰመጉ አቅም በፈቀደ መጠን ሻሸመኔ ከተማ ላይ ተፈጸመውን መብት ጥሰት ዋና ትኩረቱን አድርጎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ጥር 14 ቀን 2015 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ተደርጎ በነበረው መግባባት ላይ ያልተደረሰበት የሀይማኖት አባቶች ሹመት ጋር ተያይዞ ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የተፈጸሙ ሲሆን ጥር 26ቀን 2015 ዓ.ም በወቅቱ አዲስ ተሹመው የነበሩት ግለሰቦች በሻሸመኔ ከተማ ሪፍት ቫሊ እየተባለ በሚጠራው ሆቴል በማረፍ ጥር 27ቀን 2015ዓ.ም ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ለመግባት ባደረጉት ጥረት የመንግስት የጸጥታ አካላት ቤተክርስቲያንን ለመጠበቅ በቤተክርስቲያን የነበሩትን ምዕመን ከአካባቢው ለማራቅ በተጠቀሙት ተመጣጣኝ ያልሆነ የሀይል እርምጃ በርካታ ሰዎች ህይወታቸው እንዲያልፍ፤ የአካል ጉዳት እንዲደርስባቸው ምክንያት ሲሆን በወቅቱ ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ወዲያው ህክምና እንዲያገኙ ከማድረግ ይልቅ ወደ ፖሊስ ጣቢያ በመወሰዳቸው ብዙ ደም ሊፈሳቸውና ከፍተኛ ጉዳት ሊደርስባቸው መቻሉን እንዲሁም በእዚህ ሂደት ውስጥ የኦሮሚያ ክልል የጸጥታ ኃይሎችና ከሌላ አካባቢ በመኪና ተጭነው የመጡ

የተደራጁ ሰዎች መሳተፋቸውን እንዲሁም በአካላቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች እራሳቸውና ቤተሰቦቻቸው ላይ በሚደርስባቸው ዛቻና ማስፈራሪያ ምክንያት ከአካባቢያቸው ሊርቁ መቻላቸውን ኢሰመጉ ካካሔደው የምርመራ ውጤት ለማወቅ ተችሏል፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ ማህበረ ቅዱሳን በቀን 20/10/2015ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ማቅ/ሥአ/1996/05/ሀ ለኢሰመጉ በሰጡት ማስረጃ መሰረት እና ኢሰመጉ በሰራው የምርመራ ስራ 14 የእምነቱ ተከታዮች መሞታቸውን አሳውቋል፡፡ በተጨማሪም አላትዮን ሆስፒታል በቀን 15/7/2015ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር አ/ሆ/8752/01/15 ለኢሰመጉ በሰጠው ማስረጃ መሰረት በሻሸመኔ ከተማ በ27/5/2015ዓ.ም በተከሰተው ግርግር ወቅት ጉዳት ደርሶባቸው ለህክምና ወደ ሆስፒታሉ ገብተው ህክምና ያገኙ ተጎጂዎች ቁጥር ወንድ132፣ ሴት 35 በድምሩ 167 ሲሆኑ የጉዳቱ ምክንያትም በጥይት የተመቱ 15 ሰዎች እና በድብደባ ጉዳት የደረሰባቸው 152ሰዎች ሲሆኑ ለህክምና ከገቡት 167ሰዎች መካከል 2ሰዎች በህክምና ሲረዱ ቆይተው ህይወታቸው ማለፉን አስታውቋል፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ ማህበረ ቅዱሳን በቀን 20/10/2015ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ማቅ/ሥአ/1996/05/ሀ ለኢሰመጉ በሰጡት ማስረጃ መሰረት እና ኢሰመጉ በሰራው የምርመራ ስራ መሰረት በጥር 14 ቀን 2015ዓ.ም ወንድ 297፣ ሴት 96 በድምሩ በ393 የእምነቱ ተከታዮች ላይ የደረሰ የአካል ጉዳት ነበር። ማስተባበሪያ መምያው እንደገለጸው ጉዳቱ የደረሰው በወቅቱ አዲስ ተሹመዋል የተባሉት የሀይማኖት አባቶች ቤተክርስቲያን እንገባለን በማለታቸው እና የእምነቱ ተከታይ(ምዕመኑ) አጥቢያ ቤተክርስቲያኑን እንዲጠብቅ ከእምነቱ አባቶች በተላለፈው መልዕክት መሰረት የእምነቱ ተከታዮች ቤተክርስቲያን አናስገባም በማለት ለመከላከል በሞከሩ ሰዎች ላይ የደረሰ ሲሆን ከባድ ጉዳት የደረሰባቸው አብዛኞቹ ሰዎች በቀጠሮ ከሆስፒታል በመውጣት ቤታቸው በመኝታ ላይ ይገኙ እንደነበር እና የተወሰኑት ደግሞ ሀዋሳ በሚገኘው በያኔትና አላትዮን ሆስፒታል ህክምናቸውን ሲከታተሉ ቆይተዋል፡፡

ጉዳት የደረሰበት ግለሰብ ስለጉዳቱ ሲያስረዳ<<***ቤተክርስቲያኗ ባደረገችልን ጥሪ መሰረት ለጥበቃ ገብቼ ሳለ ጠዋት ላይ ህዝቡ ለማስቀደስ ሲገቡ የህግ አካል በሆኑት የኦሮሚያ ልዩ ኃይልና ፖሊሶች አንድ ላይ በመሆን ከቤተክርስቲያን እንዳንወጣ ከዘጉብን በኋላ እኛም በመከላከል ላይ እያለን ጠዋት 4ሰዓት ላይ ሁለት ሰው ገደሉብን ከሰዓት 9 ሰዓት ድረስ እየተከላከልን ምግብ ተከልክለን ውጪ ያለ ህዝብ እየታሰረብን በ3መኪና ሞልተው ሰዎችን አምጥተው ከህግ አካል ጋር አንድ ላይ በመሆን በከባድ መሳሪያ ፎቅ ላይ ሆነው በመተኮስና አስለቃሽ ጪስ በመርጨት ጉዳት ሊያደርሱ ችለዋል በዚህም ወቅት ተሰብሮ የወደቀ ብረት እላዬ ላይ በመውደቁ በግራ እግሬ ላይ ጉዳት ሊደርስ ችሏል***» በማለት አስረድቷል፡፡

አንድ ምስክር ስለሁኔታው ሲያስረዳ« ***በቀን 27/5/2015ዓ.ም ከጠዋቱ 3ሰዓት ጀምሮ ሁላችንም ቤተክርስቲያን ውስጥ ነበርን በእለቱ የወርሃዊ የቅዳሴ ፕሮግራም ስለነበረን አብዛኛው ሰው ቤተክርስቲያን ውስጥ ነበር ከ6ሰዓት በፊት 2ሰዎች ተገደሉ ፖሊስ አዳዲሶቹን ሰዎች ለማስገባት ሲሞክር አማኙ አላስገባም በማለቱ ምክንያት መከላከያ መጥቶ ነገሮችን***

በማረጋጋት 7ሰዓት ላይ መከላከያ ተመልሶ በመውጣቱ ምክንያት ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ሌላ ተግባር ፈጥረው አማኙን ህብረተሰብ ከከባድ መሳሪያ ጀምሮ እስከ ዱላ ድረስ ባለው አቅማቸው እጅግ በጣም ብዙ በመሆን የግድያ፣የአካልና የስነልቦና ጉዳት አድርሰዋል። ጓደኛዬም የዚሁ ጉዳት ሰለባ ሲሆን በወቅቱ ተገድሏል ተብሎ ከተገደሉ ሰዎች ጋር ነበር ነገር ግን በህይወት እንዳለ ሲታወቅ ለህክምናሳ ተወሰዶ በጽኑ ህመማን ማቆያ ውስጥ ለ8ቀን ቆይቶ ሊነቃ ችሏል» በማለት አስረድቷል።

በአካላቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ምስል እንደሚከተለው ቀርቧል።





በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ ማህበረ ቅዱሳን በቀን 20/10/2015ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ማቅሥአ/1996/05/ሀ ለኢሰመጉ በሰጡት ማስረጃ መሰረት ከላይ ከተጠቀሰው ክስተት ጋር ተያይዞ በወቅቱ በተለያዩ አካባቢዎች 421ሰዎች ታስረው የነበሩ መሆኑን ነገር ግን በአጠቃላይ ከተለያዩ የአዲስ አበባ አካባቢዎች በስምና በአድራሻ መለየት ያልተቻለ በተለያየ ቀንና ሁኔታ 2179(ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሰባ ዘጠኝ)ምዕመናንና አገልጋዮች ታፍነው ወደ አዋሽ አርባ እና አዋሽ 07 እስር ቤቶች ተወስደው ታስረው የነበሩ መሆኑን በተጨማሪም ከተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች በተለይም ከአዲስ አበባና ከኦሮሚያ ክልል የአህጉረ ስብከት ስራ አስኪያጆችን ሰራተኞችን፣ካህናት እና ምዕመናን እንግልትና እስር እንደደረሰባቸው ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመረዳት መቻላቸውን ገልጸውልናል።

ከላይ ተጠቅሶ የነበረውን ክስተት ባለመቀበላቸውና በመቃወማቸው በርካታ የሀይማኖቱ ተከታዮች እንዲሁም የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ከስራቸው ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ተሰናብተዋል። በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጥር 26 ቀን 2015ዓ.ም ባወጣው መግለጫ መሰረት ከጥር 29 ቀን 2015ዓ.ም ጀምሮ ባሉት 3 ቀናት ምዕመኑ እንዲጾምና በመላው አለም የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ካህናት እና ምዕመናን ሙሉ ጥቁር ልብስ እንዲለብሱ ትእዛዝ ያስተላለፈች ሲሆን የሀይማኖቱ ተከታዮች

የቤተክርስቲያኒቱን ትእዛዝ በማክበር ጥቁር ልብስ የለበሱ ቢሆንም በወቅቱ የተለያዩ ድርጅቶች "ለምን ጥቁር ልብስ ለበሳችሁ" በማለት ከስራ ማገዳቸውን ኢሰመጉ ከተለያዩ አካባቢዎች ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለማወቅ ችሏል፡፡

በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ የማህበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት በቀን 20/10/2015ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ማቅሥአ/1996/05/ሀ ለኢሰመጉ በሰጡት ማስረጃ መሰረት ምንም እንኳን የስም ዝርዝር የተካተተበት ባይሆንም ከቤተክርስቲያንና ከመንግስት መዋቅሮች ከስራ ገበታቸው የተፈናቀሉ፥ ደመወዝ የተቀጡ ወይም የታገዱ በቁጥር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ቦታ	ብዛት	ምርመራ
1	አዲስ አበባ	1	የሀይማኖት ጸብ ለማስነሳት እና ሁከትና ብጥብጥ አስነስተሃል በሚል ምክንያት የአንድ ወር ደሞዝ መቀጣት
2	ወሊሶ	5	ቤተክርስቲያን አውግዛ ከለየቻቸው ጋር አልተባበርም በማለታቸው ከስራ የታገዱ/የተባረሩ
3	ነቀምቴ	14	ቤተክርስቲያን አውግዛ ከለየቻቸው ጋር አልተባበርም በማለታቸው ከስራ የታገዱ/የተባረሩ
4	ሻሸመኔ	2	ቤተክርስቲያን አውግዛ ከለየቻቸው ጋር አልተባበርም በማለታቸው ከስራ የታገዱ/የተባረሩ
ለሁለት ወር ያህል ከስራ ታግደው የተመለሱ			
5	አዲስ አበባ	3	ጥቁር በመልበሳቸው
6	በዴሳ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል	8	ጥቁር በመልበሳቸው
ከስራ ደረጃ ዝቅ የተደረጉ እና በማስጠንቀቂያ የታለፉ			
7	ሻሸመኔ	3	--

በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ ማህበረ ቅዱሳን በቀን 20/10/2015ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ማቅሥአ/1996/05/ሀ ለኢሰመጉ በሰጡት ማስረጃ መሰረት የ 4 ግለሰቦች ባጃጆች መስታዎት መሰበሩን ገልጸዋል። በወቅቱ የቤተክርስቲያኗን ንብረት በተመለከተ ሙዳይ ምጽዋቶች ተሰብረው ገንዘብ እንዲሁም የቤተክርስቲያኗ ቋሚ ንብረቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለማወቅ ችሏል:

ትግራይ ክልል፡

ኢሰመጉ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በመንግስት የጸጥታ ኃይሎች እና በትግራይ ኃይሎች መካከል (በጊዜ ሂደት የተለያዩ ቡድኖች የተሳተፉበት) ተከስቶ የነበረውን የትጥቅ ግጭት ተከትሎ በትግራይ ክልል የተፈጸሙትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በአካል ተገኝቶ ለመመርመር የፈቃድ ጥያቄንና የትብብር ደብዳቤን አስመልክቶ ለኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር እና ለኢፌዴሪ ሰላም ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር ER3-M41/07/21 በቀን 12/07/2013 ዓ.ም ያስገባ ቢሆንም ሁለቱም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ምንም አይነት ምላሽ ሳይሰጡ ቀርተዋል፡፡

ኢሰመጉ ለኢፌዴሪ ሰላም ሚኒስቴር በድጋሚ የትብብር ደብዳቤ እንዲሰጠው በደብዳቤ ቁጥር ER3-230/16/21 በቀን 14/08/2013 ዓ.ም እንዲሁም ኢሰመጉ በወቅቱ ለነበረው የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ተመሳሳይ የፈቃድ እና የትብብር ደብዳቤ ጥያቄን ያቀረበ ቢሆንም ፈቃድ አና የትብብር ደብዳቤ ለመስጠት የተጠቀሱት ተቋማት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ምንም እንኳን ኢሰመጉ በወቅቱ ተፈጽመው የነበሩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በአካል ተገኝቶ ለመመርመር ዝግጅቱን ጨርሶ የነበረ ቢሆንም በነበሩ የፈቃድ እና የትብብር ክልከላዎች ምክንያት ይህ ሳይሳካ ቀርቷል፡፡ ነገር ግን ኢሰመጉ አቅም በፈቀደ መጠን በተለያዩ መንገዶች በክልሉ ተፈጽመው የነበሩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ይፋ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡
በተጨማሪም ኢሰሙጉ ከህዳር 2016ዓ.ም ጀምሮ በትግራይ በተመረጡ ቦታዎች ላይ ምርመራ ለማድረግ የተለያዩ ሙከራዎችን ያደረገ ሲሆን በህዳር 24 ቀን 2016 ዓ.ም የምርመራ ስራው የመጀመሪያ ቡድን ወደ ትግራይ ክልል ዋና ከተማ ወደ መቀሌ ለመሰማራት ተችሏል፡፡ የዚህ የምርመራ ቡድን ዋነኛ አላማ የነበረው ከሁለት ከተሞች የምራመራ ስራ በተጨማሪ ለሌሎች ቡድኖች የምርመራ ስራ ይረዳ ዘንድ ከተለያዩ የመንግስት አካላት በክልሉ ተዘዋውሮ ለመመርመር የምርመራ ፍቃድ እንዲሁም መቀመጫቸውን በመቀሌ ከተማ ካደረጉ የትግራይ ክልል ቢሮዎች በትጥቅ ግጭቱ ጊዜ እና ከትጥቅ ግጭቱ በኋላ የደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን እንዲሁም በክልሉ የተከሰተውን ከፍተኛ ርሃብ እና በእዚህ ምክንያት የደረሱ ጉዳቶችን የሚገልጹ መረጃዎችን መሰብሰብ ነበር፡፡

ይህንንም አስመልክቶ ኢሰመጉ የምርመራ ፍቃድን ለማግኘት ለትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር በደብዳቤ ቁጥር ER3-M41/188/23 በቀን 20/03/2016 ዓ.ም ያስገባ ቢሆንም ጊዜያዊ አስተዳደሩ አሁን ላይ በክልሉ ያሉ ችግሮችን በመግለጽ የምርመራ ፈቃዱን ሳይሰጥ ቀርቷል፡፡ በተመሳሳይ ኢሰመጉ ለተለያዩ የትግራይ ክልል የመንግስት ቢሮዎች የመረጃ ጥያቄን ያቀረበ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ለትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር በደበዳቤ ቁጥር ER3-M41/188/23 በቀን 20/03/2016 ዓ.ም፣ ለትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ማህበራዊ ጉዳይና መልሶ ማገገም ቢሮ በደብዳቤ ቁጥር ER3-M41/193/23 በቀን 20/03/2016 ዓ.ም እና ለትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ሴቶች ቢሮ በደብዳቤ ቁጥር ER3-M41/191/23 በቀን 20/03/2016 ዓ.ም ይገኙበታል፡፡

ሆኖም ግን በተጠየቀው መሰረት መረጃን ለማጋራት ፈቃደኛ የሆነውና መረጃውን ሊያጋራ የቻለው የክልሉ የማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ብቻ ሲሆን በተገኘውም መረጃ መሰረት በክልሉ 2,832,142 (ሁለት ሚሊዮን ስምነት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺ አንድ መቶ አርባ ሁለት) ተፈናቃዮች መኖራቸውን ቢሮ በደብዳቤ አሳውቋል፡፡

ምንም እንኳን ኢሰመጉ የተሟላ የምርመራ ስራን በትግራይ ክልል ማከናወን ባይችልም የምርመራ ባለሙያዎች በአካል በክልሉ ተገኝተው በነበረበት ወቅት ካደረጉት ምልከታ መረዳት እንደተቻለው በክልሉ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የአገር ውስጥ ተፈናቃይ እንደነበረ ምልከታው በተደረገበት ወቅት ኣረጋገጥን ሲሆን እነዚህም ተፈናቃዮች ምንም አይነት እርዳታ እያገኙ እንዳልነበረ ይህም የሆነበት ዋነኛ ምክንያት ዓለም አቀፍ የሆኑት እርዳታ ሰጪ ተቋማት በክልሉ ይሰጡ የነበረውን ሰብዓዊ ድጋፍ ማቋረጣቸው እንደሆነ እንዲሁም የክልሉ ጊዜያዊ አስተዳደር እና የፌደራል መንግስት በቂ እርዳታ ማቅረብ ባለመቻላቸው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

በነበረው የትጥቅ ግጭት ወቅት እንዲሁም የትጥቅ ግጭቱ በፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ከተፈጸመ በኋላ በሴቶች ላይ ሰፊ የሆነ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የተፈጸመ ሲሆን በትጥቅ ግጭቱ ወቅትም ሆነ ከትጥቅ ግጭቱ በኋላ ህክምና የሚሰጡ ተቋማት አገልግሎት በማቆማቸው ምክንያት በርካታ ሴቶች በተፈጸመባቸው ጾታዊ ጥቃት ህይወታቸውን ያጡ ሲሆን በርካቶችም በህክምና እጦት ምክንያት ለከፍተኛ ጉዳት ተዳርገዋል፣ እንዲሁም በቂ የሆነ የስነልቦና ህክምና እና ድጋፍ ባለማግኘታቸው ምክንያት ይህ መግለጫ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ በከፍተኛ የስነልቦና ጉዳት ውስጥ እንደሚገኙ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ለተጨማሪ ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭ በሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ማለትም በሴቶች፣ በህጻናት፣ በአካል ጉዳተኞች፣ በአረጋውያንና በሌሎችም ላይ ከፍተኛ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መፈጸማቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

በክልሉ በነበረው የትጥቅ ግጭት ምክንያት ከፍተኛ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እንደ ግድያ፣ አካል ጉዳት፣ ማፈናቀል፣ እስራት፣ ንብረት ውድመት፣ ከስራ እና ከትምህርት አላግባብ መታገድና መስተጓጎል፣ አድሎ፣ በተለያዩ አዲስ አበባን ጨምሮ የአገሪቱ አካባቢዎች በትግራይ ተወላጆች ላይ ማንነትን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች፣ እስራቶች፣ የንግድ ቤቶች እሸጋ፣ በክልሉ ውስጥም መሰረታዊ አገልግሎቶችን የማቋረጥና እንቅስቃሴን አላግባብ የመገደብ ስራ እና ሌሎችም የተፈጸሙ ሲሆን ትጥቅ ግጭቱ በሰላም ስምምነት ከተጠናቀቀ በኋላም እነዚህ ድርጊቶች በተወሰነ መልኩ የቀጠሉ ሲሆን በክልሉ ውስጥ መጠነ ሰፊ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መፈጸማቸውን የሚያሳዩ መረጃዎችን ለማግኘት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም በትግራይ ክልል የሚደረገው የመሰረተ ልማት መልሶ ግንባታ በተገቢው መልኩ በፍጥነት እየተከናወነ ባለመሆኑ ምክንያት ማኅበረሰቡ ከእነዚህ መሰረተ ልማቶች ሊያገኘው የሚገባውን ጥቅም እያገኘ አይደለም እንዲሁም የማገገሚያ (Rehabilitation) ስራዎችም እንዲሁ በተገቢው ሁኔታ እየተፈጸሙ ባለመሆናቸው ምክንያት ከፍተኛ ችግሮች እየተስተዋሉ ይገኛሉ፡፡

በመጨረሻም በትግራይ ክልል እና በአጎራባች ክልሎች መካከል የፐሪቶሪያን ስምምነት አፈጻጸም እና ሌሎች ምላሽ ያላገኙ ጉዮችን ተከትሎ ውጥረቶች እየታዩ ያሉ ሲሆን እነዚህ አለመግባባቶች ለተጨማሪ ግጭትና የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መነሻ ምክንያት እንዳይሆን አፋጣኝ ምላሽ ያስፈልጋቸዋል፡፡

ኢሰመጉ በትግራይ ክልል ያሉ የሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮችን በቅርበት እየተከታተለ ያለ ሲሆን በክልሉ በመገኘት ሰፋ ያለ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ምርመራ ለማከናወንና ከእዚህ በፊት ተዘግቶ የነበረውን ጽ/ቤት ዳግም ለመክፈት አሁንም ከሚመለከታቸው የመንግሰት አካላት ጋር የምርመራ ፈቃድ ለማግኘት በመነጋገር ላይ ያለ ሲሆን አስፈላጊውን ፈቃድና ትብብር በሚያገኘበት ጊዜ በክልሉ በመዘዋወር በመንግስት የጸጥታ አካላት፣ በኤርትራ ሰራዊቲ፣ በልዩ ኃይል፣ ሚሊሻና በተለያዩ አካላት የተፈጸሙ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በጥልቀት የምርመራ ስራዎችን በመስራት ግኝቶችን ይፋ የሚያደርግ ይሆናል፡፡

ኢሰመጉ በክልሉ በትጥቅ ግጭቱ ወቅትና ከትጥቅ ግጭቱ በኋላ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን አስመልግቶ ተደጋጋሚ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን በማውጣት ይህ ድርጊት እንዲቆም ሲወተውት የቆየ ሲሆን በዋናነት ከትጥቅ ግጭቱ በኋላ ያጋጠመውን ሰብዓዊ ቀውስ እና የእርዳታ አቅርቦት መቋረጥን ተከትሎ የተከሰተን ርሀብ በአስቸኳይ ምላሽ እንዲሰጠው የፌደራል መንግስትን፣ የክልሉን ጊዜያዊ አስተዳደርን እንዲሁም ዓለም አቀፍ ረጂ ተቋማትን ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ሲወተውት ቆይቷል አሁንም በተደጋጋሚ በመወትወትና በማሳሰብ ላይ ይገኛል፡
:

ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፡

1. **ጥሰቱ መነሻ ምክንያት የቅርብ እና የሩቅ**

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን የተከሰተው ጥሰት መነሻ ለረጅም ዓመታት የቆየ ሲሆን፣ የታጠቁ ኃይሎች በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ በተለያየ ጊዜ ጥቃት ሲያደርሱ ቆይቷል፡፡ የጥሰቱ መነሻ “አካባቢውን ከመጤዎች ማጽዳት” በሚል የሚደረግ የጥፋት ዘመቻ መሆኑን ለመረዳት የተቻለ ሲሆን በዚህ መንፈስ በአካባቢው አጠራር ቀይ የሆነን ማንኛውንም ሰው /ቤንሻንጉልና ጉሙዝ/ ያልሆነን በሙሉ መግደል፣ ንብረቱን መዝረፍና ማውደም ከአካባቢው ማስወገድ በሚል የተፈጸመ የመብት ጥሰት መሆኑን ለመረደት ተችሏል፡፡

- **የመብት ጥሰቱ ዓይነት**
  የተፈጸመው የመብት ጥሰት ግድያ፣ በጥይት፣ በቀስትና በተለያዩ ስለታማ ነገ ሮች የማቁሰል፣ የንብረት ውድመት እና መፈናቀል ናቸው፡፡
- **የመብት ጥሰቱ ፈጻሚ**
  የጉሙዝ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ጉህዴን/ ታጣቂ ቡድን ሲሆን የክልሉ ልዩ ኃይል/አድማ ብተና እና የአካባቢው ፀጥታ ኃይል በተለያየ መንገድ ድጋፍ ማድረጉን ለመረዳት ተችሏል፡፡

- **ጉዳዩ አሁን ያለበት ሁኔታ**
  በጥቃቱ ህይወታቸው ያለፈ ግለሰቦች የተቀበሩ ሲሆን፣ ቁስለኞች በተለያዩ በሆስፒታል እና በተመላላሽነት ታክመዋል። ቤት የፈረሰባቸው እና የተፈናቀሉ ነዋሪዎች ምንም አይነት ካሳ አልተሰጠም፣ በጥሰቱ ፈጻሚዎች ላይም ምንም አይነት ህጋዊ እርምጃ አልተወሰደም።

2. የጥሰቱ ዝርዝር

መንግስት ከጉህዴን ጋር ባደረገው ስምምነት የፓርቲው ታጣቂዎች የተሃድሶ ስልጠና ከተደረገላቸው በኋላ ማህበረሰቡን እንዲቀላቀሉ የተደረጉ ሲሆን፣ ከዚህም በተጨማሪ የተሃድሶ ስልጠና ሳይደርግላቸው ከነ መሳሪያቸው ማህበረሰቡን እንዲቀላቀሉ የተደረጉ ታጣቂዎች ነበሩ።

ጥቃት ከደረሰባቸው ሰዎች በተሰበሰበ መረጃ መሰረት በአካባቢ የተፈጸመው ጥቃት ለረዥም ጊዜ የታቀደበት እና ማንነትን መሰረት ያደረገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

በተለምዶ የጉምዝ ታጣቂዎች በመባል የሚታወቁት ታጣቂ ቡድኖች ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ባህር ዳር ከተማ ወደ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ግልገል በለስ ከተማ ለመድረስ 8 ሰዓት በተነሳ ሚኒ ባስ ተሽከርካሪ ። ሰዓት በተለምዶ ቻይና ካምፕ ተብሎ ወደ ሚጠራው ሰፈር ሲደርሱ ጥቃት ተፈጽሞባቸዋል።

ጥቃት ከተፈጸመባቸው ሰዎች በተገኘ መረጃ መሰረት ግልገል በለስ ከተማ በተልምዶ ቻይና ካምፕ ። ሰዓት የደረሰ ሲሆን፣ 3 (ሶስት) የቤኔሻንጉል ጉሙዝ ልዩ ኃይል መለያ ልብስ የሚመስል መለያ ልብስ የለበሱ የጉሙዝ ታጣቂ ዎች እና ቀስት የያዙ ግለሰቦች የተሸከርካሪውን ሹፌር አስቁመው የመኪና ውን ሞተር አጥፍቶ እንዲቆም መሳርያ በመደቀን እንዳስገደዱት፣ ከቆመ በኋላ ያስቆሙት ታጣቂ ቡድኖች ስልክ በመደወል ተጨማሪ የሰው ሃይል እንዲጨመር ያደረጉ ሲሆን በግምት የ 20 (ሃያ ደቂቃ) ቆይታ በኋላ በመኪና ተጭነው በግምት 15 (አስራ አምስት) የሚሆኑ እና በወቅቱ በመንግስት ትጥቅ እንዲፈቱ ያልተደረጉ የጉሙዝ ታጣቂዎች የስልክ ጥሪውን ተከትለው በቦታው መገኘታቸውን፣ በተሸከርካሪው ውስጥ 19 (አስራ ዘጠኝ) ተሳፋሪ የነበረ ሲሆን ለተሳፋሪዎቹ የአካባቢውን ቋንቋ የሚችል ግለሰብ ታጣቂዎቹ “ከነ መኪናው እናቃጥላቸው ወይስ አውርደን እንረሽናቸው” እያሉ ሲነጋገሩ በመስማቱ ለሹፌሩ መኪናውን በአፋጣኝ እንዲነዳው ይነግረዋል። ይህን ተከተሎ መኪናውን ያስቆሙት ታጣቂዎች ተኩስ በመክፈታቸው መኪና ውስጥ የነበሩ 3 (ሶስት) ሰዎች ወዲያው የተገደሉ ሲሆን፣ ሹፌሩን ጨምሮ 6 (ስድስት) ሰዎች ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል።

ጥቃቱ የተፈጸመበት ቦታ ከፍተኛ ኬላ 20 ደቂቃ የሚርቅ ቢሆንም ምንም አይነት የጸጥታ አካል አልደረሰላቸውም ነበር። የኢሰመጉ የምርመራ አባላት ለምርመራ በሄዱበት ሰዓት እነዚህ ተጎጂ ዎች በፓዊ ሪፈራል ሆስፒታል እርዳታ እየተደረገላቸው ነበር።

በተጨማሪም በተመሳሳይ ሰዓት ግልገል በለስ ከተማ ቀበሌ 02 ልዩ ቦታው ቻይና ካምፕ በሚባል አከባቢ 3 (ሶስት) ሰዎች ከብት በመጠበቅ ላይ እንዳሉ በእነዚሁ ታጣቂ ኃይሎች ተኩስ የተከፈተባቸው ሲሆን፣ ከሶስቱ ሁለቱ መሳሪያ

በመያዛቸው ቦታ ቦታ ይዘው እራሳቸውን የመከላከል እርምጃ ወስደዋል። በዚህ መሃል አንድ ግለሰብ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል።

ታጣቂዎቹ ይህን ከፈጸሙ በኋላ ካሉበት ካምፕ ተጨማሪ ሃይል በመያዝ በዛ ያሉ ነዋሪዎች ወደ ሚገኙበት በተለምዶ ቻይና ካ ምፕ በግምት 70 (ሰባ) የሚጠጉ ታጣቂዎች ክላሽ፣ መ ትረ የስ፣ ላውንቸር፣ ቦንብ፣ እና ቀስት በመያዝ አ ካባቢውን ለ 30 (ሰላሳ) ደቂቃ ያህል ከከበቡት በኋል ባገኙት ሰው ላይ መተኮስ የጀመሩ ሲሆን ከተማ የነበሩ በሰአቱ የነበረውን ሁኔታ በአካባቢው ላሉ የፖሊስ አባላት ቢያሳውቁም “እኛ ወደ አካባቢው ሄደን እርምጃ ለመውሰድ ስላልታዘዝን ምንም ማድረግ አንችልም” በማለት መልሰውላቸዋል።

በጥቃቱ የተገደሉ ግለሰቦች አብዛኛዎቹ ቤተሰብ የሚያስተዳድሩ በመሆናቸው የነሱ መገደል ቤተሰቦቻቸው ላይ ከፍተኛ ቀውስ አስከትሏል። የኢሰመጉ የምርመራ አባላት ለምርመራ በሄዱበት ሰዓት በዚህ ጥቃት የተጎዱ ግለሰቦች በባህርዳር ከተማ በግል እና በመንግስት ሆስፒታሎች እየተረዱ ነበር።

ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም በቤኔሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን ማንዱራ ወረዳ ግልገል በለስ ከተማ በልዩ ስሙ ቻይና ካ ምፕ በሚባለው ቦታ ማንነትን መሰረት ባደረገው ጥቃት ከፍተኛ የሆነ የሰው እና የንብረት ጉዳት የደረሰ ሲሆን፣ የአ ካባቢው አስተዳደር ከቤታቸው ለተፈናቀሉ እንዲሁም የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ግለሰቦች ወደነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ምንም አይነት ጥረት አላደረገም።

ይህንኑ አስመልክቶ የመተከል ዞን አስተዳደር ኮምንኬሽን ቢሮ ኃላፊ በደብዳቤ ቁጥር 01/ኢፋ/2015 በቀን 14/11/2015 ዓ.ም በሰጠው መረጃ መሰረት "በ30/10/2015 ዓ.ም.አንድ የከብት እረኛ በመገደሉ አንድ ግለሰብ ለአድማ በታኝ (በድሮ ልዩ ሃይል) አባላት ያሳወቀ ሲሆን፣ ይህን ተከትሎ አድማ በታኞች እና ታጣቂዎች በመሄድ እያሉ የአካባቢው ነዋሪ ተኩስ ከፍቶባቸዋል። አድማ በታኞች እና ታጣቂዎች ተኩስ አጸፋ ለመመለስ በተደረገ ተኩስ ልውውጥ 6 (ስድስት) ሰዎች የተገደሉ ሲሆን 7(ሰባት) ሰዎች ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል።" በማለት መልስ የሰጡን ሲሆን፣ የተሰጠን መልስ ከምርመራ ውጤቱ ጋር የሚቃረን ሆ ኖ ተገኝቷል።

በምርመራው ውጤት የሚያሳየው ጥሰቱ የተፈጸመው ከመንግስት ጋር በእርቅ ፈጽመው ትጥቅ ሳይፈቱ ከአድማ በታኞች ጋር በአንድ ካምፕ ውስጥ የነበሩት ታጣቂዎች የነዋሪዎችን መኖሪያ ከበው እና መኪና በማስቆም በፈጸሙት ተኩስ የተፈጸመ ጥሰት ሲሆን፣ ዞን አስተዳደር ኮምንኬሽን ቢሮ ኃላፊ አስቀድሞ ተኩስ ከፈተ ያሉት ግለሰብ የተገደለው በመኖሪያ ቤቱ እንዳለ በተከፈተበት የጅምላ ተኩስ እንጂ ሚች ተኩስ አስጀምሮ መገደሉን የሚያሱ መረጃዎች ከአካባቢ ነዋሪዎች እና ከአይን እማኞች የተገኘው መረጃ ሊያረጋግጥ አልቻለም። የሚችች ቁጥርም ከ10 ሰው በላይ እና የቁስለኞች ደግሞ ከ20 ሰው በላይ መሆኑ በአካባቢው ከነበሩ የዓይን ምስክሮች እና የህክምና ተቋማት ለመረዳት ተችሏል።

ሰንጠረዥ 1. ግድያ

ተ.ቁ	ስም	ዕድሜ	ጾታ	ቀን	ቦታ

1	ኢብራሂም ጫኔ መሐመድ	30	ወንድ	በ30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
2	የጌታ አበራ መሐመድ	40	ወንድ	በ30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
3	ሐሩን እንድሪስ ዓሊ	40	ወንድ	በ30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
4	ኑረዲን ዓሊ ሠይድ	13	ወንድ	በ30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
5	ተዋቸው አባተ መለሰ	22	ወንድ	በ30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
6	እሼቴ ውበቱ		ወንድ	በ30/10/2015 ዓ.ም.	ፓዊ ሆስፒታል
7	ሼክ አደም መሐመድ አህመድ	52	ወንድ	በ30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
8	ህራ ወርቁ		ሴት	በ30/10/2015 ዓ.ም.	ፓዊ ሆስፒታል
9	ፈለጉሽ ወርቁ ተኬ	18	ሴት	በ30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02

ሰንጠረዥ 2. አካል ጉዳት/ማሰቃየት/ድብደባ

ተ.ቁ	ስም	ዕድሜ	ጾታ	ቀን	ቦታ
1	ከዲጃ እንድሪስ ዓሊ	20	ሴት	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
2	ሰይድ እንድሪስ ዓሊ	32	ወንድ	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02

3	እየሩስ ወርቁ ተኬ	28	ሴት	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
4	ትግስት ወርቁ ተኬ	18	ሴት	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
5	አየሩ ደስይበል ጃለታ	25	ወንድ	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
6	ብርቱካን አራጋው መሐመድ	37	ሴት	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
7	ማርሸት ወለሌ ጌቱ	28	ሴት	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
8	ኢማን መሐመድ ዓሊ	4	ሴት	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
9	ዓሊ አደም		ወንድ	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
10	ጌታሁን የሀንስ		ወንድ	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
11	የሊቶ ምትኩ		ወንድ	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
12	መሐመድ ጡዋር		ወንድ	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
13	ትንሳዔ ተስፋዬ		ሴት	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
14	ዩሱፍ ምትኩ		ወንድ	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
15	ኢሳ መሐመድ		ወንድ	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
16	ሙሉጌታ አየነው		ወንድ	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
17	ማሪያ አደም		ሴት	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02

18	መቅደስ ፋንተ		ሴት	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
19	ዘፋኒያ መሐመድ		ሴት	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02
20	ኡመር		ወንድ	30/10/2015 ዓ.ም.	ግልገል በለስ ከተማ ቀ.02

ሰንጠረዥ 3. እስራት

ተ.ቁ	ስም	ዕድሜ	ጾታ	እስራቱ የተፈበት ቀን	እስራቱ የተፈጸመበትቦታ
1	አመንቴ ባሲዞ ባውቆ	30	ወንድ	25/10/2015 ዓ.ም	በጉህዴን ታጣቂዎች ካምፕ

ጋምቤላ ክልል

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) በ27/12/2014ዓ.ም በጋምቤላ ክልል የሚገኙ ተፈናቃዮችን የጎበኘ ሲሆን ተፈናቃዮቹ ከ2006ዓ.ም ጀምሮ ከደቡብ ሱዳን ከኑዌር ብሔረሰብ ዞን አኮቦ ወረዳ አራት ቀበሌዎች አካባቢያቸውን ለቀው ጎግ ወረዳ ፒኝዶ አቅራቢያ 04ቀበሌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኙ ሲሆን በታህሳስ ወር ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ በአራት ቀበሌዎች ላይ ድንገተኛ የሆነ የጦር መሳሪያ ተኩስ የነበረ መሆኑን እና በርካታ ሰዎች ህይወታቸውን ማጣታቸውን እና ከአብዛኛው ተፈናቃይ ቢያንስ ከአንድ በላይ ቤተሰብ በጥቃቱ የተገደሉባቸው መሆኑን እንዲሁም በወቅቱ ጥቃቱ ሲደርስ ማንኛውም የጸጥታ ኃይል በአካባቢው ባለመኖሩ ጥቃቱን የከፋ እንዳደረገው ኢሰመጉ ተፈናቃዮቹን ባነጋገረበት ወቅት ለማወቅ ችሏል።

ተፈናቃዮች ጎግ ወረዳ ፒኝዶ አቅራቢያ 04 ቀበሌ ከደረሱ በኋላ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ሆነ ሌሎች አካላት በቂ የሚባል ድጋፍ እንዳልተደረገላቸውና በስድስት ወይም በዘጠኝ ወር አንዴ ለሶስት ቤተሰብ ሃምሳ ኪሎ ይሰጣቸው የነበረ ቢሆንም እሱም መቆሙን እና አሁን ላይ የሚተዳደሩትም በቅርብ እርቀት የጊሎ ወንዝ ላይ አሳ በማጥመድ እና የሰፈሩበት አካባቢ በእጅ ቁፋሮ የግብርና ስራ በመስራት ሲሆን ለግብርና ስራቸውም ከሚመለከተው የመንግስት አካላት ተገቢውን ድጋፍ እንዳልተደረጋቸው እንዲሁም የመሰረተ ልማት አገልግሎት እንደ ጤና ተቋም ፣

ትምህርት ቤት እና የውሃ አቅርቦት አለመኖሩን በተጨማሪም ወደ አካባቢያቸው የመመለስ ፍላጎት ቢኖራቸውም ከፍተኛ የደህንነት ስጋት እንዳለባቸው ኢሰመጉ በ ጉብኝቱ ወቅት ለማወቅ ችሏል፡፡

በጋምቤላ ያሉ ተፈናቃዮና መጠለያ ጣቢያ ምስል





በጋምቤላ ክልል ከላይ ከተጠቀሰው አካባቢ ተፈናቅለው በተለያዩ ቀበሌዎች ተጠልለው የሚገኙ ተፈናቃዮች ቁጥር

ተ.ቁ	ቀበሌ	ወንድ	ሴት	ድምር
1	ኣፓረዋ	509	495	1004
2	ቡቶር	302	439	741
3	ኡጆኪ	578	590	1168
4	አኮቦ	501	590	1091

አፋር ክልል፡

ኢሰመጉ ከሃምሌ 10 ቀን 2015ዓ.ም እስከ ሃምሌ 13 ቀን 2015 ዓ.ም በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሁለት ወረዳዎች ማለትም አሳይታ እና አፋንቦ ምርመራውን አካሂዷል፡፡ በአሳይታ ችግሩ ካለባቸው ቀበሌዎች መካከል ዋሙሌ፣ ኮሮዶራ፣ ካርቡዳ፣ አዳዳሊ፣ በርጊ እና ገላሌ ፤ ከአፋንቦ ቀበሌዎች ደግሞ አለሰበሎ እና ሆንጉቢ ቀበሌዎችን በአካል በመገኘት ችግሩን መመልከት ችለናል፡፡ ከአለሰቤሎ ቀበሌ በአደሃመቱ እና ቡከስ የሚባሉ ጣቢያዎች ችግሩ ጎልቶ እንደሚታይ ለማስተዋል ተችሏል፡፡

በአፋር ክልል በሚገኘው አዋሽ ወንዝ ላይ ለመገንባት ለተሞከረው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ መስኖ ይሆን ዘንድ የተገደበው አዋሽ ወንዝ ግድብ ማስተንፈሻ ወደ አሳይታ እና አፋንቦ ወረዳዎች በመለቀቁ ምክንያት የሁለቱ ወረዳዎች ቀበሌዎች በሰው ሰራሽ ሃይቅ መዋጣቸውን በአካባቢው የሚኖሩ ነዋሪዎች ለኢሰመጉ ገልጸዋል፡፡

በሰው ሰራሽ ሃይቅ የተዳረጉት ሁለት ወረዳዎች ሲሆኑ በአሳይታ ችግሩ ካለባቸው ቀበሌዎች መካከል ዋሙሌ፣ ኮሮዶራ፣ ካርቡዳ፣ አዳዳሊ፣ በርጊ እና ገላሌ ፤ ከአፋንቦ ቀበሌዎች ደግሞ አለሰበሎ እና ሆንጉቢ ቀበሌዎችን በአካል በመገኘት ችግሩን መመልከት የተቻለ ሲሆን ከአለሰበሎ ቀበሌ በአደሃመቱ እና ቡከስ የሚባሉ ጣቢያዎች ችግሩ ጎልቶ እንደሚታይ ለመረዳት ተችሏል፡፡



ምስል ፣ በአሳይታ ወረዳ ከአምስት መቶ አባወራዎች በላይ ይታረስ የነበረ በአሁኑ ሰአት በሰው ሰራሽ ሃይቅ የተዋጠ

በዚህ ሰው ሰራሽ ሀይቅ ምክንያት መፈናቀል፣ አካል ጉዳት ጨምሮ የተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት የደረሰባቸው መሆኑን፤ ቤቶቻቸው፣ ንብረቶቻቸው እና ከብቶቻቸው መውደማቸውንና በውሃ መዋጣቸውን፣ የቀሩትም ከብቶቻቸው ከገደብ የሚለቀቅ የተበከለ ውሀ እየጠጡ በመሆኑ ከፍተኛ ጉዳት እና ሞት እየደረሰባቸው መሆኑን ተጎጂዎች አስረድተዋል። በተጨማሪም በሁለቱ ወረዳዎች እንዲሁም በአካል በመገኘት መመልከት የተቻለባቸው ስምንት ቀበሌ ተጎጂዎች ዳግም የአዋሽ ወንዝ አቅሙን ጨምሮ ሊለቀቅ ይችላል የሚል ሥጋት እንዳለባቸው የገለጹ ሲሆን ምርመራ የተከናወነበት የክረምት ወቅት እንደመሆኑ የውሃ መጠኑ መጨመሩ ለዚህ አይነት ስጋታቸው ዋነኛ ምክንያት እንደሆነ አስረድተዋል ይህንንም ስጋት እና ሰው ሰራሽ ሃይቁ ቦታ ድረስ በመገኘት መመልከት ተችሏል፡፡ ክትትል በተደረገባቸው አካባቢዎች ሰው ሰራሽ ሃይቁ ያልደረሰበት ቦታዎች በራሳቸው እንዲሁም በመንግስት እርዳታ በአሮፕላን ጭምር መንግስት ከቦታው እንዲወጡ ያደረገ ቢሆንም፣ መደበኛ ኑሯቸውን ለመቀጠል የሚያስችላቸውን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ለተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔ ማፈላለግን በተመለከተ ምንም ስራ እንዳልተሰራ ማወቅ ተችሏል፡ ፡



ምስል 2 በአፋንቦ ወረዳ የቴምር እርሻ የነበረ በአሁኑ ሰአት በውሃ በመወሰድ ላይ ያለ ቦታ

ኢሰመጉ ባከናወነው ክትትል ተፈናቃዮች በቂ፣ ወቅቱን የጠበቀ እና ተደራሽ የሆነ ምግብ፣ ውሃ፣ መጠለያ፣ የጤና አገልግሎት፣ ትምህርት እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ያካተተ የሰብዓዊ ድጋፍ እየቀረበላቸው እንዳልሆነ ተመልክቷል፡፡ በተለይ ውሃው ድንገት በተለቀቀበት ወቅት የሕክምና ቁሳቁሶች፣ የመድኃኒቶች እና የክትባት ማስቀመጫ ጨምሮ በርካታ የጤና አገልግሎት ተቋማት በውሃው ተውጠው በመውደማቸው የሕክምና ቁሳቁስ እና መድኃኒት እጥረት ፈጥሯል።



ምስል 3 በአፋንቦ ወረዳ በሰው ሰራሽ ሃይቅ ተውጠው ከነበሩ መማሪያ ክፍሎች መካከል አንዱ አሁናዊ ሁኔታ

ኢሰመጉ በቦታው የላከው ቡድን በአካባቢዎች የነበረውን አሳሳቢ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ከለየ በኋላ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የፌዴራል እና የክልል መንግሥት ተቋማት የሁኔታውን አሳሳቢነት የሚገልጽ በተለይ የሰብዓዊ መብት ጥያቄ እና መረጃዎችን ለማግኘት በአካል እና በደብዳቤ ጥያቄ ቢያቀርብም መልስ ማግ ኘት አልተቻለም፡፡ ከነዚህም መካከል የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤትን በ12/11/1014ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ER3-M41/145/23 ፤ ለኢፌዲሪ ውሃ እና ኢነርጂ ሚንስትር በ16/11/1014ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ER3-M41/156/23 ስለጉዳዩ ማብራሪያ የተጠየቀ ቢሆን ከሁለቱም የመንግስት ቢሮዎች ምንም አይነት ምላሽ ሳይገኝ ቀርቷል፡፡ በተመሳሳይ ኢሰመጉ ለኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ስራዎች ኮርፖሬሽን የውሃና ኢነርጂ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ዘርፍ

ከላይ ከተከሰተው ክስተት ጋር ተያይዞ መረጃን የጠየቀ ሲሆን ኮርፖሬሽኑ በሰጠው ምላሽ ግድቡ በ2005 ዓ.ም ውስጥ መሆኑን በመግለጽ ከግድቡ ስራ መጠናቀቅ በ ኋላ የግድቡን እንክብካቤ እና የውሃ ፍሰት መቆጠጠር ስራ እየተከናወነ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን መሆኑን በመግለጽ የተባለውን መረጃ መስጠት የሚችለውም ይህ ተቋም መሆኑን የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ስራዎች ኮርፖሬሽን የውሃና ኢነርጂ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ዘርፍ በደብዳቤ ቁጥር ውኢደ/49.1/653/15 በቀን ሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም በላከው ደብዳቤ አሳውቋል፡፡

የምርመራ ቡድኑ የተንዳሆ ግድብን አስመልክቶ ቦቦታው በመገኘት ያለውን እውነታ እንዲሁም የችግሩን መጠን ከተመለከተ በኋላ ግድቡን በበላይነት ለሚያስተዳድረው ለኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን በደብዳቤ ቁጥር ER3-N35/92/23 በቀን 12/12/2015 ዓ.ም የአዋሽ ወንዝ ላይ የተገነባው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የተንዳሆ ግድብ ማስተንፈሻ ለምን ወደ ሁለቱ ወረዳዎች እንደፈሰሰ ፈሶም ይህንን አይነት ጉዳት ሲያደርስ ለምን ምንም ማድረግ እንዳልተቻለ ማብራሪያ ተጠይቋል፡፡

ኮርፖሬሽኑንም በጎዳር 4 ቀን 2016 ዓ.ም ቢሮ ድረስ በመሄድ ማነጋገር የተቻለ ሲሆን በተገኘው መረጃ መሰረት ግድቡ በአሁኑ ሰዓት ለጊዜያዊነት ቁጥጥር የሚደረግለት በኮርፖሬሽኑ እንደሆነ ይሁን እንጂ ፋብሪካው አገልግሎት እንደማይሰጥ ምንም አይነት ምርትም እያመረተ እንዳልሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ኮርፖሬሽኑ በቦታው ሰራተኞት እንዳሉት ስራቸውም ከአዲስ አበባ ዋናው መቆጣጠሪያ ጣቢያ በግድቡ ላይ የውሃ መጠን ሲጨምር ማስተንፈሻውን በሚነገራቸው ልክ እንደሚከፍቱ ነው፡፡ የተንዳሆ ግድብ ማስተንፈሻ የተገነባው በሰከንድ 200 ሜትር ኪዩብ ውሃ ለማስተንፈስ ታስቦ ቢሆንም እስዛሬ በማስተንፈሻው በሰከንድ ከ100 ሜትር ኪዩብ ውሃ በላይ ተለቆ እንደማያውቅ፣ አሁን የሚስተዋለው ችግር ከውሃ መጠን ጋር የሚገናኝ እንዳልሆነ እና ኮርፖሬሽኑ እንዲቆጣጠር የተፈቀደለት ግድቡን ብቻ ሲሆን ከግድቡ ውጪ የሚገኙትን ስራዎች ማከናወን የሚገባው ባብዛኛው የታችኛው የአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በአሁኑ ሰአት በአፋር ክልል ሁለቱ ወረዳዎች የተከሰተው ችግር የታችኛው የአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን እንዲያከናውናቸው ከሚፈለጉ ነገር ግን ያልተከናወኑ ስራዎች ምክንያት መሆኑን ከኮርፖሬሽኑ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

በተገኘው መረጃ መሰረት በታችኛው የአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን ሊሰሩ ከሚገቡ ነገር ግን ያልተሰሩ ስራዎች

- የሎጊያ ወንዝ ካናል በጎርፍ ከፈረሰ በኋላ ጥገና አልተደረገም
- ከሚሌ እስከ አፋንቦ ደለል መጥረግ አልተከናወነም
- የአዋሽ ገባር ወንዞች ላይ ቁጥጥር አይደረግም
- የወንዝ ጥገና፣ የወንዝ ቅየሳ እንዲሁም የደለል ጠረጋ ስራዎች አለመሰራታቸው፡፡

በተገኘው መረጃ መሰረት በአፋር ክልላዊ መንግስት ሊሰሩ ከሚገቡ ነገር ግን ያልተሰሩ ስራዎች

- በኮርፖሬሽኑ በተደጋጋሚ የነርፍ ስጋትን በሚመለከት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ መስተዳድሩ ችላ ማለት
- በግድቡ ማስተንፈሻ መንደሮች ላይ የሚደረግ የአርብቶ አደሮችን ሰፈራ እንዲያስቆም ሲጠየቅ ችላ ማለቱ
- ችግሩ ከተከሰተም በኋላ የችግሩ ዋነኛ ተጠያቂ የሆነውን የታችኛው የአዋሽ ተፋሰስ የሰመራን ጽ/ቤት በቅርበት አለመስራቱ

በአጠቃላይ ኮርፖሬሽኑ የውሃ መልቀቅ ስራዎች ከመሰራታቸው በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎችን ለሚመለከታቸው አካላት ቢያሳውቁም ሰራዎች እንዳልተሰሩ በቃል እንዲሁም በደብዳቤ አስረድቷል፡፡ ተቋሙ ላለፉት ሶስት እና አራት አመታት ስህተቶች እንዲስተካከሉ አልፎም ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለአፋር ክልላዊ መንግስት፤ የታችኛው የአዋሽ ተፋሰስ፤ ለመስኖ እና ቆላማ ሚንስቴር፤ ለተንዳሆ ግድብና መስኖ አስተዳደር ማዕከል እንዲሁም ለአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ቢሮ በተደጋጋሚ በተለያየ ደብዳቤዎች ቢያሳውቅም አልተስተካከልም፡፡ በተጨማሪም ኢሰመጉ ባሰባሰባቸው መረጃዎ መሰረተ የአዋሽ ወንዝ ተፋሰስ የልማት ስራዎን የሚመለከተው የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር መሆኑን ስለተረዳ በድጋሚ ለውሃና ኢነርጂ ሚንስትር ሚንስቴር በደብዳቤ ቁጥር ER3-M41/12/2024 በቀን 16/07/2016 ዓ.ም ማብራሪያ የጠየቀ ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ምንም ምላሽ አላገኘም፡፡ ኢሰመጉ ይህንን አስመልክቶ የታችኛው አዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣንን አፋር ክልል ባለው ቢሮ እንዲሁም በሌሎች ቢሮዎች ለማግኘት እና መረጃ ለመቀበል ያደረገው ሙከራ ያልተሳካ ሲሆን ነገር ግን ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ የታችኛው አዋሽ ተፋሰስ በእዚህ ልዩ መግለጫ በቀረቡት ጉዳዮች ላይ ማብራሪያን ማቅረብ ከቻለ ኢሰመጉ እነዚህን ማብራሪያዎች እና ማስረጃዎች ለመቀበል ዝግጁ መሆኑን ከወዲሁ ይገልጻል፡፡

ሲዳማ ክልል፡

አሰመጉ በሲዳማ ክልል ማዕከላዊ ሲዳማ ዞን ሎካ አባያ ወረዳ በሚገኙ አልቦ፣ ጭረቻ፣ ቡሬ ቡኩቶ እና ፉልቃ በሚባሉ ቀበሌዎች ላይ ከጥር 29 ቀን እስከ የካቲት 01 ቀን 2016 ዓ.ም የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የምርመራ ስራ አከናውኖ ግኝቶቹን እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

በሲዳማ ክልል ማዕከላዊ ሲዳማ ዞን ውስጥ የሚገኘው የሎካ አባያ ወረዳ ፓርክ ካለበት በግምት 10 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከአጼ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ በአካባቢው ሰፍረው የሚገኙ ነዋሪዎች ከወረዳው ፖሊስ አዛዥ በተገኘ መረጃ መሰረት ፓርኩ በ2007 ዓ.ም ባደረገው የማካለል ስራ ምክንያት እነዚህ ነዋሪዎች በፓርክ ውስጥ በመከለላቸው ምክንያት በሚል ከተነጂዎች በተገኘ መረጃ መሰረት ከታች በሰንጠረዥ ውስጥ የተቀመጡ ንብረቶች በአልዳቦ ቀበሌ ታህሳስ 22 ቀን 2016 ዓም፣ በጭረቻ ቀበሌ ታህሳስ 06 ቀን 2016 ዓ.ም፣ በቡራ ቡኩቶ እና ፉልቃ ቀበሌዎች በታህሳስ 02 ቀን 2016 ዓ.ም ወድመዋል፡፡

	አልዳቦ ቀበሌ	ጭረቻ ቀበሌ	ቡሬ ቡኩቶ ቀበሌ	ፉልቃ ቀበሌ
አባወራ	55	331	47	31
እማወራ	8	163	2	7
የቤተሰብ አባላት ብዛት	510	3772	347	286
የወደመው ንብረት ግምት	129 010 000	232 540 000	72 000 000	23 860 000

ይህ ድርጊት በተፈጸመበት ወቅት በአልዳቦ ቀበሌ 2 (ሁለት) ሰዎች ላይ እስራት የተፈጸመ ሲሆን በጭረቻ ቀበሌ ውስጥ ደግሞ በ 4 (አራት) ወንድ እና 1 (አንድ) ሴት ላይ ድብደባ ተፈጽሞባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በቡሬ ቡኩቶ ቀበሌ ውስጥ የደረሰባቸውን የንብረት ውድመት ተከትሎ አቶ ሹቤ ዱራ የተባሉ የ80 (ሰማንያ) አመት አዛውንት እና አቶ የቴራ ሀርጋሞ የተባለ የ40 (አርባ) አመት ጎልማሳ በ22/05/2016 ዓ.ም በድንጋጤ ህይወታቸው ማለፉን ለመረዳት ተችሏል፡ ፡

ኢሰመጉ ያነጋገራቸው ተጎጂዎች ከአጼ ኃይለ ስላሴ ዘመን ጀምሮ ይገበሩበት የነበረውን ደረሰኝ ለማየት የተቻለ ሲሆን ኢሰመጉ በአካባቢው በአካል በመገኘት ባደረገው ምልከታ የነዋሪዎቹ ቤቶች መቃጠላቸውን እና ነዋሪዎቹ በቅጠል በተሰራ ትናንሽ መጠለያ ጫካ ውስጥ ሰርተው በማይመች የአየር ሁኔታ ውስጥ ዝናብና ጸሀይ እየተፈራረቀባቸው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከእዚህም በተጨማሪ በነዋሪዎች ላይ በመንግስት አካላት እስራት፣ ድብደባ፣ ዛቻ እና ማስፈራራት የመሳሰሉት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እየተፈጸሙ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

የሎካ አባያ ወረዳ ፖሊስ አዛዥ ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ መሰረት ቤቶቹን የማንሳት ስራ የተሰራው ጥናት ተሰርቶ መሆኑን፣ ቤት የተቃጠለባቸው ሰዎች በሌሎች ቦታዎች ቤትና ቦታ ያላቸው መሆኑን፣ በፓርክ ውስጥ መሆናቸው እና እንዲወጡ እንደተነገራቸው እና በእዚህ አግባብ ቤቶቹን የማንሳት ስራ መሰራቱን ገልጸዋል፡፡

በተመሳሳይ የሲዳማ ክልል ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ፓርኩ ከበፊትም ጀምሮ የነበረ መኑንና ሰዎቹም በፓርኩ ይዞታ ላይ መስፈራቸውን፣ እርምጃ ከመወሰዱም በፊት ቀደም ተብሎ ከነዋሪዎቹ ጋር ንግግር መደረጉን ነገርግ ነዋሪዎቹ ለመነሳት ፍቃደኛ ባለመሆናቸው የተወሰደ እርምጃ መሆኑን፣ ቤቶቻቸው የፈረሱባቸው ሰዎች በከተማ ሌላ ቤት ያላቸው መሆኑን ለኢሰመጉ ገልጸዋል፡፡

ነገር ግን ኢሰመጉ ባደረገው የምርመራ እንዲሁም የምልከታ ስራ ነዋሪዎቹ ከአጼ ኃይለስላሴ ጊዜ አንስቶ በቦታው ላይ ስለመኖራቸው የሚያሳይ ግብር ይገበሩበት የነበረው ማስረጃ እንዳላቸው፣ ቅያሪ ቤት በከተማ እንደሌላቸው፣ ቤቶቹን የማቃጠል እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ምንም አይነት ውይይት እንዳልተደረገ እና ቅድመ ማስጠንቀቂያ

እንዳልተሰጣቸው ይልቁን በድንገት በመምጣት ቤቶቹ መቃጠላቸውን፣ በነዋሪዎቹም መካከል ልዩነት በማድረግ አንዳንድ ቤቶችን በመለየት ሳይቃጠሉ እንደቀሩ ይህም ከአመራሮች ጋር ግንኙነት ያላቸው ቤቶች ተለይተው እንዳልተቃጠሉ፣ ቤቶቻቸው ለተቃጠሉባቸው ሰዎች ምንም አይነት ካሳ እንዳልተሰጣቸውና ምንም አይነት ቅያሪ ቤት እንዳልተሰጣቸው ለመረዳት ተችሏል።

በተጨማሪም ለነዋሪዎቹ ምንም አይነት መፍትሔ ሳይሰጥ እስራት እየተፈጸመባቸው መሆኑን እና ለኢሰመጉ ለምን አቤቱታ አቀረባችሁ በሚል የታሰሩ ሰዎች መኖራቸውን ለመረዳት ተችሏል።

ሌላው በእዚህ ክልል ውስጥ የተፈጸመው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በሃዋሳ ከተማ ሀዌላ ክፍለ ከተማ ጋራ ሪቀታ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ ራቴ ዋኤና ቤተሰቦቻቸው ላይ የአካባቢው ነዋሪ የሆኑ ግለሰቦች በአካባቢው የሚገኙ ባለስልጣን ዘመዶቻቸውን መከታ በማድረግ ድብደባ፣ ህገወጥ እስርና የንብረት ውድመት ያደረሱባቸው መሆኑን ለኢሰመጉ የገለጹ ሲሆን አቶ ራቴ ዋኤ ከ አቶ ቲቦ ጤካሞ ቤተሰቦች ጋር በጫት ማሳ የድንበር ግጭት የነበራቸው ሲሆን ይህንን መነሻ በማድረግ የአቶ ራቴ ዋኤ ልጅ የሆነው መቶ አለቃ ተሾመ ራቴ በሀገር መከላከያ ሰራዊት ውስጥ የሚያገለግል ሲሆን እውነትነቱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ልጃቸሁ ሞቷል በማለት ቤተሰቡ እንዲያዝን ማድረጋቸውን እንዲሁም ዛቻና ማስፈራሪያ ስለበዛባቸው ለቱላ ክፍለ ከተማ ፖሊስ ፣ለሲዳማ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን እንዲሁም ለክልሉ ለጸጥታና አስተዳደር ቢሮና ለክልሉ ቅሬታ ሰሚ ያመለከቱ ቢሆንም መልስ ባለማግኘታቸውና ጥበቃ ሳይደረግላቸው በመቅረቱ በቀን 11/5/2014ዓ.ም ከቀኑ 6ሰዓት በቡድን በመደራጀት ቤታቸው ድረስ በመሄድ ጉዳት እንዳደረሱባቸው እንዲሁም በወቅቱ በቀበሌ አመራር ጥረት ተይዘው የነበሩት ሰዎች በመለቀቃቸው በቤተሰቡ ላይ የግድያ ዛቻ እያደረሱባቸው በመሆኑ ከቤታቸው ተፈናቅለው እንደሚገኙ ለኢሰመጉ ገልጸዋል።

ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፡

ኢሰመጉ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በደራሼ ዞን በጋቶ፣ ኩሱሜ እና በአርጉባ ጣናአ አካባቢዎች የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ከ10/11/2015 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 14/11/2015 ዓ.ም ድረስ የምርመራ ባለሙያ በቦታው በመላክ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ምርመራ አካሂዷል። በእዚህም ምርመራ መሰረት 12 (አስራ ሁለት) አባወራዎች ላይ በአጠቃላይ 77 (ሰባ ሰባት) የቤተሰበ አባላት ላይ የመብት ጥሰቶች መፈጸማቸውን ለመረዳት ተችሏል።

በደራሼ ዞን ደራሼ ከተማ አርጉባ ጣናአ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ ከተማ ካሳ በአካባቢ ተደርጎ የነበረ ውን ህዝበ ውሳኔ ለማስገ ምገም ጊዶ ሌ ከተማ በ ነበሩበት ወቅት ማለትም በ1/06/2015 ዓ.ም ከምሽቱ 4፡00 (አራት ሰዓት) አካባቢ ወደ 100 (መቶ) የሚሆኑ የተደረጁ ቡድኖች ወደ ቤታቸው በመሄድ በቤት ውስጥ የነበረውን የ 22 (ሃያ ሁለት) አመት ወጣት የ 12ኛ ክፍል ተማሪ የሆነውን ልጃቸውን አምደወርቅ ከተማን በጦር መሳሪያ ገድለዋል።

ለእዚህ መነሻ ምክንያት የሆነው በቦታው ከነበሩ ምስክሮች እና የሟች ቤተሰቦች ለመረዳት እንደተቻለው አቶ ከተማ ካሳ በቀድሞ ደራሼ ልዩ ወረዳ ግብርና ምክትል ኃላፊና የተፈጥሮ ዘርፍ ኃላፊ የነበሩ ሲሆን በልዩ ወረዳው አርጉባ

ጣናአ ቀበሌ ለደሃ ደሃ የተመደበ የእርዳታ ገንዘብ አላግባብ በአመራሮች መዘረፍ የለበትም በሚል የዐቃቤ ህግ ምስክር በመሆናቸው፣ ከቀድሞ ሰገን አካባቢ መፍረስን ተከትሎ ከደራሼ ልዩ ወረዳ አደረጃጀት ጋር ተያይዞ በጊዜው ከፍተኛ አመራር የነበሩ በመሆናቸው ደራሼን ሸጧል በሚል እና በ2014 ዓ.ም በልዩ ወረዳው ተከስቶ በነበረው ግጭት በጊዜው ተዋቅሮ ለነበረው የምርመራ ቡድን አስተርጓሚ የነበሩ በመሆኑ ቤት ለቤት ልዩ ኃይልን መርቷል በሚል የተሳሳቱ አመለካከቶች እንዲሁም ሰውን ይበላል በሚል የተሳሳተ አመለካከት የ2014 ዓ.ም ማትሪክ ተፈታኝ የነበረውን መጀመሪያ ልጅ የሆነውን አምደወርቅ ከተማን ቤት ድረስ ተደራጅቶ በመሄድ በጦር መሳሪያ እና በተቀጣጣይ ፈንጂ በመወርወር ተማሪ አምደወርቅን በጥይት በመግደል የሚችን ንብረት በመዝረፍና በማቃጠል እንዲሁም የአቶ ከተማ ካሳን ቤት በማቃጠል አውድመዋል፡፡ የተደራጁት ቡድኖች ይህንን ድርጊት ከፈጸሙ በኋላ ወደ አቶ ከተማ ካሳ ታላቅ ወንድም ወደሆኑት ጋዲሴ ካሳ ቤት በመሄድ ከቤታቸው አባረው በማውጣት በቆንጨራ እና በድንጋይ በመደብደብ በአሰቃቂ ሁኔታ ገድለዋል፡፡ ከእዚህም በመቀጠል የአራት አባወራ ቤትና ንብረት አቃጥለዋል፡፡

በተፈጸመው ጥቃት የተገደሉ ሰዎች ምስል፡

	
ስም፡ አቶ ጋዲሴ ካሳ	ስም፡ ተማሪ አምደወርቅ ከተማ
ዕድሜ፡ 55	ዕድሜ፡ 22

የደረሰባቸውን ጉዳት አስመልክቶ አቶ ከተማ ካሳ ለቀድሞ ደራሼ ልዩ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት በ17/06/2015 ዓ.ም፣ ለቀድሞ ደራሼ ልዩ ወረዳ ዋና አስተዳደር፣ ፍትህ ጽ/ቤት እና ምክር ቤት፣ ጸጥታ ጽ/ቤት በ21/10/2015 ዓ.ም እና በ14/09/2015 ዓ.ም ለደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ መንግስት፣ ለክልል ርዕሰ መስተዳደር ቢሮ፣ ለፀጥታ ቢሮ፣ ፖሊስ ኮሚሽን እና ፍትህ ቢሮ አቤቱታቸውን ያስገ ቡ ቢሆን ምንም አይነት ምላሽ ሳያገኙ ይህ መግለጫ እስከተጠናቀረበት ጊ ዜ ድረስ ተፈናቅለው ይገኛሉ፡፡

የወደሙ ንብረቶችና በቀድሞ ደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የደራሼ ልዩ ወረዳ ከተማ ልማት ኮንስትራክሽን ጽ/ቤት የተሰጡ የንብረት ግምቶችን የያዘ ምስል፡

	
የአቶ ከተማ ካሳ የወደመ ንብረት	የወ/ሮ ከበቡሽ ካርዜ የወደመ ንብረት
አጠቃላይ ግምት፡261 884.90 (ሁለት መቶ ስልሳ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ አራት ብር ከዘጠና ሳንቲም	አጠቃላይ ግምት፡ 102 186.25 (አንድ መቶ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ስድስት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም
የወደመው ንብረት፡ ሁለት ቆርቆሮ እና አንድ የሳር ቤት	የወደመው ንብረት፡ አንድ ቆርቆሮ እና ሁለት ሳር ቤት
	
የሟች ጋዲሳ ካሳ የወደመ ንብረት	የአቶ ገረሙ ካሳ የወደመ ንብረት
አጠቃላይ ግምት፡ 65 790.35 (ስልሳ አምስት ሺ ሰባት መቶ ዘጠና ብር ከሰላሳ አምስት ሳንቲም)	አጠቃላይ ግምት፡ 91 037.25 (ዘጠና አንድ ሺ ሰላሳ ሰባት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም)
የወደመው ንብረት፡ አንድ ቆርቆሮ እና ሁለት ሳር ቤት	የወደመ ንብረት፡ አምስት የሳር ቤት

	
የአቶ ደፋሩ አቲሞ የወደመ ንብረት	የአቶ ጴጥሮስ ታኑሌ የወደመ ንብረት
አጠቃላይ ግምት፡ 77 128. 25 (ሰባ ሰባት ሺ አንድ መቶ ሀያ ስምነት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም)	አጠቃላይ ግምት፡ 136 241. 05 (አንድ መቶ ሰላሳ ስድስት ሺ ሁለት መቶ አርባ አንድ ብር ከአምስት ሳንቲም
የወደመው ንብረት፡ አንድ ቆርቆሮ እና ሁለት ሳር ቤት	የወደመው ንብረት፡ አንድ ቆርቆሮ እና አራት ሳር ቤት

በተመሳሳይ ቀን ማለትም በ01/06/2015 ዓ.ም የአቶ ከተማ ካሳን ቤት እና ንብረት ካወደሙ በኋላ እነዚሁ የተደራጁ ቡድኖች በአርጉባ ጣናአ ቀበሌ ውስጥ የሚኖሩ የወ/ሮ አዳነች አጡማ፣ ዘነበች ሰንቶ፣ የአቶ ጅራኔ ጅቦ፣ አዲሱ አጡማ፣ ገረሙ ካሳ፣ የሟች አቶ ጋዲሳ ካሳ አና ወይዘሮ ከበቡሽ ካርዜ ቤት እና ንብረትን በእሳት አቃጥለዋል የተረፈውን ዘርፈዋል፡፡ በእዚህ ቀን የተፈጸመው ጥቃት ከተጎጂዎች በተገኘው መረጃ መሰረት ጥቃት የተፈጸመባቸው ሰዎች የጋሞ ብሔር በመሆናቸው መሆኑን የገለጹ ሲሆን አንድ በቦታው የነበረ ምስክር እንዳስረዳው ከሆነ

> ***“ጥቃቱን ያደረሱት ሰዎች ጥቃቱን ከመፈጸማቸው አንድ ቀን አስቀድሞ በቀን ተሰብስበው ሲጨፍሩና ጋሞን እናጠፋለን እያሉ ሲፎክሩ እና ቤት ንብረት ለማውደምም ህይወት ለማጥፋት እንደተዘጋጁ በይፋ ካሳወቁ በኋላ በ01/06/2015 ዓ.ም ጥቃቱን አድርሰዋል፡፡”*** ሲል አስረድቷል፡፡

ተመሳሳይ ማንነትን መሰረት ያደ ረገ ጥቃት 03/05/2015 ዓ.ም መፈጸሙንና በእዚህም ጥቃት ከተጎጂዎች በተገኘው መረጃ መሰረት የተደራጁ ቡድኖች ጋሞ ከአካባቢያችን መውጣት አለበት እና ከጋሞ ጋር ግንኙነት ያላችሁ ከእዚህ አካባቢ መውጣት አለባችሁ በሚል ቤት ንብረት ማቃጠላቸውን ገልጸዋል፡፡ አንድ ጉዳት የደረሰበት ግለሰብ ስለሁኔታው ሲያስረዳ

> *“ጥር 03 ቀን 2015 ዓ.ም ከምሽቱ 3፡00 ሰዓት አካባቢ በቡድን ሆነው የጋሞ ብሔረሰብ ዝርያ ያለበት ቤት እናጠፋለን እያሉ እየጨፈሩ ወደ ቤታችን መጡ እኔ እናቴ የጋሞ ሰው በመሆኗ ፍርሀት አድሮብኝ ነበር፡፡ ስለፈራሁኝ ጎረቤት ቤት ሄጀ ተደበኩኝ እየጨፈሩ የመጡ ትም ሰዎች ግማሾቹ ቤታችንን ሲያቃጥሉት ግማሾቹ ጥይት እየተኮሱ ሲጨፍሩ ነበር፡፡* ” ሲል አስረድቷል፡፡

በሁለቱም የጊዜዎች ጥቃት የተፈጸመባቸው ሰዎች አቶ ከተማ ካሳ የዐቃቤ ህግ ምስክር በሆኑበት ጉ ዳይ ማለትም ለድሀ ድሀ የቀረበ የሴፍቲ ኔት እርዳታ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያቀረቡትን በመለየት እና ከጋሞ ብሔር የመጡ ናቸው በማለት በመለየት ጥቃት የተፈጸመባቸው ሲሆን በተጨማሪም እነዚህ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ቡዳ ናቸው ሰው ይበላሉ በሚል በጎብረተሰቡ እንዲ ገለሉ የማድረግ ተግባርም የተፈጸመባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ያፈሩት ቤት እና ንብረት ወድሞባቸው ይህ ሪፖርት በሚጠናቀርበት ጊዜ ከፊሎቹ ተፈናቀለው ወደሌላ አካባቢ የተሰደዱ ሲሆን ቀሪዎቹ ደግሞ በፕላስቲክ መጠለያ ውስጥ ተጠልለው ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን ይህንን ጥቃ ት ያደረሱት ቡድኖች ማንነት እየታወቀ እና ተጎጂዎችም በቂ ከሆነ ማስረጃ ጋር ጉዳያቸውን ለፖሊስ ያመለከቱ ቢሆንም ይህንን ድርጊት የፈጸሙ ሰዎች አሁንም በነጻነት እየተንቀሳቀሱ ይልቁንም ተጎጂዎች ላይ ዛቻ እና ማስፈራሪያ እያደረሱ ይገኛሉ፡፡

የወደሙ ንብረቶችና በቀድሞ ደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የደራሼ ልዩ ወረዳ ከተማ ልማት ኮንስትራክሽን ጽ/ቤት የተሰጡ የንብረት ግምቶችን የያዘ ምስል፡

<table>
<tr><td></td><td></td></tr>
<tr><td>የወ/ሮ ዘነቦች ሰንበቶ የወደመ ንብረት</td><td>የአቶ ጂራኔ ጂቦ የወደመ ንብረት</td></tr>
<tr><td>አጠቃላይ ግምት፡ 101 835.70 (አንድ መቶ አንድ ሺ ስምንት መቶ ሰላሳ አምስት ብር ከሰባ ሳንቲም)</td><td>አጠቃላይ ግምት፡ 33 467.35 (ሰላሳ ሶስት ሺህ አራት መተ ስልሳ ሰባት ብረ ከሰላሳ አምስት ሳንቲም)</td></tr>
<tr><td>የወደመው ንብረት፡ ሁለት ቆርቆሮ እና ሁለት ሳር ቤት</td><td>የወደመው ንብረት፡ ሁለት ሳር ቤትየ</td></tr>
</table>

<table>
<tr><td></td><td></td></tr>
</table>

የአቶ አድመሱ አጡማ የወደመ ንብረት	የወ/ሮ አዳነች አጡማ የወደመ ንብረት
አጠቃላይ ግምት፡ 94 458.60 (ዘጠና አራት ሺ አራት መቶ ሀምሳ ስምንት ብር ከስልሳ ሳንቲም)	አጠቃላይ ግምት፡ 45 360.15 (አርባ አምስት ሺ ሶስት መቶ ስልሳ ብር ከአስራ አምስት ሳንቲም)
የወደመው ንብረት፡ አንድ ቆርቆሮ እና አንድ የሳር ቤት	የወደመው ንብረት፡ ሶስት የሳር ቤት

በተመሳሳይ ካኖላ ከበደ ኩሴ የተባለ ግለሰብ ሚያዚያ 14 ቀን 2015 ዓ.ም በደራሼ ዞን ጋቶ መንደር 1 ቀጠና 9 ውስጥ ለረዥም ጊዜ ከጋቶ ኩስሜ በነበረ ግጭት ምክንያት ተፈናቅሎ ፉጨጫ እየኖረ የነበረ ሲሆን በቀድሞ ደራሼ ልዩ ወረዳ አስተዳደር ከህብረተሰቡ ጋር ባደረጉት ውይይት በአካባቢው እርቅ ተደርጎ ተፈናቃዮች ወደ መኖሪያቸው እንዲመለሱ በተደረገው ስምምነት ሚያዚያ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ወደቀድሞ መኖሪያ መንደሩ ተመልሶ እየተዘዋወረ ከህብረተሰ ብ ጋር እየተገናኘ ባለበት ወቅት በአካባቢው ባለ የፖሊስ አባል ተገድሏል፡፡ ስለድርጊቱ በቦታው የነበረ ሰው ሲያስረዳ

> ***"ሟች የእንኳን ደህና መጣህ ሰላምታ ልውውጥ ከህብረተሰቡ ጋር እያደረገ ባለበት ነው ገዳይ ከየት እንደመጣ ሳይታወቅ ወደ ሰማይ ጥይት እየተኮሰ ወደ ተሰበሰበው ህብረተሰብ ሲጠጋ ሁሉም ከጥይት ለማምለጥ ሲሸሽ ሟች በአካባቢው በነበረች ነዋሪ ቤት ውስጥ ቢደበቅም የተደበቀበት ቤት ባለቤት ለገዳይ ባደረገቸው ጥቆማ ምክንያት ገዳይ ከግብረ አበሮቹ ጋር በመሆን ሟች አቶ ካኖላ ከበደ ኩሴን ይዞ ከቤት ውስጥ በማውጣት በያዘው መሳሪያ በጥይት መቶ ገድሎታል"*** ሲል አስረድቷል

በአካባቢው የነበረው ማህበረሰብ እና ቤተሰብ የሟች ካኖላ ከበደ ኩሴን አስክሬን እንዳይቀብሩ ተከልክለው የነበረ ሲሆን በድብቅ በአቅራቢያ የነበረ ጫካ ውስጥ ቀብረውታል፡፡ ይህንንም ጉዳይ አሰመልክቶ ቤተሰቦች ለክልል ፍትህ ቢሮ፣ ለፌደራል ፍትህ ቢሮ፣ ለክልል ፖሊስ መምሪያ ያመለከቱ ቢሆንም ጥቃት አድራሾች ማንነት እየታወቀ ምንም አይነት ፍትህም ሆነ ለወደመባቸው ንብረት ካሳ ለተጎጂዎች አልተሰጠም፡፡



ስም፡ ካኖላ ከበደ ኩሴ

ዕድሜ፡ 35

በተጨማሪም በእዚሁ ክልል ኮንሶ ዞን ደራሼ ወረዳ ጋቶ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ ገረሱ ከበደ ኩሴ ጥቅምት 28ቀን 2015ዓ.ም የሚሊሻ አባላት ፣ፖሊስ እና የቀበሌ አስተዳደር ቤት ድረስ በመምጣት ከእኛ እየወሰድከ ከጋቶ ተፈናቅለው ፉጨሜ ላይ ለሚገኙ ተፈናቃዮች መረጃ እየሰጠህ ነው በማለት ባደረሱበት ከፍተኛ የሆነ ድብደባ በተለያዩ ሆስፒታሎች ህክምና ማድረግ ቢችልም ጥቅምት 18 ቀን 2016ዓ.ም ህይወቱ ሊያልፍ መቻሉን ለኢሰመጉ በቀረቡለት አቤቱታ ለማወቅ የቻለ ሲሆን በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት በኮንሶ ዞን ካራት ከተማ አስተዳደር ካራት ጤና ጣቢያ በቀን 18/3/2016ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር መ51/0245/16ዓ.ም በሰጠው ማስረጃ መሰረት አቶ ገረሱ ከበደ ኩሴ በጤና ጣቢያቸው ሲረዱ መቆየታቸውንና በጊዜው ድብደባ ደርሶባቸው እንደነበር የሚያሳይ ምልክቶች መኖራቸውንና የደረሰባቸው ጉዳት ከጤና ተቋሙ በላይ የነበረ በመሆኑ ወደ አርባምንጭ ሆስፒታል መላካቸውን እና በዚያው ህይወታቸው ማለፉን ገልጸዋል።

በመጨረሻም በቀድሞ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በአሁኑ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አማሮ ዞን ቡኒት ቀበሌ 5979 የሚሆኑ አባዎራዎች የአማራ ብሔር ተወላጆች በጣሊያን ጊዜ ወላጆቻቸው ላደረጉት ከፍተኛ ተጋድሎ የደም ካሳ በማለት መንግስት በዚህ ቀበሌ አስፍሯቸው ከ 57 አመት በላይ በዙሪያው ከሚገኙ የኮሬ፣የቡርጂ፣የኮንሶ፣ የደራሼ፣የአሌ ፣የኦሮሞና ሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ተጋብተውና ተዋልደው ቤት ንብረት አፍርተው ሲኖሩ የነበረ መሆኑን ነገር ግን ከህዳር ወር 2011ዓ.ም ጀምሮ በብሔራቸው ምክንያት ሀገራችሁ እዚህ አይደለም ውጡልን መባላቸውን እና ቤታቸው እና ሙሉ ንብረታቸው በመቃጠሉ ከአካባቢው ተፈናቅለው ወደ ተለያዩ አካባቢዎች ተበታትነው የቀን ስራ ሰርተው ልጆቻቸውን ማስተዳደር እና መመገብ በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ መሆናቸውን ለኢሰመጉ ገልጸዋል።

ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፡

በእስልመና እምነት ተከታዮች ላይ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፡

በአዲስ አበበ ከተማ አስተዳደርና በኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ አስተዳደር ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች በ2015 ዓ.ም በተለያዩ ወቅቶች የቤት ፈረሳ እንቅስቃሴዎች እንደነበሩ እና ይህም እንቅስቃሴ በተወሰነ መልኩ አሁንም መቀጠሉ ይታወቃል። ይህም የፈረሳ እንቅስቃሴ የሃይማኖት ተቋማትንም የጨመረ ሲሆን ኢሰመጉ ከኦሮሚያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክርቤት በቃል ባገኘው መረጃ መሰረት ወደ 19 የሚጠጉ መስጊዶች መፍረሳቸውን ለመረዳት ተችሏል።

በተጨማሪም የህንን የመስጊዶችን የማፍረስ እንቅስቃሴ ተከትሎ በአዲስ አበባ አንወዋር መስጊድ በ18/09/2015 ዓ.ም እና 25/09/2015 ዓ.ም በታላቁ አንዋር መስጊድ የጁምዓ ስግደት ከተፈጸመ በኋላ ድርጊቱን በመቃወም ሰልፍ በወጡ የዕምነቱ ተከታዮች ላይ የመንግስት የጸጥታ ኃይሎች በወሰዱት ተመጣጣኝ ያልሆነ የሀይል እርምጃ ምክንያት የሰዎች

ህይወት ማለፉን፣ የአካል ጉዳት መድረሱን፣ ንብረት መውደሙን እና በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ላይ እስራት ተፈጽሞ የነበሩ መሆኑን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

በጋዜጠኞች እና በፖለቲካ ፓርቲ አባላትና አመራሮች ላይ የተፈጸሙ እስሮች፡

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 6/2015 ከታወጀበት ጊዜ ጀምሮ እና አዋጁ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከመጽደቁ በፊት በአዲስ አበባ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ እና በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ውስጥ በሚገኙ አካባቢዎች በርካታ እስሮች እየተፈጸሙ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ እስሮች አብዛኞቹ በሚባል ደረጃ የህግ ስነ ስርዓትን ያልተከተሉ ሲሆኑ የሚታሰሩ ሰዎችም በተገቢው ሰዓት ፍርድ ቤት እንደማይቀርቡ፣ ተይዘው የሚወደቡት ሁኔታ የአስገድዶ መሰወር (እገታ) ባህሪ ያለው መሆኑ፣ ምንም እንኳን በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት የተጠርጣሪዎች መብቶች ገደብ የማይጣልበት ቢሆንም እነዚህ መብቶች በሞላ በሚባል ደረጃ እንደማይከበሩ ለመመልከት የተቻለ ሲሆን ምንም እንኳን ይህ አዋጅ መርማሪ ቦርድ ያለው ቢሆንም ይህ ቦርድ የታሰሩ ሰዎችን ስም ዝርዝርና ያሉበት ቦታ ይፋ ሳያደርግ ቆይቷል፡፡

ከተፈጸሙት እስሮች መካከልም ሀምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የሆኑት የተከበሩ አቶ ክርስቲያን ታደለ እና የአዲስ አበባ ምክር ቤት አባል የሆኑት የተከበሩ ዶ/ር ካሳ ተሻገር ያለመከሰስ መብታቸው ሳይነሳ በፖሊስ ተይዘው በፌደራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ እንደሚገኙ፣ በተመሳሳይ የአማራ ክልል ምክር ቤት አባል የሆኑት የተከበሩ አቶ ዮሐንስ ቧያሌው ያለመከሰስ መብታቸው ሳይነሳ ከታሰሩት መካከል ይገኙበታል፣ የአልፋ ሚዲያ የበይነ መረብ መገናኛ ብዙኃን መስራች እና ባለቤት የሆነው ጋዜጠኛ በቃሉ አላምረው ሀምሌ 30 ቀን 2015 ዓ.ም በፖሊሶች መያዙን፣ የጄነራል ተፈራ ማሞ ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ መነን ኃይሌ ነሀሴ 3 ቀን 2015 ዓ.ም በፖሊሶች የተያዙ ሲሆን የተያዙበት ምክንያትም ከእዚህ ቀደም በማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ ባስተላለፏቸው መልእክቶች እንደሆነ፣ ከእነዚህ እስሮች በተጨማሪ በአዲስ አበባ ከተማ የጅምላ እስሮች እየተፈጸሙ ሲሆን ይህም የጅምላ እስር ከወቅታዊ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በሚል እንደሚፈጸም፣ የተያዙ ሰዎች ፍርድ ቤት እንደማይቀርቡ፣ ቤተሰቦች ታሳሪዎቹ ያሉበትን ማወቅ እንዳልቻሉና አንዳንድ ትምህርት ቤቶች እንደ ማቆያነት ጥቅም ላይ እየዋሉ እንደነበር ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡

ኢሰመጉ ከታሳሪ ቤተሰቦች ባገኛቸው መረጃዎች በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በአዲስ አበባ ፖሊስና በፌደራል ፖሊስ አንዳንዶቹም የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸውን መኪናዎች ጭምር በመጠቀም ከተያዙ በኋላ ወደ አፋር ክልል አዋሽ አርባ እንደሚወሰዱ ለመረዳት ችሏል፡፡

ሀምሌ 30 ቀን 2015 የአልፋ ሚዲያ የበይነ መረብ መገናኛ ብዙኃን መስራች እና ባለቤት የሆነው ጋዜጠኛ በቃሉ አላምረው እና ነሀሴ 04 ቀን 2015 ዓ.ም በፌደራል ፖሊስ አባላት የተያዘው ጋዜጠኛ አባይ ዘውዱ ይገኙበታል፡ ፡ ጋዜጠኛ አባይ ዘውዱን አስመልክቶ በተሰበሰበ መረጃ መሰረት ጋዜጠኛው በ15/12/2015 ዓ.ም ወደ አዋሽ አርባ ተወስዶ እንደነበር ቤተሰቦች ከተለያዩ ምንጮች እንደሰሙ ነገር ግን ማረጋገጥ እንዳልቻሉ፣ ጋዜጠኛ

በቃሉ አላምረው ግን ለረጅም ጊዜ ድረስ ያለበትን ማወቅ እንዳልቻሉ ኢሰመጉ ከሰበሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

በሴቶች ላይ የተፈጸሙ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች፡

በኢትየጵያ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የተለያዩ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች በተለያዩ አካባቢዎች ሲፈጸሙ ይስተዋላሉ፡፡ የእነዚህ ጥቃቶች በጊዜ ሂደት መጨመር ለጉዳዩ ተገቢ በቂ ትኩረት እና ዘላቂ መፍትሄ አለመሰጠቱን ማሳያ ምልክት ነው፡፡ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ሴቶች በማህበረሰብ ወስጥ ውጤታማ የሆነ እኩል ተሳትፎ እንዳይኖራቸውና የደህንነት ስጋት እንዲሰማቸው ከፍተኛ አስተዋጾ ያደርጋሉ፡፡ በተለይም በአገሪቱ በተደጋጋሚ በሚነሱ ግጭቶችና በታጣቂዎች በሚፈጸሙ ጥቃቶች ምክንያትና ሴቶች ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭ በመሆናቸው የተነሳ ልዩ ልዩ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እየደረሱባቸው ይገኛሉ፡፡

በሰሜኑ ኢትዮጵያ ክፍል ተነስቶ የነበረው የትጥቅ ግጭት በትግራይ፣ በአማራ እና በአፋር ክልሎች ውስጥ በርካታ ሴቶች ላይ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እንዲፈጸሙ ምክንያት የነበረ ሲሆን በመቀጠልም በአማራ ክልል የተነሳውና በእዚህ መደበኛ መግለጫ ላይ ከፍላ አንድ እና ክፍል ሁለት በሚል ርዕስ ስር የቀረበው ግኝት በጥቂቱ እንደሚያሳየው በርካታ ሴቶች በእዚህ ግጭት ምክንያት ጾታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች ተጋላጭ እንዲሆኑ ምክንያት እየሆነ ይገኛል፡ :

በእዚህ ርዕስ ሌላው ትኩረት ለሰጠው የሚገባው ሀሳብ ደግሞ ተደራራቢ የሆነ ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭ የሆኑ ሴቶች ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ማለት እንደ ሴት አካል ጉዳተኞች፣ የአገር ውስጥ ተፈናቃይ ሴቶች፣ ሴት ህጻናት፣ አረጋውያን ሴቶች፣ የአእምሮ ህመም ያለባቸው ሴቶች እንዲሁም ከተዘረዘሩት ውስጥ ከሁለት በላይ የሆነ ተጋላጭነት ያለባቸው ሴቶች የሚገኙበት ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ለእነዚህ ሴቶች ልዩ ትኩረት ባለመሰጠቱ ምክንያት ለከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችና ለጾታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች ሲጋለጡ ይታያል፡፡

ይህ መደበኛ መግለጫ በሚሸፍነው የጊዜ ወሰን ውስጥ ልዩ ልዩ የሆኑ መጠነ ሰፊ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች የተፈጸሙ ሲሆን አንዱ ከላይ እንደተጠቀሰው በአማራ ክልል ያለውን ግጭት ተከትሎ በግጭቱ እየተሳተፉ ባሉ አካላት እየተፈጸመ ያለ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ነው፡፡

ከአዚህ በታች ደግሞ የተወሰኑ በሴቶች ላይ የደረሱ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን የጉዳዩን አሳሳቢነት ለማሳያነት ያክል የሚቀርቡ ይሆነል፡፡ ኢሰመጉ በእዚህ መደበኛ መግለጫ ላይ ያቀረባቸው ጥሰቶች የተዘረዘሩት ብቻ ሳይሆኑ ለማሳያነት ያክል የቀረቡ መሆናቸውን አንባቢዎች እንዲረዱ ያሳስባል፡፡

በትግራይ ክልል ዓዲ ጉደም ከተማ መስከረም 28 ቀን 2016 ዓ.ም ኪሮስ ሕሉፍ የምትባል ሴት በትዳር አጋርዋ በጠጣለባት ቦንብ ምክንያት ተገድላች፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን ወንበራ ወረዳ ታህሳስ 20 ቀን 2016 ዓ.ም አንድ የ17 ዓመት ተማሪ የ5 ዓመት ህፃን ልጅን አስገድዶ የደፈረ ሲሆን የወረዳው ፍርድ ቤትም በስድስት ወር

እስራት እንዲቀጣ ፈርዶበታል፡፡ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ኮሬ ዞን ኬሌ 01 ቀበሌ መጋቢት 2015 ዓ.ም አንድ የ42 ዓመት አባት የ8ኛ ክፍል እና የ13 አመት ታዳጊ የሆነች ልጃቸውን አስገድደው የደፈሩ ሲሆን የዞኑ ፍርድ ቤትም የ10 ዓመት ቅጣት ወስኖባቸዋል፡፡

በሐዋሳ ከተማ የዳሸን ባንክ ሀዋሳ ዋርካ ቅርንጫፍ ሰራተኛ የሆነችው ወይዘሪት ፀጋ በላቸው በተደጋጋሚ ዛቻ እና ማስፈራራት ሲፈጸምባት ከቆየ በኋላ ግንቦት 15 ቀን 2015 ዓ.ም ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት አካባቢ በተለምዶው አሮጌው መነሃሪያ ከሚባል ቦታ በወቅቱ የሀዋሳ ከተማ ከንቲባ የግል ጠባቂ በነበረው ተጠርጣሪ ኮንስታብል የኋላመብራት ወልደማሪያም መጠለፏንና ወይዘሪት ፀጋ በላቸው ከዘጠኝ ቀናት በኃላ ከታገተችበት ነፃ ወጥታ ከቤተሰቦቿ ጋር መቀላቀሏን ለማወቅ ተችሎ የነበረ ሲሆን ተጠርጣሪው ከቆይታ በኋላ በፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋለ ሲሆን ተከሳሹ ላይም በመጀመሪያ የ16 ዓመት ጽኑ እስራት እንደተፈረደበት ነገር ግን በይግባኝ ፍርዱ ወደ 10 ዓመት እስራት እንደተቀነሰ ለመረዳት ተችሏል።

በምስራቅ ሀረጌ ዞን ኮምቦልቻ ወረዳ ቀበሌ 02 ነዋሪ የነበረችው ወ/ሮ አያንቱ ሙስጠፋ ጥር 15 ቀን 2016 ዓ.ም ማታ ላይ በገዛ የትዳር አጋርዋ ከልጆችዋ ጋር በተኛችበት በተፈጸመባት የአሲድ ጥቃት ምክንያት 3ኛ ደረጃ የሆነ ቃጠሎ የደረሰባት ሲሆን የአሲድ ጥቃቱ በአይኗ፣ በጭንቅላቷ፣ ፊቷ ላይ ፣ ደረቷ ፊት ፣ እጇ ላይ ጉዳት አድርሷል። በእዚህም ጥቃት ምክንያት ወ/ሮ አያንቱ ሙስጠፋ የቀኝ አይኗ በደረሰበት ከፍተኛ ጉዳት ሊጠፋ ችሏል፡፡ በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የነበረችው አብቅየለሽ ወርቁ ጥር 4 ቀን 2016 ዓ.ም ጦር ኃይሎች አካባቢ የስፖርት እንቅስቃሴ በምትሰራበት ቦታ ውስጥ አሰልጣኟ በነበረ ግለሰብ በአሰቃቂ ሁኔታ ብዙ ቦታዎች ተወግታ የተገደለች ሲሆን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው የግድያው ምክንያት ለምን ያለፈቃዴ ምስሌን በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ለቀቅሽ የሚል እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ጸታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች በጣም ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ሲሆን በአገሪቱ በሁሉም አካባቢዎች በሚባል ደረጃ እነዚህ ጥቃቶች በአሳሳቢ ደረጃ እየተበራከቱ ይገኛሉ፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይየጠለፋ ድርጊቶች እየተበራከቱ ያሉ ሲሆን ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ ሽማግሌዎችን በመላክ የተጠላፊ ቤተሰቦችን የማሳመን ስራ እየተለመደ እየመጣ ያለ ሆኗል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትና ሌሎችም ጥቃቶች እንደሚያሳዩት በርካታዎቹ የሚፈጸሙት የቅርብ በሆኑና ሴቶቹ በሚያምኗቸው ሰዎች ሲሆን ይህም የጉዳዩን አስከፊነት ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት እጅግ ዝቅተኛ የሆነ ቅጣት ሌሎች ሰዎች ድርጊቱን እንዳይፈጸሙ የሚከላከል ሊሆን ሳይችል ቀርቷል፡፡

በኢሰመጉ ላይ እየተፈጸሙ ያሉ ጥቃቶች እና ከፍተኛ ጫናዎች፡

ኢሰመጉ ከተመሰረተበት 1984 ዓ.ም ጀምሮ በግንባር ቀደምትነት የሰብዓዊ መብቶች ስራዎችን ሲሰራ የቆየ ተቋም ነው፡ ፡ በእስካሁኑ የሰብዓዊ መብቶች የማስከበር ስራው ድርጅቱ እንደ ድርጅት እንዲሁም ሰራተኞቹ እና አባላቶቹ ላይ ልዩ

ልዩ ጥቃቶች እና ከፍተኛ ጫናዎች ሲደርሱበት ቆይተዋል አሁንም በመድረስ ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ልዩ ልዩ ጥቃቶች እና ከፍተኛ ጫናዎች በአገሪቱ ያለው የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ እና የሰብዓዊ መብቶች ስራዎች ምን ያህል አስጊ ደረጃ ላይ እንደደረሰ በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ መግለጫ ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በኢሰመጉ ላይ ያለማቋረጥ መጠናቸው እየጨመሩ የሄዱ በመንግስት የሚፈጸሙ ጥቃቶች እና ከፍተኛ ጫናዎችን ከቅርብ ጊዜው በመጀመር በዝርዝር እንደሚከተለው ያቀርባል፡፡

ከእዚህ በታች በተዘረዘሩት ጥቃቶችና ከፍተኛ ጫናዎች ግድያ ከተፈጸመባቸው በስተቀረተጎጂዎችን ለተጨማሪ ጥቃት እና ጫና ላለመዳረግ ሲባል ስማቸውን ከመግለጽ ተቆጥበናል፡፡

- መጋቢት 28 ቀን 2016 ዓ.ም ከሰዓት 10፡30 ሰዓት አካባቢ ሲቪል የለበሱ ሁለት የመንግስት የደኅንነት አባላት የኢሰመጉ የስራ ኃላፊ ቤት በመሄድ ዛቻ እና ማስፈራራት የፈጸሙ ሲሆን እነዚህ የደኅንነት አባላት አመራሮቹ የሚሰሩትን ስራ እንደሚያውቁ፣ እየተከታተሏቸው እንደሆነና ከሚሰሩት የሰብዓዊ መብቶች የማስከበር ስራዎች እንዲቆጠቡና መንግስትን በሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ከመወንጀል እንዲቆጠቡ ካልሆነ ግን ዋጋ እንደሚከፍሉ ያሰጠነቀቁ ሲሆን ይህ ድርጊት የመጀመሪያ ሳይሆን ከእዚህ ቀደም መጋቢት 09 ቀን 2015 ዓ.ም ተመሳሳይ ድርጊት በእዚሁ የኢሰመጉ የስራ ኃላፊ ላይ ተፈጽሟል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ ጊዜያት ስልክ በመደወል የማስፈራራት እንዲሁም ሚያዚያ 5 ቀን 2016 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት አካባቢ የኢሰመጉ የስራ ኃላፊን በመኪና በመከታተልና ፎቶግራፍ በማንሳት በሚሰሩት የሰብዓዊ መብቶች ስራዎች እና በኢሰመጉ አመራርነታቸው ምክንያት ብቻ ክትትል ሲደረግ ነበር ይህም ድርጊት በተደጋጋሚ ሲፈጸም የነበረና አሁንም በመቀጠል ላይ ያለ ነው፣
- የኢሰመጉ ሰሜን ኢትዮጵያ ቀጣና ባህርዳር ጽ/ቤት ሰራተኛ ህዳር 05 ቀን 2016 ዓ.ም በአማራ ክልል ውስጥ ያለውን ግጭት ተከትሎ የደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የምርመራ ስራ አከናውኖ ከጨረሰ በኋላ ምሽት ላይ በመኖሪያ ቤቱ አካባቢ በታጠቁ ሶስት የመንግስት የጸጥታ አካላት ልብስ በለበሱ ሰዎች ጥቃት ደርሶበታል፡፡ የጥቃቱን ዝርዝር ለማስረዳት ሶስት የታጠቁ ሰዎች መሳሪያቸውን በመተኮስ ከከበቡት በኋላ ራሱን መከላከል በማይችልበተ ሁኔታ ውስጥ ባለበት ሰዓት ጭንቅላቱን በመምታት ራሱን ስቶ ሲወድቅ ይዞት የነበረውን ተንቀሳቃሽ ስልክ፣ ወደ 10 ገጽ የሚጠጋ የምርመራ ስራ ሪፖርት ሰነድ የያዘ ፍላሽ ዲስክ፣ የድርጅቱን (የኢሰመጉ) የአባልነት እና የሰራተኝነት መታወቂያውን ወስደውበታል፡፡ እንዲሁም ጥቃቱ በደረሰበት ወቅት ጥቃቱን ያደረሱት ሰዎች “የምትሰራውን ስራ እናውቃለን” በማለት የተለያዩ ስድቦች እና ማስፈራሪያዎችን አድርሰውበታል፣
- ሚያዚያ 17 እስከ 19 ቀን 2015 ዓ.ም በአዳማ ከተማ ተዘጋጅቶ በነበረ የህዝብ ተጠየቅ (Public Inquiry) ላይ ኢሰመጉ ተካፋይ የነበረ ሲሆን በእዚህ የውይይት መድረክ ላይ ተሳታፊና በወቅቱ የኦሮሚያ የፖሊስ እና ፍትህ ቢሮ ኃላፊዎች የነበሩ ያለ ህግ አግባብ ታህሳስ 27 ቀን 2015 ዓ.ም ታስረው የነበሩ እና ጥር 04 ቀን 2015 ዓ.ም በዋስ የተለቀቁትን አራት የኢሰመጉ ሰራተኞቸን ጉዳይ እንዳልዘጉት፣ በማንኛውም ጊዜም እስር

ሊፈጽሙ እንደሚችሉና የኢሰመጉን ጉዳይ በቅርበት እንደሚከታተሉት በመግለጽ ምንም እንኳን ኢሰመጉ በህግ አግባብ ተመዝግቦ ላለፉት 32 ዓመታት የሰብዓዊ መብቶች ስራዎችን ሲሰራ የቆየ ተቋም ቢሆንም በከልሉ የሚያከናውናቸውን የሰብዓዊ መብቶች የምርመራ ስራዎች የመስራት ፈቃድ እንደሌለው ማስፈራሪያ አዘል መልእክት አስተላልፈዋል፡፡

- የኢሰመጉ የደቡብ ኢትዮጵያ ቀጣና አርባምንጭ ጽ/ቤት አባላት የሆኑት ሁለት ግለሰቦች ከ06/07/2015 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ጊዜዎች ያለምንም በቂ ምክንያት የኢሰመጉ አባላት በመሆናቸው፣ በአካባቢያቸው በመንግስት አስተዳደር አባላት የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በመቃወማቸውና ለኢሰመጉ መረጃዎችን ታቀርባላችሁ በሚል ምክንያት በተደጋጋሚ ጊዜ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ለህገ ወጥ እስራት ተዳርገው ቆይተዋል፡፡ እነዚህ ሁለት የኢሰመጉ አባላት በተደጋጋሚ ጊዜ በህገ ወጥ እስር ጫና የደረሰባቸው ሲሆን በእዚህም ውስጥ የአካባቢው የጸጥታ አካላት እና የፍትህ አካላት በትብብር በመሆን ፍትህ እንዳያገኙ ሲያደርጓቸው ቆይተዋል፣
- የካቲት 4 ቀን 2015 ዓ.ም በኢሰመጉ የምርመራ ክፍል ላይ የቢሮ ሰበራ ተፈጽሞ በክፍል ውስጥ ከነበሩ ንብረቶች የክፍሉ ኃላፊን መሳቢያ በመስበር አንድ ላፕቶፕ ኮምፒውተር ሆን ተብሎ የተወሰደ ሲሆን ከእዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በጊዜው የሰበራውን ድርጊት ምንም እንኳን ኢሰመጉ እራሱ የተፈጸመበትን የቢሮ ሰበራ ለፖሊስ ያመለከተ ቢሆንም የፖሊስ የምርመራ ሂደት ከመዘግየቱ ባሻገር በቢሮው ውስጥ ይሰሩ ከነበሩት ውስጥ ሶስት የምርመራ ክፍል ሰራተኞች መጋቢት 18 ቀን 2015 ዓ.ም ጉዳዩን በያዘው የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ለገሀር አካባቢ ፖሊስ ጣቢያ ለጥያቄ እንፈልጋችኋለን ተብለው በሄዱበት ታስረው መጋቢት 19 ቀን 2015 ዓ.ም ፍርድ ቤት የቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በእዚህ ጉዳይ ላይ በፖሊስ በኩል ትክክለኛ እና በቂ የሆነ የምርመራ ስራ አለመሰራቱን በመግለጽ ሰራተኞቹ በገንዘብ ዋስ ሊለቀቁ ችለዋል፡፡ ከእዚህ ቀደም በኢሰመጉ ስራ ኃላፊ ላይ የስልክ ነጠቃ የተፈጸመ ሲሆን የተነጠቀውን ስልክ በመጠቀም የስራ ኃላፊውንና ኢሰመጉን የማይወክል ጉዳይ በትዊተር ገጽ(X) እና ሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ተለጥፎ የነበረ መሆኑ ይታወሳል፡ ፡ እነዚህ ንብረቶች ይህ መግለጫ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ ባለመገኘታቸውና በውስጣቸው የሚገኙ ሌሎች መረጃዎችን ከኢሰመጉ ዓላማ ውጪ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ኢሰመጉን በእጅጉ ያሳስበዋል፡፡
- በኢሰመጉ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጣና ጋምቤላ ጽ/ቤት አንድ ሰራተኛ እና ሁለት የስራ አስፈጻሚ አባላቶቹ ላይ በተከታታይ በጸጥታና በተለያዩ አካላት ይደርሱ የነበሩ ዛቻዎችንና ማስፈራሪያዎችን ተከትሎ ኢሰመጉ ለሰራተኞቹ ደኅንነት ሲል በታህሳስ 08 ቀን 2015 ዓ.ም ወደ ሌላ ቦታ ለማዘዋወር ተገዶ ነበር፣
- በ2015 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ አዲስ በተመሰረተው ሸገር ከተማ አስተዳደር ውስጥ በነበረው ቤት የማፍረስ እና የማፈናቀል እንቅስቃሴ ቤቶቻቸው የፈረሱባቸው ግለሰቦች ለኢሰመጉ ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት ታህሳስ 27 ቀን 2015 ዓ.ም የቀረበውን አቤቱታ ለማጣራት በኢሰመጉ የተላኩ አራት የኢሰመጉ ሰራተኞች በኦሮሚያ ፖሊስ ከህግ አግባብ ውጪ ታህሳስ 27 ቀን 2015 ዓ.ም ተይዘው ለተወሰኑ

ሰዓታት ያሉበት ሳይታወቅ ከቆየ በኋላ ዘግይቶ ለኢሰመጉ በደረሰ ጥቆማ መሰረት በሸገር ከተማ አስተዳደር ገላን ጉዳ ክፍለ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ መታሰራቸው የታወቀ ሲሆን ከስምንት ቀን የእስር ቆይታ በኋላ የተለያዩ አገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማት ባደረጉት ውትወታ ምክንያት ጥር 04 ቀን 2015 ዓ.ም በገንዘብ ዋስ ሊለቀቁ ችለዋል፣

- ኢሰመጉ ታህሳስ 04 ቀን 2015 ዓ.ም "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚነሱ ተቃውሞና አለመግባባቶች መንግስት በቂ ትኩረት በመስጠት ጉዳዩ ከቁጥጥር ውጭ ከመውጣቱ በፊት አስቸኳይ ዘላቂ መፍትሔ ይስጥ!" በሚል ርዕስ ያወጣውን መግለጫ ተከትሎ የአዲስ አበባ ፖሊስ አባላት ወደ ኢሰመጉ ዋና ጽ/ቤት በመምጣት የኢሰመጉ የስራ ኃላፊዎች ላይ ዛቻ እና ማስፈራሪያ በመፈጸም ወደፊት የተለያዩ እርምጃዎችን እንደሚወስዱ ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ ኢሰመጉ ግንቦት 2015 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ በኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ አስተዳደር እና አዳማ ከተማ ውስጥ ካሉ የቤት የማፍረስና የአስገድዶ ማፈናቀል እንቅስቃሴዎች ጋር ተያይዞ ያዘጋጀውን 153ኛ ልዩ መግለጫን ተከትሎ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮሚኒኬሽን ቢሮ ለአዲስ አበባ ፍትህ ቢሮ ኢሰመጉ እንዲከሰስ በደብዳቤ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት ህዝብን ከህዝብ ለማጋጨት በመሞከርና ህዝብን ከመንግስት ለማጋጨት በመሞከር በሚል የተለያዩ ተገቢ ያልሆኑ ክሶችን ለመመስረት እንቅስቃሴ የነበረ ሲሆን ኢሰመጉም ተገቢውን የጽሁፍ ማብራሪያ አቅርቧል፡፡ ይህ ድርጊት ኢሰመጉ የሚሰራቸው የሰብዓዊ መብቶችን የማስከበር ስራዎች ላይ የክስ ማስፈራሪያዎችን በማቅረብ ከፍተኛ ጫና የሚያደርስ ሲሆን እንዲህ አይነት ድርጊት ከእዚህ ቀደም በተደጋጋሚ የተፈጸሙና አላማውም ድርጅቱ ምንም አይነት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን አስመልክቶ መግለጫዎችን እንዳያወጣ፣ በተቋቋመለት አላማ መሰረት የሰብዓዊ መብቶችን የማስከበር ስራውን በነጻነት እንዳይሰራና በቀጣይ የሚሰሩ ስራዎች ላይም ስጋት የሚፈጥርና ዋስትና የሚያሳጣ ተግባር ነው፣
- ህዳር 23 ቀን 2015 ዓ.ም አዲስ አበባ በሚገኘው የኢሰመጉ ማዕከላዊ ቀጠና ጽ/ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ከመጡ 28 አቤቱታ አቅራቢዎች መካከል 22ቱን አቤቱታ አቅርበው እንደወጡ በመንግስት የጸጥታ አካላት ከህግ አግባብ ውጭ ለቀናት ታስረው ተለቀዋል፡፡ ይህም አቤቱታ አቅራቢዎች በነጻነት አቤቱታቸውን እንዳያቀርቡ ስጋት የሚፈጥር እና ኢሰመጉ ስራ ላይ መሰናክል እየሆነ ያለ ድርጊት ነው፣
- ኢሰመጉ በተደጋጋሚ በሚያወጣቸው መደበኛ፣ ልዩ እና አስቸኳይ መግለጫዎች ላይ ከአቤቱታ አቅራቢዎች፣ ከምስክሮች እና ከተለያዩ ቦታዎች ያሰባሰባቸውን መረጃዎች ሚዛናዊ ለማድረ የተለያዩ የሚመለከታቸውን የመንግስት ተቋማት መረጃ እንዲያጋሩን በደብዳቤ የሚጠይቅ ሲሆን በደብዳቤ የሚጠየቁ አብዛኞቹ የመንግስት ተቋማት መረጃዎችን የማጋራት ግዴታና ኃላፊነት ያለባቸው ቢሆንም መረጃዎችን ለማጋራት ፈቃደኞች አለመሆናቸውና ስራውን በሚሰሩ የኢሰመጉ ሰራተኞች ላይ የሚፈጽሟቸው ማንገላታቶች፣ ዛቻ እና ማስፈራሪያዎች በኢሰመጉ ስራዎች ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እየፈጠረ የሚገኝ ሲሆን በተመሳሳይ ኢሰመጉ

በሚያደርገው የችሎት ክትትል ላይ የሚደረጉ አላገባብ ክልከላዎች በተደጋጋሚ እየተፈጸሙ ይገኛሉ፡፡ ይህ ድርጊት ስልታዊ በሆነ መንገድ ድርጅቱ ስራውን እንዳይሰራ የማድረግ እንቅስቃሴ ነው፣

- የኢሰመጉ የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ከሀገር ውጪ ከሚያደርጓቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች የስራ ዝግጅቶና ስብሰባዎች በሚመለሱበት ወቅት በመንግስት የጸጥታ አካላት ያለአግባብ ማዋከብ፣ ማንገላታትና መከታተል በተደጋጋሚ ጊዜ በመፈጸም ላይ ይገኛል፣
- በ2001 ዓ.ም ወጥቶ የነበረው እና አሁን የተሻሻለው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራትን ለመመዝገብና ለማስተዳደር የወጣ አዋጅ ቁጥር 621/2001 ተከትሎ የተገቢውን የህግ ስነ-ስርዓት ሳይከተልና፣ ፍርድ ቤት ውሳኔ እና ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ኢሰመጉ በባንክ ውስጥ የነበረው ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ሊታገድ ችሏል፡፡ ምንም እንኳን ታግዶ የነበረው ገንዘብ በ2011 ዓ.ም የተለቀቀ ቢሆንም ይህም ዕገዳ በወቅቱ ተቋሙ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ እጥረት እንዲያጋጥመው ምክንያት ሆኖ ነበር፣
- በ1997 ዓ.ም የተደረገውን አገራዊ ምርጫ ተከትሎ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ሲመረምሩ እና ሲከታተሉ በነበሩ የኢሰመጉ ሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ሰራተኞችና አባላት ላይ ከፍተኛ የሆነ እስር በዘመቻ መልክ የተፈጸመ ሲሆን ይህንን እስር እና ተያይዞ ይመጡ የነበሩ የደህንነት ስጋቶችን በመሸሽ በህይወት ለመቆየት ሲሉ በርካታ ቁጥር ያላቸው የኢሰመጉ ሰራተኞች፣ የስራ ኃላፊዎች እና አባላት ሀገር ለቀው ለመሰደድ ተገደዋል፣
- የኢሰመጉ ዋናው ጽ/ቤት ሁለት ሰራተኞች በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል በከምባታና አላባ፣ ጠምባሮ ዞን፣ በአሞ ሸለቆ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ውስጥ በወቅቱ ተከስቶ የነበረውን ግጭት ለማጣራት መጋቢት 10 ቀን 1993 ዓ.ም ወደ ስፍራው የተንቀሳቀሱ ሲሆን የአካባቢው ፖሊስ ከሁለቱ ባለሞያዎቻችን ጋር የተነጋገሩ ሰዎችን አስረዋል፣ ሰራተኞቹ ትራንስፖርት እንዳያገኙ ለአገልገሎት ሰጪ ሰራተኞች ትዕዛዝ አስተላልፈዋል፣ ሰራተኞቹ በተደጋጋሚ በፖሊስ ብርበራ ተደርጎባቸው በመጨረሻም መጋቢት 11 ቀን 1993 ዓ.ም በግዳጅ ወደመጡበት እንዲመለሱ ተደርገዋል፣
- ታህሳስ 10 ቀን 1993 ዓ.ም የኢሰመጉ ባህርዳር ጽ/ቤት ባለሙያ የነበሩ፣ የኢሰመጉ ዋናው መስሪያ ቤት ሰራተኛ የነበሩና የአዲስ አበባ ነዋሪ የነበሩ አንድ ግለሰብ በምስራቅ ወለጋ በተለያዩ ቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ውስጥ በወቅቱ የተከሰተውን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ለማጣራት በሄዱበት በአካባቢው ፖሊስ ከህግ አግባብ ውጪ ለ15 ቀን፣ ለ1ቀን ከግማሽና ለ7ነ ቀን ታስረው ከቆዩ በኋላ በገንዘብ ዋስ ተለቀዋል፣
- ግንቦት 30 ቀን 1990 ዓ.ም የኢሰመጉ ህግና አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ አባልና የመልዕክተ ኢሰመጉ መጽሔት አዘጋጅ የነበሩት አቶ ተስፋዬ ታደሰ በመንግስት የደኅንነት አባላት አዲስ አበባ ከተማ ገርጂ አካባቢ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው አካባቢ ከምሽቱ 2፡30 አካባቢ በአሰቃቂ ሁኔታ የተገደሉ ሲሆን ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ የድርጊቱን ፈጻሚዎች በማጣራት ምንም አይነት የህግ ተጠያቂነት በጥቃት

ፈጻሚዎች ላይ ያልተመሰረተ ሲሆን የክሰ መዝገቡም ሊገኝ እንዳልቻለ ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፣

- ከመስከረም 26 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ የኢሰመጉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል በመሆን ሲያገለግሉ የነበሩት አቶ አሰፋ ማሩ ሚያዚያ 30 ቀን 1989 ዓ.ም ከመኖሪያ ቤታቸው በአንድ ኪሎ ሜትር ርቀት አካባቢ ከፖሊስ መኪና ውስጥ ከተቀመጠ የፌደራል ፖሊስ በተደጋጋሚ በተተኮሰ ጥይት ጭንቅላታቸውን እና ደረታቸውን ተመተው የተገደሉ ሲሆን ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ምንም አይነት የህግ ተጠያቂነት አልተመሰረተም፣
- የኢሰመጉ የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች በተደጋጋሚ በመንግስት የጸጥታና የደኅንነት አካላት በግዳጅ ቢሯቸው ድረስ በመጥራት ጭምር በሚደርስባቸው ጥቃት፣ ህገ ወጥ እስራት ከፍተኛ ጫና፣ ዛቻ እና ማስፈራሪያ ምክንያት በተደጋጋሚ ጊዜ ስራቸውን በነጻነት እንዳይሰሩ ከማድረጉም ባሻገር ከስራቸው እንዲለቁ ተገደዋል አሁንም እየለቀቁ ይገኛሉ፣
- ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመንግስት የጸጥታና የደኅንነት አካላት በተደጋጋሚ የኢሰመጉ ቢሮዎች ድረስ በአካል በመምጣት ልዩ ልዩ ጫናዎችን በመፈጸም ላይ ይገኛሉ፡፡
- ኢሰመጉ በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ ቀጠና ጽ/ቤት በሰራተኞቹ ላይ በሚደርሰው ጥቃት፣ ከፍተኛ ጫናና የደኅንነት ስጋት አስገዳጅነት ምክንያት የተወሰኑ ቀጠና ጽ/ቤቶቹን ለማጠፍና ለመዘጋት ተገዷል፣

በእዚህ መግለጫ ላይ በቀናት ቅደም ተከተል አድርጎ ለማስቀመጥ አዳጋች የሚሆነው በኢሰመጉ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ላይ የሚደርሰው ዛቻ፣ ማስፈራራት፣ ክትትል፣ የዲጂታል ጥቃት፣ ውንጀላዎች፣ የተለያዩ የድርጅቱና የስራ ኃላፊዎች ማኅበራዊ ድህረገጾችን በመጥለፍ የኢሰመጉና የስራ ኃላፊዎችን ጽሁፍ ያልሆኑና ከተቋቋመበት ዓላማ ጋር የሚቃረኑ ነገሮችን በመለጠፍ የድርጅቱን እንዲሁም የኃላፊዎቹን ገጽታ የማበላሸት፣ የድርጅቱንና የኃላፊዎቹን ተቀባይነት የማሳጣት ድርጊቶች እና ሌሎችም ሲሆን በተደጋጋሚ ጊዜ ይህ ድርጊት ባህሪውን እየቀየረ መጠኑን እየጨመረ ሲፈጸም ቆይቷል አሁንም አስጊ በሆነ ሁኔታ በመቀጠል ላይ ይገኛል፡፡

ተያያዥ የህግ ግዴታዎች[1]

በእዚህ ልዩ መግለጫ ላይ በተገኘት ግኝቶች መሰረት የሚከተሉት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተፈጽመዋል፡፡

በህይወት የመኖር መብት እና የአካል ደኅንነት መብት፡

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (UDHR) አንቀጽ 3፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል-ኪዳንም (ICCPR) በአንቀጽ 6(1) እና 9(1) ላይ እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት እንዳለው ያረጋግጣል። ይህንኑ መብት በማረጋገጥ፣ መንግሥታት በቃል-ኪዳኑ (ICCPR) የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸውም በአንቀጽ 2(1) እና 2(2) ይደነግጋል።

የአፍሪካ ቻርተር በሰዎች እና ህዝቦች መብቶች (ACHPR) አንቀጽ 4 ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደህንነት መብቱ ሊከበርለትና ሊጠበቅለት እንደሚገባና እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ ሊነፈግ እንደማይችል ተመላክቷል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 14 “ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው” ሲል ይደነግጋል። በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 15 ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት እንዳለውና በሕግ ከተደነገገው ውጪ ሕይወቱን ሊያጣ እንደማይችል በግልፅ ደንግጓል፡፡ በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት በአንቀጽ 16 ላይ ማንም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው ሲል ያስቀምጣል፡፡ በእነዚህ ዓለም አቀፍ፣ አህጉር አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ህጎች ላይ የመንግስት ዋነኛ ኃላፊነት የዜጎችን መብት የማክበር፣ የማስከበር እና የሚሟላት እንደሆነ ይታወቃል፡፡

የንብረት ውድመት በተመሳሳይ የንብረት መብትንም ብንመለከት በቂ መኖሪያ እና መጠለያ የማግኘት መብት በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ እና በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ መብቶች እውቅና የተሰጠው መብት ሆኖ እናገኘዋለን። ማንም ሰው ለራሱና ለቤተሰቡ ጤንነትና ደህንነት በቂ በሚሆን የኑሮ ደረጃ የመኖር መብት ያለው ሲሆን ይህም ምግብን፣ ልብስን፣ መጠለያን ጨምሮ አስፈላጊ የሆኑ ማህበራዊ አገልግሎቶችን የማግኘትንና እነዚህን ከመሳሰሉ ለመኖር መሰረታዊ የሆኑ ነገሮችን ከሚያሳጡ ድርጊቶች መጠበቅን ይጨምራል።

በአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 14 እና በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(1) መሰረት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት የመሆን መብቷ/ቱ ተረጋግጧል። ይህ መብት የህዝብ ጥቅምን ለማስጠበቅ በሌላ ሁኔታ በህግ እስካልተገደበ ድረስ ወይም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት መጠቀምን ይጨምራል። እንዲሁም በዚሁ ህገመንግስት አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 7 ላይ በግልጽ እንደተደነገገው ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው።

[1] በሲዳማ ክልል የተፈጸመውን ከመኖሪያ ቤት መብት ጋር ተያይዞ ያሉ የመብቶች ድንጋጌዎችን ከአሰመጉ 153ኛ ልዩ መግለጫን ይመልከቱ

ህገወጥ እስራት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 17 እንደተደነገገው ማንም ሰው በህግ በተደነገገው መሰረት ካልሆነ በቀር ነፃነቱን አይነጠቅም፤ ማንም ሰው በዘፈቀደ ሊታሰር አይችልም፣ ማንም ሰው ያለ ክስ ወይም የጥፋተኝነት ክስ ሊታሰር አይችልም። ኢትዮጵያ ፈርማ ከተቀበለቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች አንዱ የሆነው የተባበሩት መንግስታት ቻርተር መሰረት መንግስት የዘር፣ የፆታ፣ የቋንቋና የእምነት ልዩነት ሳያደርግ ሰብዓዊ መብቶችን እና መሰረታዊ ነፃነቶችን ለማክበር እና ለማስከበር መስራት እንዳለበት ይደነግጋል። ነገር ግን የምርመራው ግኝት እንደሚያሳየው የህግ አካላት ሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ሲፈጽሙ ተስተውለዋል ከዚህም መሃል ያለፍርድ እስራት (Arbitrary Arrest) ይገኝበታል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 19 (አስራ ዘጠኝ) እንደሚደነግገው ወንጀል ፈጽመዋል በመባል የተያዙ ሰዎች የቀረበባቸው ክስና ምክያቶቹ በዝርዝር ወዲያውኑ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲነገራቸው መብት ይሰጣል። በተጨማሪም የተያዙ ሰዎች በ48 (በአርባ ስምንት) ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅርብ መብት አላቸው። ይህ ካልሆነ አካላቸው ነጻ እንዲወጣ የመጠየቅ መብት አላቸው። አንቀጽ 21 እንደሚያስቀምጠው በህግ ከለላ ስር ያሉ ሰዎች በትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ጓደኞቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸው እና ከሕግ አማካሪዎቻቸው ጋር የመገናኘት መብት አላቸው።

የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን በአንቀጽ 9 (ዘጠኝ) እንደሚደነግገው ማንኛውም ሰው የሰውን ነፃነትና ደህንነት የማግኘት መብት አለው። ማንም ሰው በዘፈቀደ ሊታሰር አይችልም። ማንም ሰው በህግ በተደነገገው መሰረት ካልሆነ በቀር ነፃነቱን አይገፈፍም። በህግውጥ እስራት ነፃነቱን የተነጠቀ ማንኛውም ሰው ጉዳዩን በፍርድ ቤት የመከታተል መብት ያለው ሲሆን። ፍርድ ቤቱም ስለ እስር ህጋዊነት የሚገባውን ማጣራት አድርጎ ሳይዘገይ ወስኖ እስሩ ህጋዊ ካልሆነ ከእስር ነጻ ማድረግ አለበት።

ጸታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች፡

የሰብዓዊ መብቶች ዓለም አቀፍ መግለጫ (UDHR)፣ ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን(ICCPR)፣ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን(ICESCR) ለሴቶች እኩል ሰብዓዊ መብቶችን የሚያጎናጽፉ ሲሆን ከእነዚህም መብቶች መካከል የአካል ደህንነት መብት እና በህይወት የመኖር መብቶች ይገኙበታል። እነዚህን መብቶች የማስከበር ሀላፊነትንም በመንግስት ላይ ይጥላሉ። በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ማንኛውንም አይነት አድሎ ለማስወገድ የወጣው ስምምነት(CEDAW) በአንቀጽ 2 ንኡስአንቀጽ "ለ እና ሐ" ላይ ለሴቶች መብቶች ያለምንም አድሎ ጥበቃ እንዲያደርግ እና እነዚህን መብቶች በፍርድ ቤቶች አለምንም አድሎ እንዲያስከብር በመንግስት ላይ ኃላፊነትን ይጥላል።

በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ማንኛውንም አይነት አድሎ ለማስወገድ የወጣው ስምምነት(CEDAW) የአማራጭ ፕሮቶኮል (optional protocol) ያለው ሲሆን ይህ ፕሮቶኮል በስምምነቱ በተዘረዘሩት መብቶች ላይ ጥሰት የተፈጸመባት ሴት ወይም ሴቶች እራሳቸው ወይም በእነርሱ ምትክ ሌላ አካል በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ማንኛውንም አይነት አድሎ ለማስወገድ የወጣው ስምምነት(CEDAW) ኮሚቴ አቤቱታን እንዲያቀርቡ ለማስቻል የወጣ ፕሮቶኮል ሲሆን ኢትዮጵያ ይህንን ፕሮቶኮል አላጸደቀችም።

የአፍሪካ ቻርተር የሰዎች እና የህዝቦች መብቶች ፕሮቶኮል የሆነው የአፍሪካ ሴቶች መብቶች(Maputo protocol) በመግቢያው ላይ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጾታዊ ጥቃቶች ምንነት ትርጉም ከመስጠት በተጨማሪ በአንቀጽ4 ንኡስ አንቀጽ 2(ሰ) ላይ መንግስት በሴቶች ላይ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በሚፈጽሙ አካላት ላይ ቅጣት እንዲጥል ኃላፊነትን ይጥላል፡፡ በዚህ ስምምነት ላይ የሚገኙ በርካታ አንቀጾች ላይ ማለትም አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ ሐ, መ እና ረ፣ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ ሀ፣ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 3፣ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 27 ላይ ኢትዮጵያ ተአቅቦዎችን ያደረገች በመሆኑ ምክንያት የተጠቀሱት አንቀጾች በኢትዮጵያ ላይ ገዢ አይሆኑም። የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ህገመንግስት አንቀጽ 35 ሴቶች ህገመንግስቱ ያረጋገጠላቸውን መብቶች የመጠቀም መብት እንዳላቸው ይደነግጋል።

አስገድዶ መሰወር (International Convention for the Protection of All Persons from Enforced Disappearance) ላይ በአንቀጽ 1 ላይ እንደሚያሳየው ማንም ሰው በግዳጅ እንዲሰወር አይደረግም። ምንም አይነት ልዩ ሁኔታዎች፣ የጦርነት ሁኔታም ሆነ የጦርነት ስጋት፣ የውስጥ ፖለቲካ አለመረጋጋት ወይም ሌላ ማንኛውም የህዝብ ድንገተኛ አደጋ፣ ለግዳጅ መጥፋት እንደ ምክንያት ልቅርብ አይችሉም። የሚመለከተው አካል ድርጊቶችን ለመመርመር ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 28 ላይ እንደተደነገገው ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች በሰው ልጅ ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን የሰው ዘር የማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣ አስገድዶ ሰውን መሰወር ወይም ኢሰብዓዊ ድብደባ ድርጊቶችን በፈጸሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም፡፡ በህግ አውጪው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግስት አካል ውሳኔዎች በምህረት ወይም በይቅርታ አይታልፍም፡፡

የአገር ውስጥ ተፈናቃዮችን አስመልክቶ ያሉ መብቶች

የካምፓላ ስምምነት በአንቀጽ 2(d) የስምምነቱን አላማ ሲዘረዝር “ለስምምነቱ አባል ሀገራት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በሚመለከት ከመፈናቀል ስለመጠበቅ፣ ከተፈናቀሉም በኋላ ጥበቃ ስለማድረግ እና ሰብአዊ ድጋፍ መስጠትን በተመለከተ ያለባቸውን ሃላፊነት እና ግዴታ ማሳወቅ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡” በተመሳሳይ የሀገር ውስጥ መፈናቀልን ስለመከላከል ስምምነቱ በአንቀጽ 3 ንኡስ አንቀጽ 1(a) ላይ የስምምነቱ አባል ሀገራት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን መከላከል እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን በሚመለከት ያወጣው የመመሪያ መርህ በመርህ 6(1) ላይ ማንኛውም ሰው ከመኖሪያ ቦታው በዘፈቀደ ያለመፈናቀል መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለው መንግስት ዜጎችን የሀገር ውስጥ መፈናቀልን ሊያስከትሉ ከሚችሉ ነገሮች መከላከል እንዳለበት መረዳት እንችላለን፡፡ በዚህም መሰረት በተዘዋዋሪ ዜጎች ከሀገር ውስጥ መፈናቀል የመጠበቅ መብት አላቸው ብለን መደምደም ይቻላል፡፡

በካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 3(ነ)(b) በግልጽ እንደተደነገገው በማህበራዊ ማንነታቸው፤ በሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ አመለካከታቸው የሰዎችን ወይም የማህበረሰቦችን መፈናቀል ሊያስከትሉ የሚችሉ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ መገለልን እና ፍረጃን የመከላከል ኃላፊነት በመንግስት ላይ የሚጥል ሲሆን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህገ መንግስት የክልሉ ባለቤት ብሎ ያስቀመጣቸው በርታ፣ ጉሙዝ፣ ሽናሻ፣ ማኦና ኮሞ መሆናቸውን በመሆኑ ይህ ህገ መንግስት ሌሎች ብሔሮች ላይ ባላቸው ማንነት ምክንያት እንዲገለሉና ሀብት ንብረት ካፈሩበት ቦታ እንዲፈናቀሉ አንዱ መነሻ ምክንያት ሆኗል። መንግስትም ለመፈናቀል ምክንያት የሆኑትን ነገሮች ባለመከላከሉ የብዙ ሰው ህይወት አልፏል፣ ንብረት ወድሟል እንዲሁም ሀብት ንብረታቸውን ጥለው ተፈናቅለዋል።

በተጨማሪም በካምፓላ በስምምነት አንቀጽ 4(ነ) አባል ሀገራት ለሀገር ውስጥ መፈናቀል ምክንያት የሚሆኑ ነገሮችን ለመከላከል እና ለማስቆም ይረዳ ዘንድ በዓለም አቀፍ ህጎች በሰብዓዊ መብቶች እና በሰብዓዊነት ህጎች ላይ የተቀመጡ ግዴታዎቻቸውን ማክበር እንዳለባቸው ይደነግጋል። ይኸው አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 4(d) ላይ ሁሉም ሰው በተጠቃለለ ጥቃት ወይም በሰብዓዊ መብት ጥሰት ምክንያት ከሚደርስ መፈናቀል የመጠበቅ መብት አለው ሲል ዜጎች ከመፈናቀል የመጠበቅ መብት እንዳላቸው ደንግጓል።

ስምምነቱ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ ነ ላይ አባል ሀገራት በድንበሮቻቸው ውስጥ ለሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሰብአዊ ድጋፍ እና ጥበቃ ያለምንም አድልዎ በማቅረብ ረገድ ተቀዳሚ ሀላፊነት እንዳለባቸው ይደነግጋል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን በሚመለከት ያወጣው የመመሪያ መርህ በመርህ 3(ነ) ላይ ከካምፓላ ስምምነት ጋር ተመሳሳይ በሚባል ደረጃ መንግስታት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የመጠበቅ እና ድጋፍ የማድረግ ተቀዳሚ ሀላፊነት እንዳለባቸው በግልጽ አስቀምጧል። ከነዚህ ድንጋጌዎች የምንረዳው በቀዳሚነት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን መርዳት እና ጥበቃ የማድረግ ሃላፊነት የሀገሪቱ መንግስት መሆኑን ነው።

ከካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2(b) እና (c) የጋራ ንባብ እንደምንረዳው መንግስት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በተቻለ መጠን ሳይዘገይ በቂ ሰብዓዊ ድጋፍ ምግብ፣ ውሀ፣ መጠለያ፣ የህክምና እንክብካቤ እና ሌሎች የጤና አገልግሎቶች፣ የንጽህና አጠባበቅ፣ ትምህርት እና የትኛውንም አይነት አስፈላጊ ማህበራዊ አገልግሎት እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይህንን ድጋፍ ለተቀባይ ማህበረሰብ ማድረግ እንዳበት፤ ልዩ ጥበቃ እና ሰብዓዊ ድጋፍ ካሉበት ሁኔታ አንጻር ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ማለትም ከቤተሰቦቻቸው ለተለዩ ህጻናት፣ ለእማወራዎች፣ ለነፍሰጡር ሴቶች፣ ህጻናት ልጆች ላሏቸው ሴቶች፣ ለአዛውንቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ለተላላፊ በሽታ ታማሚዎች መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል።

በተመሳሳይ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን በሚመለከት ያወጣው የመመሪያ መርህ በመርህ 18 እና 19 ላይ እያንዳንዱ የሀገር ውስጥ ተፈናቃይ በቂ የኑሮ ደረጃ የማግኘት መብት እንዳለው፣ መንግስትም

በምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ ቢሆንም ያለ ምንም አድልዎ ቢያነስ አስፈላጊ ምግብ እና ንጹህ ውሀ፣ መጠለያ፣ ልብስና አስፈላጊ የህክምና እና የንጽህና አገልግሎት ማቅረብ እንዳለበት እንደሁም ድጋፍ በሚሰጥበት ሰዓት ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ የህብረተሰብ ክፍሎችንም ጨምሮ ይዟል፡፡

በተጨማሪም ይኸው የመመሪያ መርህ ትምህርትን በሚመለከት በመርህ 23 ላይ ሁሉም ሰው የመማር መብት እንዳለው በመግለጽ ይህ መብት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችም የተሰጠ መሆኑን እና መንግስትም ይህንን መብት በዋናነት ለተፈናቀሉ ህጻናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በነጻና በአስገዳጅ መልኩ ማቅረብ እንዳለበት እንዲሁም ይህ ትምህርት ባህላዊ ማንነታቸውን፣ ቋንቋቸውን እና ሀይማኖታቸውን ማክበር እንዳለበት አስቀምጧል፡፡

በካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 2 (k) እና በአንቀጽ ıı ንኡስ አንቀጽ (2) ላይ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች በጋራ በምንመለከትበት ሰዓት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ደህንነት እና ድጋፍ በሚመለከት በሚወሰኑ ውሳኔዎች ላይ የስምምነቱ አባል ሀገራት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ማማከር እና ውሳኔዎች ላይ ተሳታፊ ማድረግ እንዳለባቸው፤ የስምምነቱ አባል ሀገራት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ወደመጡበት አካባቢ ለመመለስ፣ ተፈናቅለው ባሉበት አካባቢ ለማስፈር ወይም ወደሌላ ቦታ ማዘዋወርን እንዲሁም ሌሎች አማራጮችን በሚመለከት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ነጻ ምርጫ እንዲመርጡ ማስቻል እና ዘላቂ መፍትሄ በማበጀቱ ረገድ ተሳትፏቸውን ማረጋገጥ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡

በተጨማሪም የካምፓላ ስምምነት በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 (e) ላይ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በሌላ የሀገሪቱ አካባቢ ደህንነት የማግኘት እና ህይወታቸውን፣ ደህንነታቸውን፣ ነጻነታቸውን እና ጤንነታቸውን አደጋ ላይ ወደሚጥል ወደመጡበት አካባቢ በግዴታ ከመመለስ ወይም ወደ ሌላ ቦታ ከመዘዋወር የመጠበቅ መብታቸውን አባል ሀገራት የማክበር እና የማረጋገጥ ሀላፊነት እንዳለባቸው በግልጽ አስቀምጧል፡፡

በተመሳሳይ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን በሚመለከት የወጣው የመመሪያ መርህ በመርህ 15 ላይ በግዴታ ወደ መጡበት አካባቢ ከመመለስ ወይም ደህንነታቸውን፣ ህይወታቸውን፣ ነጻነታቸው እና ጤናቸውን አደጋ ላይ ወደሚጥል ወደሌላ አካባቢ በግዴታ ከመዘዋወር የመጠበቅ መብት አላቸው ሲል ይደነግጋል፡ :

የካምፓላ ስምምነት በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የስምምነቱ አባል ሀገራት በአባል ሀገር ጥያቄ መሰረት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ድጋፍ እና ጥበቃ በማድረጉ ላይ መደጋገፍ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ይኸው ስምምነት በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 6 ላይ አባል ሀገራት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በቂ የሆነ ድጋፍ እና ጥበቃ ማድረግ እንዳለባቸው፤ ይህንን ድጋፍ እና ጥበቃ ለማድረግ ያሉ ግብአቶች በቂ ሳይሆኑ ሲቀሩ የዓለም አቀፍ ድርጅቶችን እና ሰብዓዊ ተቋማትን፣ ሲቪክ ማህበራትን እና ሌሎች ተዋናዮችን ማፈላለግ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም የስምምነቱ አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 3 አባል ሀገራት በአንቀጽ 9 ላይ የተቀመጡ

ግዴቶቻቸውን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ሰብዓዊ ተቋማት፣ ሲቪክ ማህበራት እና ሌሎች ተዋናዮች ድጋፍ መወጣት እንዳለባቸው ደንግጓል፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን በሚመለከት ያወጣው የመመሪያ መርህ በመርህ 25 ላይ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የመርዳት ቀዳሚ ሀላፊነት የሀገሪቷ መንግስት መሆኑን በመግለጽ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ ተቋማት እና ሌሎች ተመሳሳይ ባለድርሻ አካላት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እርዳታ በማቅረብ አገልግሎታቸውን የመስጠት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል ይህም ድጋፍ የሀገሪቷ የውስጥ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ እንደመግባት ሊቆጠር እንደማይገባ እና በቅን ልቦና ሊታይ እንደሚገባ በመደንገግ ፈቃደኝነት በዘፈቀደ ሊነፈግ እንደማይገባ በዋናነት የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት አስፈላጊ የሆነውን ሰብዓዊ ድጋፍ ለማቅረብ ሳየችሉ ወይም ፈቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ ፈቃድ ሊከለከል እንደማይገባ ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም የካምፓላ ስምምነት በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ አባል ሀገራት በዓለም አቀፍ ህግ መሰረት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የአፍሪካ ህብረትን እና የተባበሩት መንግስታትን ሀላፊነት እንዲሁም የዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ ድርጅቶችን ጥበቃ እና ድጋፍ የማድረግ ሀላፊነት እንዲያከብሩ ይደነግጋል፡፡

ምክረ ሀሳብ

ከእዚህ በመቀጠል በምርመራ ስራው የተገኙትን ግኝቶች መሰረት በ ማድረግ እና በህግ ትንታኔው ላይ ያሉትን ሰብዓዊ መብቶች መነሻ በማድረግ ለሚመለከታቸው አካላት በየዘርፋቸው ምክረ ኃሳቦች ይቀርባሉ፡፡

1. ለፌዴራል መንግስት የቀረቡ ምክረ ኃሳቦች፡

- መንግስት እና በግጭቱ የሚሳተፉ አካላት በአማራ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተከሰተውን ለበርካታ ሰዎች ህይወት መጥፋት፣ አካል ጉዳት፣ ንብረት ውድመት እና ሌሎችም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶ ች ምክንያት የሆነውን ግጭት በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የበኩሉን አስተዋፅኦ እና ቁርጠኝነት እንዲያሳይ፣
- በአማራ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግ ስት ውስጥ በተከሰተው ግጭት ላይ መንግስት እና በግጭቱ እየተሳተፉ ያሉ አካላት የመለየት መርህ (principle of distiniction)፣ በትጥቅ ግጭት ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማድረግ ያቆሙ ሰዎችን ያለማጥቃት መርህ (The principle on the prohibition to attack those *hors de combat)* ፣ ተገቢ ያልሆነ ስቃይን ከማድረስ የመቆጠብ መርህ (The principle on the prohibition to inflict unnecessary suffering)፣ የተመጣጣኝነት መርህ (The principle of proportionality) እና የአስፈላጊነት መርህ (The principle of necessity) እንዲከተል፣
- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ በተከሰተው ግጭት በሰዎች እና ንብረቶች ላይ ጉዳት ባደረሱ የመንግስት የጸጥታ አካላት እና በግጭቱ ላይ ተሳትፎ እያደረጉ ባሉ ሌሎች አካላት ላይ ተገቢውን ምርመራ በማድረግ በህግ ተጠያቂ እንዲያደርግ፣
- የፌደራል መንግስት እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል መንግስት በተደጋጋሚ በታጣቂ ኃይሎች የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በአስቸኳይ እንዲያስቆሙ፣
- በኦሮሚያ ክልል በተደጋጋሚ በታጣቂዎች ለሚፈጸሙ ጥቃቶች የፌደራል መንግስት የጸጥታ አካላት ከክልሉ መንግስት ጋር በመተባበር ጥቃቶች ሳይደርሱ ቀድሞ የመከላከል ስራን ጥቃቶችም በሚያደርሱ ጊዜ ፈጣን ምላሽ የመስጠት ስራን ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩበትና መሰል ጥቃቶች እንዳይደርሱ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡
- በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በተደጋጋሚ በታጠቁ ኃይሎች የሚፈጸመውን ማንነትን መሰረት ያደረገ ጥቃት የክልሉ መንግስት በቂ ትኩረት ሰጥቶ ለማስቆም ባለመቻሉ ወይም ፈቃደኛ ባለመሆኑ ምክንያት እየደረሱ ያሉ ጥቃቶችን እና ከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ጣልቃ የመግባት ስልጣኑን በመጠቀም በክልሉ በታጠቁ ቡድኖች የሚፈጸሙ ጥቃቶችን እንዲያስቆም፣ ጥቃት ፈጻሚዎችን በህግ እንዲጠይቅ እና በክልሉ የኃላፊነት ቦታ ላይ ሆነው ኃላፊነታቸውን በአግባቡ የማይወጡ የክልሉን አመራሮች በህግ ተጠያቂ እንዲያደርግ፣
- በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከተንዳሆ ግድብ ጋር እና ውሀ አለቃቀቅ ጋር ተያይዞ ለረዥም አመታት ጉዳት ላይ ያሉ በተለይም በአሳይታ ወረዳ ውስጥ ለሚገኙ የክልሉ ነዋሪዎች እና ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች

መንግስት ተገቢውን ድጋፍ እንዲያቀርብ፣ እንዲሁም ግድቡን በማስተዳደር፣ በመቆጣጠር እና ግድቡ የሚያካልላቸውን ተፋሰሶች ስራ በመስራት ረገድ የሚመለከታቸውን የክልሉን እንዲሁም የፌደራል መንግስት ተቋማትን በማስተባበር እና ተገቢውን ጥናት በማድረግ ከግድቡ ጋር ተያይዞ እየደረሱ ያሉ ጥፋቶችን እና በእዚህም ምክንያት ጉዳት እየደረሰባቸው ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን በመለየት ዘላቂ መፍትሔ እና ለተጎጂዎች ተገቢ ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ በአፋጣኝ እንዲያመቻች፣

- ከላይ በተዘረዘሩት ሁሉም አካባቢዎች ላይ የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ለተፈጸመባቸው ሰዎች መንግስት ተገቢውን ካሳ፣ ከደረሰባቸው የአካል እና የስነልቦና ጉዳት ማገገሚያ ህክምና እና ለተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔን እንዲያቀርብ፣
- በትግራይ ክልል ከነበረው የትጥቅ ግጭት ጋር ተያይዞ ከፍተኛ የሆነ ቁጥር ላለው የህገር ውስጥ ተፈናቃይ መንግስት አስፈላጊውን ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲያቀርብ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ረጂ ተቋማትን በማስተባበር አፋጣኝ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ በአስቸኳይ እንዲያቀርብ፣
- በትግራይ ክልል እና በአማራ ክልል መካከል የፖሪቶሪያን ስምምነት አፈጻጸም እና ሌሎች ምላሽ ያላገኙ ጉዮችን ተከትሎ ውጥረቶች እየታዩ ያሉ ሲሆን እነዚህ አለመግባባቶች ለተጨማሪ ግጭትና የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መነሻ ምክንያት እንዳይሆኑ የፌደራሉ መንግስት ያለበትን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ፣
- በኢሰመጉ፣ በስራ ኃላፊዎች፣ ሰራተኞችና አባላት ላይ በፌደራልና በክልል መንግስታት እንዲሁም በከተማ አስተዳደሮች እና በሌሎች የመንግስት አካላት እየደረሱ ያሉ አስጊ ደረጃ ላይ የደረሱ ግድያዎችን፣ ህገ ወጥ እስሮችን፣ ጥቃቶችን፣ ከፍተኛ ጫናዎችን፣ ማስፈራሪያዎችን፣ ዛቻዎችን፣ ማሸማቀቆችን፣ እንግልቶችን፣ ስልታዊ የስራ ገደቦችን፣ የምርመራ ፈቃድና የመረጃ ክልከላዎችን፣ ህገ ወጥ ከትትሎችን፣ ቢሮ ሰበራዎችን፣ የንብረት ነጠቃ እና መውሰድ፣ ስም ማጥፋትና ውንጀላ እና ልዩ ልዩ ጫናዎች በአስቸኳይ እንዲያቆሙ፣
- በእዚህ መግለጫ ላይ የተገለጹት ጥቃቶችና ከፍተኛ ጫናዎች እንዲሁም በሌሎች መሰል የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋማት ላይ እየተፈጸሙ ያሉ ጫናዎች በአገሪቱ ያለው የሲቪል ምህዳር አሳሳቢ ሁኔታ ላይ መድረሱን የሚያሳይ በመሆኑ መንግስት ለሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች የሚያደርገውን ጥበቃ ምቹና አስቻይ የሆኑ የህግና የፖሊሲ ማዕቀፎችን በመዘርጋትና በመተግበር በአገሪቱ ያሉ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች እንዲሁም ተቋማቶቻቸው በነጻነት ተንቀሳቅሰው ደኅንነታቸው ተጠብቆ የሰብዓዊ መብቶች የማስከበር ስራዎችን የሚሰሩበት ሁኔታ እንዲፈጥር፣

2. ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቀረቡ ምክረ ኃሳቦች፡

- በክልሉ ቀጥሎ ያለውና ህዝቡን ለከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ቀውስ የዳረገውን ግጭት በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ሁሉንም አካታች የሆነ የሰላም ግንባታ ሂደት እንዲያከናውንና ግጭቱን በመቆጣጠር በክልሉ ያሉ ሰዎች በሰላም የመኖር መብታቸውን እንዲያረጋግጥ፣
- በክልሉ ለሚገኙ አርሶ አደሮች ተገቢውን የማዳበሪያ አቅርቦት ወቅቱን በጠበቀ መልኩ እንዲያቀርብ፣

- በክልሉ በተነሱ ግጭቶች ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የፈጸሙ አካላትን ለህግ በማቅረብ ተጠያቂ እንዲያደርግ፣
- ታራሚዎች እና ተጠርጣሪዎች የሚገኙባቸውን ማቆያዎች ተገቢውን ጥበቃ በማድረግ የታራሚዎችን፣ የተጠርጣ ሪዎችን እና የጸጥታ አካላትን ደህንነት እንዲያስጠብቅ፣
- በትግራይ ክልል እና በአማራ ክልል መካከል የፐሪቶሪያን ስምምነት አፈጻጸም እና ሌሎች ምላሽ ያላገኙ ጉዮችን ተከትሎ ውጥረቶች እየታዩ ያሉ ሲሆን እነዚህ አለመግባባቶች ለተጨማሪ ግጭትና የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መነሻ ምክንያት እንዳይሆኑ የአማራ ክልል መንግስት ያለበትን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ፣

3. ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቀረቡ ምክረ ኃሳቦች፡

- የኦሮሚያ ክልል መንግስት በክልሉ በተጋጋሚ በታጣቂ ኃይሎች የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በአስቸኳይ እንዲያስቆሙ፣
- የኦሮሚያ ክልል መንግስት የህዝቡን ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት እያለባቸው ይህንን በቸልተኝነት ሳያደርጉ የቀሩ የመንግስት አካላትን በህግ እንዲጠይቁ፣
- ምስራቅ አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ የተለያዩ ቀበሌዎች ውስጥ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የፈጸሙ አካላትን በህግ እንዲጠይቅ፣
- በምስራቅ አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ውስጥ ባሉ ቀበሌዎች ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ለተፈጸመባቸው ሰዎች ተገቢው ካሳ እንዲሰጥ፣
- በኦሮሚያ ክልል ህዳር 14 ቀን 2016 ዓ.ም ቄለም ወለጋ ዞን፣ ጊዳሚ ወረዳ በኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ አባላት ላይ ግድያ የፈጸሙ አካላትን የክልሉ መንግስት በህግ ተጠያቂ እንዲያደርግ፣
- በኦሮሚያ ክልል በተደጋጋሚ በታጣቂዎች ለሚፈጸሙ ጥቃቶች የክልሉ የጸጥታ አካላት ጥቃቶች ሳይደርሱ ቀድሞ የመከላከል ስራን ጥቃቶችም በሚደርሱ ጊዜ ፈጣን ምላሽ የመስጠት ስራን ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩበትና መሰል ጥቃቶች እንዳይደርሱ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ፣

- በሻሸመኔ ከተማ እንዲሁም በሌሎች የአዲስ አበባና የኦሮሚያ ክልል ከጳጳሳት ሹመት ጋር ተያይዞ በተነሳ ግጭት በምዕመናን ላይ ሞት እንዲሁም የአካል ጉዳት ደርሷል። ሆኖም ጉዳት አድራሾች ለፍርድ ያልቀረቡ በመሆኑ ወንጀል ሰርቶ ተጠያቂ አለመሆን እየተለመደ እንዲመጣ ምክንያት የሚሆን በመሆኑ የሚመለከተው የፌደራልም ሆነ የኦሮሚያ ክልል መንግስት አጥፊዎችን ለህግ እንዲያቀርብ፣

4. ለትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር የቀረቡ ምክረ ኃሳቦች፡

- ጊዜያዊ አስተደደሩ በክልሉ በመንቀሳቀስ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለሚመረምሩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ላልሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማትና ለሌሎች ተቋማት ተገቢውን ፈቃድ በመስጠት እና መረጃ በማጋራት ኃላፊነቱን እንዲወጣ፣

- በክልሉ የተከሰተውን ርሀብ ተከትሎ እየደረሱ ላሉ ከፍተኛ ጉዳቶች ተገቢውን ትኩረት በመስጠትና ከፌደራል መንግስት ጋር በመተባበር አፋጣኝ ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲያቀርብ፣
- በሰሜን ኢትዮጵያ ክፍል ተከስቶ በነበረውን የትጥቅ ግጭት ምክንያት እንዲሁም የትጥቅ ግጭቱ በፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ከተፈጸመ በኋላ በሴቶች ላይ ለተፈጸሙ ጾታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች የክልሉ መንግስት ትኩረት ሰጥቶ በመስራት አፋጣኝ ፍትህ፣ የህክምና ድጋፍ፣ የስነልቦና ድጋፍ እና ሌሎችም አስፈላጊ ድጋፎችን እንዲያቀርብ፣
- በነበረው የትጥቅ ግጨት ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች በተለይም ለሴቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያንና በሌሎችም ተገቢውን ድጋፍ እና ከጉዳት ማገገሚያ እርዳታዎን እንዲያቀርብ፣
- ከላይ የተጠቀሰውን ግጭት ተከትሎ የደረሱ ማህበራዊ ተቋማትን ማለትም እንደ ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል እና ሌሎችንም መሰረተ ልማቶች መልሶ የማቋቋም ስራዎች ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ክልሉ እንዲሰራና ማህበረሰቡ የሚገባውን ጥቅም እንዲያገኝ እንዲያደርግ፣
- በትግራይ ክልል እና በአማራ ክልል መካከል የፕሪቶሪያን ስምምነት አፈጻጸም እና ሌሎች ምላሽ ያላገኙ ጉዮችን ተከትሎ ውጥረቶች እየታዩ ያሉ ሲሆን እነዚህ አለመግባባቶች ለተጨማሪ ግጭትና የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መነሻ ምክንያት እንዳይሆኑ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ያለበትን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ፣

5. ለጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቀረቡ ምክረ ኃሳቦች፡

- ክልሉ በውስጡ ለሚገኙ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ተገቢውን ጥበቃ እንዲያደርግ
- ለአገር ውስጥ ተፈናቃዮች በቂ የሰብዓዊ ድጋፍ እንዲያቀርብ፣
- የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ላይ ጥቃት የፈጸሙ አካላትን በህግ ተጠያቂ እንዲያደርግ፣
- በክልሉ በተደጋጋሚ የሚነሱ የጎሳ ግጨቶች ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እንዲፈጸሙ ምክንያት እየሆኑ በመሆናቸው የክልሉ መንግስት በዘላቂነት የእነዚህ ግጭቶች መነሻ የሆኑ ምክንያቶችን እንዲፈታ፣
- ድንበር ተሻግረው በአጎራባች አገሮች የሚፈጸሙ የጎሳ ጥቃቶች ለማስቆም የክልሉ መንግስት እንዲሁም የፌደራል መንግስት አስፈላጊ የሆነውን የመንግስት የጸጥታ አካል በቦታው በማስፈር የነዋሪዎችን ደኅንነት እንዲያስጠብቅ፣

6. ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቀረቡ ምክረ ኃሳቦች፡

- በክልሉ ከተንዳሆ ግድብ ጋር ተያይዞ ለረዥም አመታት ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች በመለየት፣ ተገቢውን ጥናት በማድረግ፣ ከሚመለከታቸው የፌደራል መንግስት ተቋማት ጋር በመተባበር ጉዳቱን የማስቆም፣ የቅድመ ጥንቃቄ፣ ተፋሰሶችን ከደለል የማጽዳት፣ የግድቡን አካባቢ ደህንነት በማስጠበቅ፣ በግድቡ ዙሪያ ውሃ የሚቀበሉ ተፋሰሶችን አስፈላጊውን የጎርፍ መከላከል ስራ እና የእድሳት ስራ የመስራት ስራዎችን በአፋጣኝ እንዲሰራ እና ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች በመለየት የጉዳት መጠናቸውን በማስላት ተገቢውን ካሳ በአስቸኳይ እንዲከፍል

እንዲሁም በእዚህ ምክንያት ለተፈናቀሉ ሰዎች ተገቢውን አፋጣኝ እርዳታ እንዲያቀርብ፣ በውሀ ምክንያት የወደሙ የትምህርት፣ የጤና እና ሌሎች መሰረታዊ አቅርቦቶችን መልሶ እንዲያቋቁም እንዲሁም ተቀዳሚ ተጠያቂነት እና ኃላፊነት የክልሉ መንግስት እንደሆነ በመረዳት ኃላፊነቶችን ከመሸሽ በመቆጠብ አፋጣኝ እና ዘላቂ መፍትሔ በአስቸኳይ እንዲያቀርብ፣

- በክልሉ በሰሜን ኢትዮጵያ ተከስቶ የነበረውን የትጥቅ ግጭት ተከትሎ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ገለልተኛ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማት እንዲያጣሩ ምቹ ሁኔታዎችን እንዲፈጥር
- በክልሉ በሰሜን ኢትዮጵያ ተከስቶ የነበረውን የትጥቅ ግጭት ተከትሎ ጉደት ለደረሰባቸው አካላት የክልሉ መንግስት ተገቢውን ድጋፍ እንዲያቀርብ፣
- ከላይ የተጠቀሰውን ግጭት ተከትሎ የደረሱ ማህበራዊ ተቋማትን ማለትም እንደ ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል እና ሌሎችንም መሰረተ ልማቶች መልሶ የማቋቋም ስራዎች ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ክልሉ እንዲሰራና ማህበረሰቡ የሚገባውን ጥቅም እንዲያገኝ እንዲያደርግ፣

7. ለቤንሻንጉሉ ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቀረቡ ምክረ ኃሳቦች፡

- በክልሉ ያሉ ማንነትን መሰረት ያደረጉ ልዩነቶችን ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ለጥቃቶች በር እየከፈቱ ያሉ አመለካከቶችን፣ ህጎችን እና ልማዶችን በማሻሻል ኃላፊነቱን እንዲወጣ፣
- በጥቃት ወቅት በተለየ መልኩ ተጋላጭ ለሆኑ እንደ ሴቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ሌሎችም ተጋላጭ ለሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ትኩረት በመስጠት መንግስት ጥበቃ እና ድጋፍ እንዲያደርግ፣
- መንግስት ታጣቂዎችን ከማህበረሰቡ ጋር ከመቀላቀሉ በፊት ተገቢውን የትጥቅ ማስፈታት ሂደቶችን ማስፈጸም አለበት፣
- በክልሉ ለረዥም ጊዜ በታጣቂ ኃይሎች እየተፈጸመ ያለውን ጥቃት ለማስቆም የአገር ሽማግሌዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ጋዜጠኞች፣ ሚዲያዎች፣ በአካባቢዎቹ የሚንቀሳቀሱ ዓለም አቀፍ እና አገር በቀል ድርጅቶች፣ ሲቪል ማኅበራት እና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን አስተዋጾ እንዲያበረክቱ፣

8. ደቡብ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቀረቡ ምክረ ኃሳቦች፡

- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በደራሼ ዞን ደራሼ ከተማ አርጉባ ጣናኦ ቀበሌ ውስጥ በመደራጀት በተማሪ አምደወርቅ ከተማ እና በአቶ ጋዲሴ ካሳ ላይ ግድያ የፈጸሙ አካላትን የክልሉ መንግስት በህግ ተጠያቂ እንዲያደርግ፣
- በክልሉ የሚፈጸሙ ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እንዲቆሙ የክልሉ መንግስት ያለበትን ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር፣ የማስከበር እና የማሟላት ኃላፊነት እንዲወጣ፣
- አርጉባ ጣናኦ ቀበሌ በተፈጸመ ጥቃት ጉበረት ያወደሙ ሰዎችን የክልሉ መንግስት በህግ ተጠያቂ እንዲያደርግና ንብረታቸው ለወደመባቸው ሰዎች ድጋፍ እንዲያደርግ፣

- አርጉባ ጣናአ ቀበሌ የተፈጸመውን ጥቃት የክልሉ መንግስት በዘላቂነት እንዲፈታ እና መሰል ጥቃቶች እንዳይፈጸሙ ተገቢውን ጥበቃ እንዲያደርግ፣
- በደራሼ ዞን ጋቶ መንደር 1 ቀጠና 9 ውስጥ በካኖላ ከበደ ኩሴ ላይ ግድያ የፈጸመውን የፖሊስ አካል ዞኑ በህግ ተጠያቂ እንዲያደርግ፣

9. ለሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቀረቡ ምክረ ኃሳቦች፡

- በክልል ማዕከላዊ ሲዳማ ዞን ሎካ አባያ ወረዳ በሚገኙ አልዳቦ፣ ጭረቻ፣ ቡራ ቡከቶ እና ፉልቃ ቀበሌዎች ላይ ቤቶቻቸው ከሎካ አባያ ወረዳ ፓርክ ክለላ ጋር ተያይዞ በህገ ወጥ መንገድ ለተቃጠለባቸው ሰዎች የክልሉ መንግስት ተገቢውን የንብረት ውድመት ጥናት በማድረግ ካሳ እንዲከፍላቸው፣
- ቤቶቻቸው የተቃጠሉባቸው ነዋሪዎች ይህ መግለጫ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ቤቶቻቸው በተቃጠሉባቸው አካባቢዎች ላይ በቅጠል በተሰራ ትናንሽ መጠለያዎች ጫካ ውስጥ ያሉ በመሆኑክልሉ መንግስት ከነዋሪዎቹ ጋር ተገቢውን ውይይት በማድረግ ቅያሪ ቤት እንዲሰጥ እና ተገቢውን ካሳ እንዲከፍል የእንደሁም ይህ እስከሚሆን ድረስ ጊዜያዊ መጠለያን እንዲያዘጋጅላቸው፣
- ቤቶቻቸው የተቃጠሉባቸው ሰዎች ላይ ከክልሉ መንግስት የሚደርሱ ዛቻ እና ማስፈራራቶች እንዲሁም የሚፈጸሙ እስራቶች እንዲቆሙ፣
- በክልሉ መንግስት የሚደረጉ የልማት ማፈናቀሎች በተገቢው ጥናት፣ ህዝቡን በማከለ እና ባወያየ መልኩ፣ ተገቢውን ካሳ በመክፈል፣ በህግ አግባብ እና አድሎ ባለማድረግ እንዲከናወኑ፣

10. ተጋላጭ የማኅበረሰብ ክፍሎችን በሚመለከት የቀረቡ ምክረ ኃሳቦች፡

- በተለያዩ ምክንያቶች በእዚህ ልዩ መግለጫ ላይ በተዘረዘሩ አካባቢዎች ላይ ማለትም በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በጋምቤላ፣ በአፋር፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በደቡብ ኢትዮጵያና በሲዳማ ክልሎች ላይ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ህጻናት፣ የአእምሮ ህሙማን፣ አረጋውያን፣ ህዳጣን የማህበረሰብ ክፍሎች፣ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ሌሎችም ተጋለጭ የማህበረሰብ ክፍሎች ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የተፈጸመባቸው በመሆኑ የሚመለከታቸው የተጠቀሱት የክልል መንግስታትና የፌደራል መንግስት ለእነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች ልዩ ተገቢ ትኩረት በመስጠት ለደረሰባቸው ጉዳት አፋጣኝ መፍትሔ እና ተገቢውን ካሳ እንዲሰጡ፣
- በተጠቀሱት ክልሎች አዲስ የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች እንዴት አድርገው ከጉዳታቸው ጋር መኖር እንደሚችሉ ለማሳወቅና ከደረሰባቸው ከፍተኛ የሆነ ስነልቦናዊ እና አካላዊ ጉዳት ማገገም እንዲችሉ ክልሎቹ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍ እንዲያደርጉ፣
- በተጠቀሱት ክልሎች ውስጥ ጾታዊ ጥቃት ለተደረሰባቸው ሴቶች ተገቢውን ህክምና፣ የህግ ድጋፍ እና የስነልቦና ድጋፍ በአስቸኳይ የክልሎቹ መንግስታት፣ የፌደራል መንግስትና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲያደርጉ፣

- በግጭት አውድ እየተፈናቀሉ ለሚገኙ ሰዎች የፌደራል እንዲሁም የተጠቀሱት የክልል መንግስታት በመፈናቀል ወቅት፣ በመፈናቀል ሂደት ውስጥ እና ከተፈናቀሉ በኋላ ለሚደርስባቸው የጉበረት ውድመት ተገቢውን ካሳ እንዲከፍሉ እና ይህ እነዲሆን ለማስቻል መንግስት በካምፓላ ስምምነት ላይ ያደረገውን የካሳ ተአቅቦ እንዲያነሳ እና አዲስ በሚዘጋጀው ረቂቅ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች አዋጅ ላይ ካሳን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን እንዲያካትት፣

11. ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን አስመልክቶ የቀረቡ ምክረ ኃሳቦች፡

- በተለያዩ ጊዜያት በሴቶች ላይ እየተፈጸሙ ያሉ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ላይ መንግስት በቂ ትኩረት በመስጠት ሴቶችን በተመለከተ ያሉ ህጎችን በማሻሻል ለሴቶች ተገቢውን ከለላ የሚሰጥ የህግ ማዕቀፍ እንዲዘረጋ፣
- ፍርድ ቤቶች ጾን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን አስመልክቶ የሚሰጧቸው ውሳኔዎች ህጉ የሚፈቅደው መሆኑን፣ አስተማሪ መሆኑንና ሌሎች ተመሰሳይ ወንጀሎችን እንዳይሰሩ ከልካይ መሆኑን እንዲያረጋግጡ፣
- መንግስት በአፍሪካ ቻርተር የሰዎች እና የህዝቦች መብቶች ፕሮቶኮል የሆነው የአፍሪካ ሴቶች መብቶች(Maputo protocol) ላይ ያደረጋቸው አንዳንድ ተአቅቦዎች ሴቶች ሊኖራቸው የሚገባቸውን መብቶች የሚገድብ በመሆኑ ተአቅቦዎቹን እንዲያነሳ እንዲሁም በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ማንኛውንም አይነት አድሎ ለማስወገድ የወጣው ስምምነት(CEDAW) የአማራጭ ፕሮቶኮል (optional protocol) ለሴቶች ተጨማሪ መብቶችን የሚያጎናጽፍ በመሆኑ ይህንን የአማራጭ ፕሮቶኮል (optional protocol) እንዲያጸድቅ፣
- ሁሉም ባለድርሻ አካላት ማለትም መንግስት፣ የሀይማኖት አባቶች የማህበረሰብ አንቂዎች፣ በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ሲቪል ማህበራት እንዲሁም ግለሰቦች በሴቶች ላይ የሚደርስን ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ለመከላከል በጋራ እንዲቆሙ እና የሴቶች መብቶችን መንግስት እንዲያከብር፣ እንዲያስከብር እና የህግ እንዲሁም የስነ-ስርአት ማሻሻያዎችን እንዲያደርግ የተጠናከረ እና የተቀናጀ የውትወታ ስራን እንዲሰሩ፣

12. ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ምክረ ኃሳቦች፡

- የአገር ሽማግሌዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ፣ ጋዜጠኞች፣ ሚዲያዎች፣ ሲቪል ማህበራት እና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ከላይ በተዘረዘሩት አካባቢዎች ላይ እየተፈጸሙ ያሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እንዲቆሙ የበኩላቸውን አስተዋጾ እንዲያበረክቱ እና በሰላም ግንባታ፣ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ ለህግ የበላይነት እና ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ምትክ የሌለውን ኃላፊነታቸውን እንዲያበረክቱ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀረባል፡
:

- ዓለም አቀፍ ረጂ ተቋማት እንደ UN, IOM, WFP, USAID እና ሌሎችም በአገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች በዋናነት በትግራይ፣ በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች ለተከሰቱ ሰብዓዊ ቀውሶች አፋጣኝ ድጋፍ እንዲያቀርቡ እና የመተባበር ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ፣
- በግጭት አውድ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሱ በመምጣታቸው በተለይም ማንነትን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እየተበራከቱ በመምጣታቸው ሰላም ግንባታ ላይ የሚሰሩ የመንግስት አካላትና ሲቪል ማህበራት እነዚህ ግጭቶች እንዲቆሙ የበኩላቸውን ሃላፊነት እንዲወጡ፣

- የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን በአገሪቱ እጅግ መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያሉ የሃሳብ ልዩነት እና አለመግባባቶችን ለመፍታት የተቋቋመ በሆኑና እነዚህ ልዩነቶቸም አብዛኛውን ጊዜ ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ምክንያት በመሆናቸው ኮሚሽኑ በተቋቋመለት አላማ መሰረት ምክክሮችን በማድረግ በዘላቂነት ያሉ የግጭቶች ምክንያት የሆኑ አለመግባባቶች እንዲፈቱ የበኩሉን ኃላፊነት እንዲወጣ እና ይህም ደግሞ እንዲሳካ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በሙሉ ተባባሪ እንዲሆኑ፣
- በአገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄደው አገራዊ ምክክር ላይ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ቡድኖች ያላቸውን ልዩነቶች በሰላማዊ መንገድ መፍታት እንዲችሉ በምክክርና በውይይቱ ላይ እንዲሳተፉ እና መንግስትም ይህ እንዲሆን የበኩሉን ኃላፊነት እንዲወጣ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽንም ሁኔታዎችን እንዲያመቻች፣
- የሚኒስትሮች ምክርቤት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲን ማጽደቁ የሚታወስ ሲሆን ይህ ፖሊሲ በተገቢው ሁኔታ እንዲፈጸም ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን እንዲወጡ እና ይህም ፖሊሲ አካታች የሆነ አፈጻጸምን እንዲከተል፣
- በዓለም አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍና በአገር አቀፍ ደረጃ ሰብዓዊ መብቶች ላይ የሚሰሩ ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በኢሰመጉ ላይ በመንግስት አማካኝነት እየደረሱ ያሉ አስጊ ደረጃ ላይ የደረሱ ጥቃቶች እና ከፍተኛ ጫናዎችን በመገንዘብ እነዚህ ጥቃቶች እና ከፍተኛ ጫናዎች እንዲቆሙና ተጠያቂነት እንዲሰፍን እንዲያደርጉ፡፡ እንዲሁም ከኢሰመጉ ጎን በመቆም አስቸኳይ ድጋፍ እና ከለላን በማቅረብ የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ፣
- በመጨረሻም አገራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለማ አቀፋዊ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማት እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ኢሰመጉ በእዚህ አስቸጋሪ ወቅት ከመንግስት እየገጠሙት ያሉት ጥቃቶችና ከፍተኛ ጫናዎች በአስቸኳይ እንዲቆሙ የበኩለቸውን እንዲያደርጉና ኢሰመጉ በአገሪቱ ያለው የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ እንዲሻሻል የበኩሉን አስተዋጾ እንዲያደርግ ድጋፍና ከለላ ለኢሰመጉ እና በተቋሙ ለሚሰሩ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች እንዲያቀርቡ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት

  ፖ.ሳ.ቁጥር ፡- 80001፣ ኢ-ሜል፡- national.parliament@telecom.net.et

  ፋክስ ፡- (+251) 011 155-0400፣የስልክ ቁጥር ፡- (+251) 011 124-1000፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት፡-

  ፖ.ሳ.ቁጥር ፡- 20122/1000፣ ኢ-ሜል ፡- kumashih@gmail.com

  ፋክስ ፡- (+251) 011 124-1208/011 124-2308፣

  የስልክ ቁጥር ፡- (+251) 011 122-3322፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት፡-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 23698፣ ፋክስ ፡- (+251) 011 551- 8656፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-8186፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ፡-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡-1031፣ ፋክስ፡- (+251) 011 122-6292፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 124-1155፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር

  ስልክ ቁጥር +251 115541868 ፋክስ +25115517775

  ኢሜይል MOJMO@ETHIONET.ET

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሰላም ሚኒስቴር

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 5608፣ ኢ-ሜል፡- mofatr1@yahoo.com

  ፋክስ፡-(+251)011 551-1200፣ የስልክ ቁጥር፡-(+251) 011 515-3204፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 2459፣ ኢ-ሜል፡ ombudsmaneth@ethionet.et

  ፋክስ፡- (+251) 011 553-2073፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 543-336፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን:

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1165፣ ኢ-ሜ፡ hrcom@ethionet.et፣

  ፋክስ፡ (+251) 011 550-4125፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 550-4031፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀነራል ጽ/ቤት:

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 199፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-2744፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለሱማሌ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔጽ/ቤት:

  ፖ.ሳ.ቁጥር 392፣ ፋክስ፡- (+251) 25 775-3429፣

  የስልክ ቁጥር፡ (+251) 257 75 34 29

ጅግጅጋ፣ ኢትዮጵያ

- ለሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት፡

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 588 ፋክስ፡- (+251) 025 775-2325፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 775-4038 / 025 775-3241 ጂግጂጋ፣ ኢትዮጵያ

- ለኦሮሚያ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት፡

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 101769፣ ኢ-ሜል፡- oromiawiev@ethionet.et

  ፋክስ፡- (+251) 011 551-3642 / (+251) 011 551-9633፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 552-4247፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት፡-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 101769 ፋክስ፡- (+251) 011 552-4247

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 555-0455

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት፡-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1324፣ ፋክስ፡- (+251) 058 220-2511፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-2659

  ባሕርዳር፣ ኢትዮጵያ

- ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት፡-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 312 ፋክስ፡- (+251) 058 220-1068፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-0924 / 058 220-0499

  ባህር ዳር፣ ኢትዮጵያ

- ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡-

  የስልክ ቁጥር፡-

  ቦንጋ፣ ኢትዮጵያ

- ለሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዘዳነት ጽ/ቤት

  ኢ-ሜይል አድራሻ፡-sidaamapoffice@gmail.com

  የስልክ ቁጥር፡-

  ሀዋሳ፣ ኢትዮጵያ

- ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት፡-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1546፣ ፋክስ፡- (+251) 046 220-2408፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 046 221-4778/ 046 220-5848፣ ሐዋሳ፣ ኢትዮጵያ

- ለደ/ብ/ብ/ህ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት፡-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 18 ፋክስ፡- (+251) 046 220-1641፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 046 220-9166

  ሃዋሳ፣ ኢትዮጵያ

- ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት፡-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 44፣ ፋክስ፡- (+251) 057 775-0814፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 055 7775-0109፣

  አሶሳ፣ ኢትዮጵያ

- ለትግራይ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት፡-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 291፣

ፋክስ፡- (+251) 034 441-6564፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 034 441-6563፣

መቀሌ፣ ኢትዮጵያ

- ለጋምቤላ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት፡-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 25፣ ፋክስ፡- (+251) 046 220-2408፣

  ጋምቤላ፣ ጋምቤላ

- ለጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት፡-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 025

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 047 551-154

  ጋምቤላ፣ ኢትዮጵያ

- ለሐረሪ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት፡-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 952 ፋክስ፡- (+251) 025 666-2530፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 666-1723 / 025 666-1746

  ሐረር፣ ኢትዮጵያ

- ለሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት፡-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 272 ፋክስ፡- (+251) 025 666-0666፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 666-1799

  ሐረር፣ ኢትዮጵያ

- ለአፋር ክልል ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት

  ስልክ ቁጥር (+251) 0336660056

  ሰመራ ኢትዮጵያ

- ለድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የከንቲባ ጽ/ቤት

  የስልክ ቁጥር፡ (+251) 025 ነ ነ 358

  ፋክስ፡ (+251) 025 ነ ነ 19 805

- ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የከንቲባ ጽ/ቤት

  ስልክ ቁጥር (+251) 0118591363